
# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 084 ኅዳር 24 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


# ሀገሪቱ ወደብ አልባ
## መሆኗ እየጨመረ ላለው የዋጋ ንረት አንዱ ምክንያት ነው

**ቃልኪዳን አሳዬ**



አዲስ አበባ፡- ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ ለመጣው የኑሮ ውድነት አንዱ እና ዋነኛው መንስኤ የሀገሪቱ ወደብ አልባ መሆን ነው ሲሉ በጅማ ዩኒቨርሲቲ የቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ መምህርና ተመራማሪ መኮንን ቦጋለ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡

ዶክተር መኮንን ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በሀገሪቷ የዋጋ ንረት ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ መጥቷል፡፡ ለዚህ በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩም የሀገሪቷ ወደብ አልባነት ግን ከዋነኞቹ ምክንያቶች አንዱ ነው ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ በስህተት ያጣችውና እስካሁንም ድረስ ዋጋ እያስከፈላት የቆየውን የወደብ ማልማት እድል የምታገኝ ከሆነ ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ የመጣውን የዋጋ ንረት ከመቅረፍ ባለፈ ዘላቂ ልማትን ለማረጋገጥ አስቻይ ሁኔታን ይፈጥራል ሲሉም ይመክራሉ፡፡

ሀገሪቱ ወደብ አልባ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


# ሀገራዊ ምክክሩ በተፎካካሪ የፖለቲካ ድርጅቶች ዕይታ

**ተስፋ ፈሩ**

ሀገራዊ ምክክሩ ቅድመ ዝግጅት እና ዝግጅት የሚባሉትን ሁለት ምዕራፎች አገባዶ ሦስተኛ ምዕራፍ ወደሆነው ምክክር ለመግባት ጫፍ የደረሰበት ጊዜ ላይ እንገኛለን፡፡ ለመሆኑ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ሀገራዊ ምክክሩን እና የምክክር ኮሚሽኑ እስካሁን ያከናወናቸውን ተግባራት እንዴት ይመለከቷቸዋል?

የኢትዮጵያ ሶሻል ዴሞክራቲክ ፓርቲ /ኢሶዴፓ/ ሊቀመንበር ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ፤ በብሔራዊ ምክክሩ ላይ መሳተፍ ተገቢ ነው ብለን በበኩላችን በፖለቲካ ድርጅት ደረጃ አቋም መያዛቸውን ይናገራሉ፡፡

ኮሚሽኑ በዘረጋው አካሄድ በወረዳ ደረጃ ባሉ ኮሚቴዎች ውስጥ ገብተን አስተዋጽኦ እንድናደርግ ነው ጥሪ ያስተላለፈልን የሚሉት ፕሮፌሰሩ፤ በተጠየቅንበት



ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ



ዮሐንስ መኮንን



አቶ ቀጀላ መርዳሳ

ቦታ ሁሉ አባሎቻችንን መድበን እየተሳተፍን ነው ሲሉ ይገልፃሉ፡፡

ኮሚሽኑ በሚጠራቸው ስብሰባዎችም ድጋፍ በመስጠት በንቃት እንደሚሳተፉ ገልጸው፤ በአጠቃላይ ለሀገራዊ ምክክር የተጠየቅነውን ድጋፍ ሁሉ እያደረግን እንገኛለን ይላሉ፡፡

የምክክሩ ውጤት እንደምናደርገው ጥረትና እንደምንሰጠው ድጋፍ ይወሰናል ያሉት ፕሮፌሰሩ፤ "ፍጹማዊ የሆነ መግባባት ላይ ያድርሰንም፤ ወይም ከዚያ በመለስ የሆኑ

ሀገራዊ ምክክሩር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# "ስንቀራረብ ወደ ኋላ የሚጎትቱንን ችግሮች ማሸነፍ እንችላለን"
## - ከንቲባ አዳነች አቤቤ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- ስንቀራረብ መተዋወቅ ብቻ ሳይሆን ወደ ኋላ የሚጎትቱንን ችግሮች ማሸነፍ የሚቻልበት እድል የሚገኝ መሆኑን መረዳት እንደሚገባ የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ተናገሩ።

በአዲስ አበባ 18ኛው የብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ቀንን ምክንያት በማድረግ የባህል ፌስቲቫል

"ስንቀራረብ ወደ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# በቱሪዝምና ሆቴል
## ዘርፎች ከሁለት ሺህ 500 በላይ ወጣቶች እየሰለጠኑ ነው

ገጽ 4



አቶ ገዛኸኝ አባተ

# የአበባ እርሻ የሚያስከትለው ጉዳት በገለልተኛ አካል ተጠንቶ እንዲቀርብ ቋሚ ኮሚቴው አሳሰበ

ገጽ 3
















# የአምራችና ሸማቹን ትስስር በማጠናከር የዋጋ ንረትን ለማረጋጋት እየተሠራ ነው

**አማን ረሺድ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- የምርቶችን ዋጋ ለማረጋጋት አምራችና ሸማቾች መካከል ያለውን የገበያ ትስስር በተሻለ ሁኔታ ለማጠናከር እየተሠራ መሆኑን የአዲስ አበባ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ገለጸ።

ኮሚሽኑ የምርት አቅርቦትና ገበያ ትስስር ላይ ያተኮረ የውይይት መድረክ ሲያካሂድ የኮሚሽኑ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሀብተየስ ዲሮ እንደገለጹት፤ መድረኩ በዘርፉ ያለውን ተግዳሮት ለመለየት እንዲሁም ከአምራቹ ጋር የገበያ ትስስር ለማጠናከር ይረዳል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን የዋጋ ንረትን ለመቆጣጠር ከአምራችና አልሚ ተቋማት ጋር የገበያ ትስስር በመፍጠር እየሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።

ከአምራችና አስመጪዎች ከዩኒየኖች ጋር የገበያ ትስስርን በመፍጠር የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶችን ያለደላላ ጣልቃ ገብነት በቀጥታ ለሸማቹ እንዲቀርብ እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ኮሚሽኑ ከሰባት ክልሎች ጋር የምርት ትስስር በመፍጠር የምርቶችን ዋጋ ለማረጋጋት እየሠራ መሆኑን ጠቅሰው፤ የኑሮ ውድነቱን ለማረጋጋት በቂ ምርቶች ወደ መዲናዋ እንዲገቡ በቅንጅት እየሠራ ይገኛል ብለዋል፡፡

በመዲናዋ 11 የሸማች ዩኒየኖች፣ 151 መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት እንዲሁም ሰባት መቶ የምርት መሸጫ ሱቆች መኖራቸውን ገልጸው፤ ከገበያ ትስስር አንጻር የሚስተዋሉ ክፍተቶች ለማረም እየተሠራ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

በትስስር መሥራቱ ገበያን ለማረጋጋትና በሸማችና አምራቹ መካከል ያለውን ሰንሰለት በማሳጠር ጥራት ያለውን ምርት ለማቅረብ እንዲያግዝ ጠቁመዋል፡፡

አምራቾችና አስመጪዎች መንግሥት ያመቻቸውን ዕድል በመጠቀም በተመጣጣኝ ዋጋ ምርቶችን ለሸማቾች ማቅረብ እንደሚገባቸው ገልጸዋል።

ችግሩን ለመፍታት ከገበሬዎች ኅብረት ሥራ ዩኒየኖች ጋር ትስስር መፈጠሩን አመላክተው፤ ምርቶች የግዢ ሥርዓቱን ተከትለው ክፍያ እንዲፈጸምባቸው እየተሠራ ይገኛል ብለዋል፡፡

በሸማቹ ጥቆማ መሠረት የምርት እጥረት እንዲፈጠር በሚያደርጉ አመራርና ባለሙያዎች ላይ የእርምት እርምጃ እየተወሰደ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በመዲናዋ የሚታየውን የኑሮ ውድነትንና የምርቶች ዋጋ ለማረጋጋት በዩኒየኖች በኩል በቂ ምርት እንዲቀርብ በትኩረት እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

ሕገ-ወጥ የምርት ግብዓትን ለመከላከል ተገቢውን ክትትል በማድረግ ወጥና የተረጋጋ ገበያ ለመፍጠር በትብብር መስራት ያስፈልጋል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

የሚመረቱ ምርቶችን በጊዜ ለሸማቹ ለማቅረብ የሚያስችል ሁኔታዎች ላይ የሚታዩ ክፍተቶች እንዲፈቱ አስመጪዎችና አምራቾች በመድረኩ አንስተዋል።



# በህላባ ሁለት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ኩንታል ምርት እየተሰበሰበ ነው

**አማን ረሺድ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- ከመኸርና ከበልግ የግብርና ሥራዎች የተገኘው ሁለት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ኩንታል ምርት እየተሰበሰበ መሆኑን በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የሃላባ ዞን ግብርና መምሪያ አስታወቀ፡፡

የሃላባ ዞን ምክትል አስተዳዳሪና የግብርና መምሪያ ኃላፊ አቶ ሀጂ ኑርዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በዞኑ በመኸርና በበልግ እርሻ ከለማው 55 ሺህ 895 ሄክታር መሬት ሁለት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለመሰብሰብ እየተሰራ ነው፡፡

ወቅቱ ምርት መሰብሰቢያ በመሆኑ በዞኑ በሁሉም ወረዳዎችና ቀበሌዎች የደረሱ ሰብሎች እየተሰበሰቡ መሆኑን ጠቁመው፤ እስካሁን 37 ሺህ ሄክታር መሬት ላይ የለሙ የተለያዩ ምርቶችን መሰብሰብ እንደተቻለ አስገንዝበዋል።

የስንዴ፣ ዳጉሳና ጤፍ ምርቶችን ከማሳ ላይ የመሰብሰብ ሥራው እየተጠናቀቀ መሆኑን የጠቆሙት ኃላፊው፤ የምርት ብክነትን ለመቀነስ በተለያዩ ቦታዎች ላይ የምርት ማጨጃና መውቂያ መሣሪያዎች ጥቅም ላይ መዋላቸውን አስታውቀዋል።



**አቶ ሀጂ ኑርዬ**

በተለያዩ አካባቢዎች ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ እየጣለ እንደሚገኝ ገልጸው፤ አሁን ላይ ዝናቡ በመቆሙ በደረሰ ምርት ላይ ጉዳት እንዳያደርስ አርሶ አደሩ፣ የግብርና ባለሙያውና በየደረጃው የሚገኘው አመራር በልዩ ትኩረት እየሠራ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

በዞኑ የስንዴ፣ የማሽላ፣ የጤፍ፣ የበቆሎ፣ የዳጉሳ፣ የቦሎቄና የበርበሬ ልማት በሜካናይዜሽንና በክላስተር የተደገፈ እንዲሆን መደረጉን አቶ ሀጂ አስረድተዋል፡፡


ከመኸር ወቅት የማሳ ዝግጅት እስከ ሰብል አሰባሰብ ስራው ምርታማነትን ለማሳደግ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የሚሰበሰበው ምርት ጥራቱን ጠብቆ ከቤት ፍጆታ ባለፈ ለገበያ እንዲቀርብና የአርሶ አደሩ ተጠቃሚነት እንዲያድግ መምሪያው በትኩረት እየሠራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ኅብረተሰቡ ሰብሉን በፍጥነት እንዲሰበስብ የሚረዱ የንቅናቄ ሥራዎች እየተከናወኑ መሆኑን ምክትል አስተዳዳሪው ጠቁመዋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራትን ጨምሮ ተማሪዎች እና የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች በምርት ስብሰባው ላይ እንዲሳተፉ አቶ ሀጂ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

የብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ትንበያ እንደሚያመለክተው በሚቀጥሉት ቀናት በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ሊቀጥል ስለሚችል በአጭር ጊዜ ውስጥ የደረሱ ሰብሎችን መሰብሰብ ያስፈልጋል ያሉት ኃላፊው፤ ዘመናዊ የአመራረት ዘዴዎችን ለአርሶአደሩ በማስተዋወቅ ጥቅም ላይ ለማዋል፣ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግና የግብርናውን ውጤታማነት ለማሳደግ አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል የማድረጉ ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል፡፡



## በሽታው በከፍተኛ ሁኔታ የመሰራጨት ባህሪ ስላለው በመከላከያ መንገዶች ላይ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል

**ማህሌት ብዙነህ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- የተከሰተው ጉንፋን መሰል በሽታ በከፍተኛ ሁኔታ የመሰራጨት ባህሪ ስላለው በመከላከያ መንገዶች ላይ ትኩረት ማድረግ እንደሚያስፈልግ የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ የኅብረተሰብ ጤና እና ድንገተኛ አደጋዎች ቁጥጥር ዳይሬክተር አቶ ዳንኤል ዳምጠው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በከተማው በተለይም ከጥቅምት ወር መጀመሪያ ጀምሮ በብዙ ሰዎች ላይ ጉንፋን መሰል በሽታ ተከስቷል።

ይህም ወቅታዊ እና በየዓመቱ ከቅዝቃዜ ጋር ተያይዞ የሚከሰት ሲሆን፤ በወረርሽኝ መልክ የሚገለጽ አለመሆኑን አስታውቀዋል።

በመሆኑንም ቢሮው የተከሰተውን የቫይረስ አይነት ለመለየት ከትምህርት ቤቶች፣ ጤና ተቋማት እንዲሁም ከፍተኛ መተላለፊያ በሆኑ ቦታዎች ላይ ከሚገኙ ከ178 ሰዎች ናሙና ተወስዶ ምርመራ አድርጓል ብለዋል።

በዚህም 17 በመቶ በላይ የኢንፍሉዌንዛ ቫይረስ እና ሦስት በመቶ የሚሆነው ከኮቪድ 19 ቫይረስ ጋር የተገናኘ መሆኑ ተረጋግጧል ብለዋል።

ይህ ህመም በተለይም እድሜያቸው ከአምስት ዓመት በታች የሆኑ ህጻናት ላይ የሚከሰት ሲሆን፤ ከመቶ ሰዎች መካከል ሃያ የሚሆኑት ላይ የሚስተዋል መሆኑን አቶ ዳንኤል ተናግረዋል።

ከፍተኛ ራስ ምታት፣ ሳል፣ ከአፍንጫ ብዙ ፈሳሽ መውጣት፣ ጉሮሮን የማቃጠል ስሜት፣ ጡንቻ አካባቢ ህመም፣ የድካም እና የምግብ ፍላጎት መቀነስ የመሳሰሉት ምልክቶች እንዳሉትም አስረድተዋል።

ምልክቶቹ ሲታዩ ወደ ህክምና ተቋም በመሄድ እራስን ከከባድ ህመም መከላከል ያስፈልጋል ብለዋል።

አቶ ዳንኤል በበሽታው የተያዙ ሰዎች አፋቸውን እና አፍንጫቸውን ሳይሸፍኑ ሲያስሉ ወይም ሲያስነጥሱ እንዲሁም ቫይረሱ ያረፈባቸውን ነገሮች ከነኩ በኋላ አፍን፣ አፍንጫ ወይም ዓይንን መንካት ቫይረሱ እንዲሰራጭ የሚያደርጉ መንገዶች መሆናቸውን ገልጸዋል።

ማኅበረሰቡ ትምህርት ቤቶች እንዲሁም ሰው በተሰበሰበበት ቦታዎች የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ጭምብል በማድረግ፣ በሕዝብ ማመላለሻ ትራንስፖርት ውስጥ መስኮቶችን በመክፈት፣ የእጅን ንፅህና በአግባቡ በመጠበቅ እንዲሁም በንክኪ ወቅት እጅን በመታጠብ በሽታውን በቀላሉ መከላከል ይቻላል ብለዋል።

በመሆኑም በሽታው በከፍተኛ ሁኔታ የመሰራጨት ባህሪ ስላለው በመከላከያ መንገዶች ላይ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል ብለዋል።

በበሽታው የተያዙ ሰዎች ህክምናው ከቤት የሚጀምር ሲሆን ህመሙን ለመከላከል እና ለማስታገስ በቂ እረፍት በመውሰድ፣ ፈሳሽና ትኩስ ነገሮች በመጠቀም እና በአካባቢው በቂ የአየር ዝውውር እንዲኖር በማድረግ ብሎም ተገቢውን ህክምና በማግኘት ስርጭቱ እንዳይስፋፋ ማድረግ ይገባል ብለዋል።

ቢሮው በከተማው በሚገኙ በሁሉም ተቋማት ስለበሽታው በቂ መረጃ ከመስጠት ጀምሮ ህክምና ለመስጠት የሚያስፈልጉ መድኃኒቶች አስቀድሞ መሥራቱን ነው የጠቆሙት፡፡

በመሆኑም ኅብረተሰቡ በሽታው ከአንድ ሳምንት በላይ የሚቆይ ከሆነ በአቅራቢያው ወደሚገኝ የህክምናና ተቋም በመሄድ አስፈላጊውን አገልግሎትና የጤና ባለሙያዎች ምክረ ሃሳቦች ማግኘት የሚችሉ መሆኑን አስታውቀዋል።

የሥራ እና ክህሎት ሚኒስቴር
MINISTRY OF LABOR AND SKILLS

# የሙያ ደኅንነትና ጤንነትን ለመጠበቅ አዲስ የአሠራር ሥርዓት እየተዘረጋ ነው

**ተስፋ ፈሩ**

አዲስ አበባ፡- የሙያ ደህንነትና ጤንነትን ለመጠበቅ አዲስ የአሠራር ሥርዓት እየተዘረጋ መሆኑን የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር አስታወቀ።

የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የሙያ ደኅንነትና ጤንነት ዴስክ ኃላፊ ጥዑመእዝጊ በርሄ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ መከላከልን መሰረት ያደረገ አጠቃላይ የሙያ ደኅንነትና ጤንነትን ማስጠበቅ የሚያስችል አዲስ አሠራር እየተዘረጋ ነው።

የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር አጠቃላይ የሥራ ላይ ደኅንነትን ከማረጋገጥ አኳያ ከ12 ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ጋር የጎንዮሽ የመግባቢያ ስምምነት መፈራረሙን ገልጸው፤ ስምምነቱ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶቹ ከዚህ በፊት ያልነበራቸው የየራሳቸው ፖሊሲ እንዲኖራቸው ያደርጋል ብለዋል።

“ሀገር አቀፍ የሥራ ደኅንነትና የሙያ ጤንነት ፖሊሲ እስከዛሬ የሚኒስቴር መስሪያ ቤታችን ፖሊሲ ብቻ ሆኖ ነው የቀረው።” ያሉት ኃላፊው፣ ፖሊሲው ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች የየራሳቸውን ፖሊሲ ማውጣት አለባቸው ቢልም ሳያወጡ መቆየታቸውን ገልጸዋል።

እንደ አቶ ጥዑመእዝጊ ገለጻ፣ ስምምነቱን ከፈረሙት 12 ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ጋር ባለፈው ዓመት በጋራ መሥራት በሚቻልበት መንገድ ላይ ምክክር ተደርጎ የጋራ ዕቅድ ወጥቷል።

እስካሁንም ከስምንቱ ጋር የራሳቸውን ፖሊሲ እንዲያዘጋጁ የማድረግ ሥራ ተጀምሯል ያሉት ኃላፊው፤ የፖሊሲ ዝግጅቱ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶቹ በሥራቸው ባሉት ዘርፎች ደኅንነቱና ጤንነቱ የተጠበቀ የሥራ ቦታ እንዲገነባ ከማድረግ አኳያ የራሳቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ የሚያስችል ነው ብለዋል።

በሀገር አቀፍ ደረጃ ያለው የሙያ ደኅንነትና ጤንነትን ተቆጣጣሪ ከ400 እስከ 500 የሚገመት መሆኑንና ከሀገሪቱ ሕዝብ አንፃር ቁጥሩ አነስተኛ መሆኑን ተናግረዋል።

በቁጥጥር ረገድ ያለውን የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት ለመቅረፍ በዚህ ዓመት በቢኤ ዲግሪ ለተመረቁ አንድ ሺህ ተማሪዎች የሶስት ዙር ስልጠና ለመስጠት ዝግጅቶች መጠናቀቃቸውን ገልጸዋል።

በሌላ በኩል በእያንዳንዱ የሥራ ቦታ ላይ ከአሰሪውና ከሠራተኛው በተውጣጡ አባላት የሥራ አካባቢ የሥራ አመራር ኮሚቴ እንደሚቋቋም ተናግረዋል።

በኮሚቴው ውስጥ አሠሪም ሠራተኛውም እኩል መብት እንደሚኖራቸው አመላክተው፣ ኮሚቴው በተወሰነ ጊዜ እየተገናኘ ስለሥራ አካባቢ ደኅንነትና ጤንነት እንዲወያይ ይደረጋል። በሥራ አካባቢ የደረሱ አደጋዎችንም በዝርዝር ይገመግማል ብለዋል።

አክለውም፣ ይሄን ለማስፈጸም የሚያስችል መመሪያ ባለፈው ዓመት መውጣቱን አውስተው፣ መመሪያውን መሰረት በማድረግ ደንብ እያዘጋጀንና የአሠራር ሥርዓት እየዘረጋን ነው ብለዋል።

እየተዘረጋ ያለው አዲስ አሠራር የኅብረተሰቡን ግንዛቤ በማሳደግ አጠቃላይ የሥራ ላይ ደህንነትና የሙያ ጤንነትን ማስከበር ያስችላል ተብሎ እንደሚጠበቅ ያመላከቱት ኃላፊው፤ በቅድሚያ ግን አሠሪዎችና ሠራተኞች ግንዛቤው እንዲኖራቸው የማድረግ ሥራ መሥራት ላይ ትኩረት እንደሚደረግ ጠቁመዋል።

# የአበባ እርሻ የሚያስከትለው ጉዳት በገለልተኛ አካል ተጠንቶ እንዲቀርብ ቋሚ ኮሚቴው አሳሰበ

**አመለወርቅ ከበደ**



አዲስ አበባ፡- ግብርና ሚኒስቴር የአበባ እርሻ ልማት በአካባቢ ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት በገለልተኛ ቡድን አስጠንቶ እንዲያቀርብ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አሳሰበ፡፡

ቋሚ ኮሚቴው በግብርና ሚኒስቴር የአበባ እርሻ ልማት ምርታማነትና የአካባቢ አያያዝ ሥርዓት ውጤታማነትን በተመለከተ የ2014/2015 በጀት ዓመት ክዋኔ ኦዲት ግኝት ላይ ውይይት አድርጓል፡፡

በወቅቱ የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ ወይዘሮ አራሬ ሞሲሳ እንደገለጹት፤ የአበባ ልማት በሀገሪቱ ከቡና ቀጥሎ ከፍተኛ ገቢ የሚያስገኝ ዘርፍ ቢሆንም የራሱ የአሠራር መመሪያ የለውም።

ከአበባ እርሻ ልማት ጋር ተያይዞ በአካባቢ ላይ የደረሰው ጉዳት በገለልተኛ አካላት ማስጠናት እንደሚገባ ጠቁመው፤ ይህ መሆኑ ተጓዳኝ ችግሮችን ማወቅና የመፍትሄ ርምጃ ለመውሰድ ያግዛል ሲሉ አስረድተዋል።

የአበባ ልማት ያስከተለው ጉዳት በገለልተኛ ቡድን ተጠንቶ ሪፖርቱ እንዲደርሰን እንፈልጋለን ያሉት ምክትል ሰብሳቢዋ፤ ተቋሙ የድርጊት መርሀ ግብሩንም እስከ ህዳር 30 ለቋሚ ኮሚቴውና ለሚመለከታቸው አካላት መላክ እንዳለበት አሳስበዋል፡፡

የአበባ ልማት ሥራው የዜጎችን ደህንነት በጠበቀ መልኩ እንዲሆን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ያለውን ግንኙነት በደንብ በማጠናከር የክትትልና ቁጥጥር እንዲሁም የተጠያቂነት ሥርዓት ሊኖር እንደሚገባ ቋሚ ኮሚቴው አሳስቧል፡፡

ምክትል ሰብሳቢዋ እንዳመላከቱት፤ ለአበባ ልማቱ ፖሊሲና ደንብ ሳይዘጋጅበት እየተሠራ በመሆኑ ዘርፉን ለመምራት የሚያስችል ደንብና አሠራር መዘርጋት ይገባል፡፡

በዘርፉ እየተዘጋጀ ያለው መመሪያ ጸድቆ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ለገንዘብ ሚኒስቴር፤ ለፌዴራል ኦዲት መስሪያ ቤት፤ ለምክር ቤቱ የግብርና ጉዳዮችና ለመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ቋሚ ኮሚቴ እንዲቀርብ ሲሉ ተናግረዋል።

በፌዴራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ዋና ኦዲተር መሰረት ዳምጤ በበኩላቸው፤ ከ2012 ዓ.ም እስከ 2014 ዓ.ም ድረስ በግብርና ሚኒስቴር የአካባቢ እርሻ ልማት አምስት ባለድርሻ አካላትን እና 11 የአበባ እርሻ ድርጅቶች ላይ ትኩረት ያደረገ የኦዲት ክንዋኔ መቅረቡን አመላክተዋል።

በኦዲት ግኝቱ መሰረት ለአበባ እርሻ ልማት የሚገዙ ኬሚካሎች በተገቢው መጠን መግዛት እንደሚገባ እና የአበባ እርሻዎች ሌላ ምርት እንዲለማባቸው ሲደረግ በገለልተኛ አካል የኬሚካል ቅሪታቸው ጥናት መደረግ እንዳለበት አሳስበዋል፡፡

በተጨማሪም የኬሚካል ማከማቸትና አወጋገድ ሂደቱ አካባቢን በማይጎዳ መልኩ ሊሆን ይገባል ሲሉ አስረድተው፤ በሰራተኞች ደህንነት፣ በአካባቢ ጥበቃና የመረጃ አደረጃጀቱን ማዘመን እንደሚገባ ተናግረዋል።

በግብርና ሚኒስቴር የእርሻና ሆርቲካልቸር ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ መለስ መኮንን (ዶ/ር) በበኩላቸው እንደገለጹት፤ የአበባ አልሚ ድርጅቶች የሚጠቀሟቸው ግብአቶችና ኬሚካሎች የሚያመጡትን ተጽዕኖ ለመከላከልና ተገቢ የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ሁኔታዎች እንዲኖሩ የሚያስችሉ ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛል።

በቋሚ ኮሚቴው በተሰጡ አስተያየቶች መሰረት ከሌሎች የሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመሆን በድርጊት መርሀ ግብሩና በኦዲት ግኝቱ መሰረት ለማስተካከል እንደሚሠሩ ገልጸዋል፡፡







# ባህላዊ መድኃኒቶች ለገበያ የሚቀርቡት ፈዋሽነታቸው ሳይረጋገጥ በመሆኑ ኅብረተሰቡ ጥንቃቄ ሊያደርግ ይገባል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- ጥራቱና ፈዋሽነቱ ተረጋግጦ ለገበያ የቀረበ ባህላዊ መድኃኒት ባለመኖሩ ኅብረተሰቡ ጥንቃቄ ሊያደርግ እንደሚገባ የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን አስታወቀ፡፡

በባለሥልጣኑ የመድኃኒት ምዝገባና ፈቃድ ዳይሬክተር አቶ ሀብታሙ በየነ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በማህበራዊ ሚዲያ ሃሰተኛ መረጃ የሚያሰራጩ ቢበራከቱም ጥራቱ ተረጋግጦና ሕጋዊ ፈቃድ ተሰጥቶት ለገበያ የቀረበ ባህላዊ መድኃኒት የለም፡፡ በመሆኑም ኅብረተሰቡ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት።

በኢትዮጵያ የባህላዊ መድኃኒት አዋቂዎች በየአካባቢያቸው ከሚቀምሙት መድኃኒት በሳይንሳዊ መንገድ ተረጋግጦና ተመርቶ ለገበያ የዋለ መድኃኒት የለም ብለዋል፡፡

ባለሥልጣኑ ባህላዊም ሆነ ዘመናዊ መድኃኒቶች ተመዝግበው ገበያ ላይ እንዲውሉና ሕዝብ ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ እየሠራ ነው ያሉት አቶ ሀብታሙ፤ በአሁኑ ወቅት ባህላዊ መድኃኒት ላይ የተሰማሩ ሰዎች የሚቀምሙት መድኃኒት በባለሥልጣኑ ተመዝግቦ ወደ ገበያ እንዲገቡ ጥረት እየተደረገ መሆኑን ጠቁመዋል።

የትኛውም መድኃኒት ወደ ገበያ ከመቅረቡ በፊት በትክክለኛው የሕክምና ሰውና በመሳሪያ መፈተሽ እንዳለበት አመላክተው፤ የንጥረ ነገሮቹ ይዘት፣ ለየትኛው በሽታ ፈዋሽ እንደሆነና የጎንዮሽ ጉዳቱ በላብራቶሪ ፍተሻ መረጋገጥ እንዳለበት አስረድተዋል፡፡

አብዛኛው ባህላዊ መድኃኒት በኢትዮጵያ የሚገኙ የባህል መድኃኒት አዋቂዎች የመጀመሪያው የመድኃኒት የዝግጅት ደረጃ በሆነው ተክሎችንና የተለያዩ ግብዓቶችን በማድረቅ፣ በዱቄትና በሚበጠበጥ መልኩ እንደሚያዘጋጁ ጠቅሰው፤ ወደ ተሻለው በክኒንና ፈሳሽ መልክ የማዘጋጀት ደረጃ ላይ አለመድረሳቸውን ገልጸዋል፡፡

በርካታ ባህላዊ መድኃኒቶች በምርምር ደረጃ ላይ መሆናቸውን አመላክተው፤ ጥናትና ምርምር የተደረገባቸው መድኃኒቶች ወደ ምርት የመቀየር ሥራዎች እየተጠበቁ መሆናቸውን አመላክተዋል፡፡

ባህላዊ መድኃኒት አዋቂዎች የቀመሟቸውን መድኃኒቶች ደህንነት፣ ፈዋሽነትና ጥራት ማረጋገጥ እንደሚገባ በተለያዩ መድረኮች ላይ ግንዛቤ በመፍጠር ወደ ሥርዓቱ እንዲገቡ ጥረት በመደረግ ላይ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የባህል መድኃኒት አዋቂዎቹን የመደገፍ፣ የሳይንሳዊ ሂደቱን የማሳየት ሥራዎች ላይ መሆኑን በመግለጽ፤ ሕጋዊ ፈቃድ ሳይኖራቸው የሚሰሩ አካላት ከድርጊታቸው ሊቆጠቡ እንደሚገባም አሳስበዋል።

በሌሎች ሀገራት ባህላዊ መድኃኒቶች በምርምር ተደግፈው በኪኒንና ፈሳሽነት መልክ ተዘጋጅተው ለገበያ እንደሚቀርቡ ጠቅሰው፤ መሰል ውጤቶችን በኢትዮጵያም ተግባራዊ ለማድረግ እየተሰራ መሆኑን አስገንዝበዋል።

በሀገሪቱ ባህላዊ መድኃኒት በምርምር ተቋማት አማካኝነት የመድኃኒት ዝግጅት ሂደትን አልፈው ገበያ ላይ ማዋል የሚችልበትን ደረጃ በማስፈት ጉዳታቸውን ማስቀረት ይቻላል ብለዋል።

ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ባህላዊ መድኃኒቶች በምርምር ታግዘው ወደ ገበያ እንዲወጡ የሚረዱ መመሪያ፣ ፖሊሲና ሕጎችን በማዘጋጀት ተግባራዊ እንደሚያደርግ ነው የገለጹት፡፡

ዜና



አቶ ገዛኸኝ አባተ

# በቱሪዝምና ሆቴል ዘርፎች ከሁለት ሺህ 500 በላይ ወጣቶች እየሰለጠኑ ነው

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- በቱሪዝምና ሆቴል ዘርፎች ዋነኛ ተዋናይ የሚሆኑ በመደበኛ የትምህርት መርሀ-ግብር ከሁለት ሺህ 500 በላይ ወጣቶችን እያሰለጠነ መሆኑን የሆቴልና ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት አስታወቀ፡፡

የኢንስቲትዩቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ገዛኸኝ አባተ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በፈጣን ዕድገት ላይ የሚገኘውን የኢትዮጵያ የሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ የሚደግፉ ብቁ ሙያተኞችን የማፍራት ሥራ እየተሠራ ነው፡፡

ኢንስቲትዩቱ በዲግሪ ፕሮግራም በሆቴልና ቱሪዝም አስተዳደር በቀን፣ በማታ፣ በቅዳሜና እሁድ መርሀ ግብሮች በዓመት ከሁለት ሺህ 500 በላይ ሰልጣኞችን ተቀብሎ እያሰለጠነ ነው ብለዋል፡፡

በአስጎብኝነት፣ በመስተንግዶና በንጽህና አጠባበቅና በምግብ ዝግጅት በደረጃ አራትና አምስት እንዲሁም በተለያዩ መስኮች አጫጭር ስልጠናዎችንም በመስጠት ላይ ይገኛል ሲሉ አመላክተዋል፡፡

የሥራ ዕድል የሚፈጠርበት ትልቅ ዘርፍ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ይህንን ፈጣን እድገት የሚደግፍ የሰው ኃይል አስፈላጊ በመሆኑ ኢንስቲትዩቱ በሆቴል፣ በቱሪዝምና በልዩ ልዩ ዘርፎች ሙያተኞችን ከማብቃት በተጨማሪ በዘርፉ ላይ የሚታዩ ክፍተቶችን ለመሙላት የማማከር፣ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን እየሠራ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

የቱሪዝም እንቅስቃሴው በመንግሥት ደረጃ ልዩ ትኩረት ተሰቶት እየተሰራበት በመሆኑ ኢትዮጵያ ያሉባትን ጫናዎች በመቋቋም የተለያዩ የቱሪስት መዳረሻ ልማቶች እያስፋፋች ትገኛለች፡፡

በተጨማሪም ሙያተኞች ከተለያዩ ሀገራት የሚመጡ ዜጎች ጋር ተግባብተው ሥራቸውን ማከናወን እንዲችሉ የእንግሊዝኛ፣ ጀርመንኛ፣ ፈረንሳይኛና ሌሎች ቋንቋዎችንም ጭምር የማስተማር ሥራ እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

የተሻለ የሰው ኃይል ማፍራት የሚቻልበትን አሠራር በመከተል በቱሪዝም መዳረሻዎች ላይ ለሚገኙ የሆቴል፣ የአስጎብኚ ማህበራትና ሌሎች በዘርፉ የተሰማሩ ሙያተኞች ያላቸውን ክፍተት በመለየት የሥራ ላይ ስልጠናዎች እየተሰጡ እንደሆነ አንስተዋል፡፡

አገልግሎት ሰጭ ተቋማትም በሚጠይቁበት ወቅት ስልጠናዎችን በመስጠት ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ የሚነሱ ችግሮች እንዲፈቱ ዘርፈ ብዙ ፕሮግራሞችን ይዞ የሚንቀሳቀስ ተቋም ነው ብለዋል፡፡

አዳዲስ የለሙ የቱሪዝም መዳረሻ የሆኑት የኮይሻ፣ ወንጭ፣ ጎርጎራና የህዳሴው ግድብ ፕሮጀክቶች፤ እንዲሁም በአዲስ አበባና በሌሎች አካባቢዎች እየተሠሩ የሚገኙ ፕሮጀክቶች ያላቸውን አቅም በጥናት በመለየት ለመሥራት ጥረት እየተደረገ መሆኑን አቶ ገዛኸኝ ተናግረዋል፡፡

አሁን ባለው ወቅታዊ ሀገራዊ ሁኔታ በሚፈለገው ልክ ስልጠናዎች ባይሰጡም፤ በኮይሻና ጎርጎራ አካባቢ በሚገኘው የቴክኒክና ሙያ ተቋማት ጋር በጋራ በመሆን አጫጭር ሥልጠናዎችን በመስጠት ዝግጁ እንዲሆኑ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

ኢንስቲትዩቱ የሚሰጣቸውን ስልጠናዎች ለማሳደግ የመሰረተ ልማት ግንባታ በማከናወን፤ ገበያው የሚፈልገውን አዲስ የሙያ ዘርፍ ምን እንደሆነ ጥናቶችን በማድረግ ካሪኩለም ቀርጾ የተለያዩ ስልጠናዎችን እየሰጠ እንደሆነ አንስተዋል፡፡

የገበያውን ፍላጎት የሚመጥኑ ሙያተኞችን በሀገር ውስጥ በማብቃት ከሌሎች ሀገራት የሚመጣበትን ሁኔታ ለማስቀረት በልዩ ትኩረት እየሠራበት መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ኢንስቲትዩቱ እንደ ስሙና ቆይታው በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፉ የራሱን አስተዋጽኦ ለማበርከት እየተንቀሳቀሰ እንዳለና መንግሥትም ትኩረት ሰጥቶ እያደራጀ መሆኑንም አቶ ገዛኸኝ ጠቁመዋል፡፡

በሀገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆኑ ሙያተኞችን በማፍራት የልህቀት ማዕከል እንዲሆን እየተሠራ ነውም ብለዋል፡፡

## ሀገሪቱ ወደብ አልባ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ኢትዮጵያ በፍትሃዊ መንገድ የጠየቀችው የባህር በር ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ የመጣውን የዋጋ ንረት ከመቅረፍ ባለፈ ዘላቂ ልማትን ለማረጋገጥ አስቻይ ሁኔታን እንደሚፈጥርም ዶክተር መኮንን ገልጸዋል፡፡

እንደ መኮንን (ዶ/ር) ገለጻ፤ የወደብ ተጠቃሚ መሆን በቀጣይ ጊዜያት እየጨመረ የመጣውን የኑሮ ውድነት በዘላቂነት ለመፍታት ተስፋ ሰጪ በመሆኑ ጥያቄ ውስጥ የሚገባ ጉዳይ አይደለም፡፡

ኢትዮጵያ በግብርና ዘርፍ ላይ በስፋት የተሰማራች ከመሆኗ ጋር ተያይዞ እንደ ማዳበሪያና መሰል ግበዓቶችን ለገበሬው በወቅቱ ለማድረስ አዳጋች እየሆነ መምጣቱ በምርታማነት ላይ ጉዳት ከማድረሱ በዘለለ የዋጋ ንረቱንም እንደሚያባብስ ዶክተር መኮንን ጠቁመዋል፡፡

ወደብ ተከራይ መሆን የሚፈለገውን ያክልና በሚፈለገው መጠን ምርቶች ወደሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ከማድረግም በተጨማሪ ለኪራይ የሚከፈለው ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ወደ ኢኮኖሚው ቢገባ ለሀገራዊ እድገት የሚኖረው አስተዋጽኦ ትልቅ እንደሆነም ዶክተር መኮንን ጠቁመዋል፡፡

ወደብ አልባነት ሌሎች የኢንቨስትመንትና የድህነት ቅነሳ ሥራዎች ላይ መዋል የሚችለው የሀገሪቱ ሀብት ለወደብ ኪራይ እየዋለ የኑሮ ውድነቱ እንዲባባስ አስተዋጽኦ እያደረገ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

ይህም በተዘዋዋሪ ከውጭ የሚገቡ ምርቶች ላይ የዋጋ ጭማሪን በማስከተል ላይ እንደሚገኝም አያይዘው ገልጸዋል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ ምርቶች ወደውጭ ሲላኩ የወደብ ኪራይ በምርት ሽያጩ ላይ በሚጨመርበት ወቅት የኢትዮጵያ ምርቶች በዓለም አቀፍ ገበያ ላይ ተወዳዳሪ እንዳይሆኑ ጫና እያሳደረ መሆኑን አውስተዋል፡፡

የጎረቤት ሀገራት ኢትዮጵያ ያቀረበችውን የሰጥቶ መቀበል መርህ ተቀብለው የራሳቸውን ተጠቃሚነት ሊያረጋግጡ እንደሚገባም ዶክተር መኮንን ተናግረዋል፡፡

በዚህም ሀገራት በጋራ መስራትና መልማት ሲጀምሩ ከኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው በተጨማሪ ለቀጣናው የፖለቲካ መረጋጋትን ያመጣል ብለዋል፡፡

አክለውም በሀገራት መካከል ሀብትን በጋራ መጠቀምና አብሮ መሥራት ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ እሴቶች ያሉት በመሆኑ በቀላሉ ተያይዞ ለማደግ መልካም አጋጣሚ የሚፈጥር መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የኢትዮጵያ ወደብ ተጠቃሚ መሆን ቀጥተኛ የውጭ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ ምቹ አጋጣሚን የሚፈጥር እንደሆነም አስረድተዋል፡፡

ኢንቨስተሮች የማምረቻ ግብዓቶችን በቀላሉ ወደሀገር ውስጥ እንዲያስገቡ በማድረግ የማምረት አቅማቸውን በሚያሳድጉበት ወቅት ምርቶቻቸውን ተመጣጣኝ በሆነ ዋጋ ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ እንዲያቀርቡ ያግዛል ብለዋል፡፡

በኢትዮጵያ አነስተኛ የቢዝነስ ኢንተርፕራይዞች በስፋት የሚገኙ በመሆናቸው ምርታማነታቸውን በማሳደግ ለሀገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን ለውጭ ገበያም ማቅረብ እንዲችሉ የሚፈለግ በመሆኑ በተመጣጣኝ ዋጋ ግብዓት ከውጭ አስገብቶ ለመስራት ምቹ አጋጣሚን እንደሚፈጥር መምህሩ አመላክተዋል፡፡

እንደ ኢትዮጵያ ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ያላትና አብዛኛውን የምግብና የማምረቻ መሳሪያዎችን ከውጭ ለምታስገባ ሀገር የወደብ ተጠቃሚ መሆን ጊዜ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ መሆን እንደሌለበትም አንስተዋል፡፡

የተጀመረው እንቅስቃሴ ምንም እንኳን ረጅም ጊዜ የሚፈጅ ቢሆንም ከግብ እንዲደርስ በፖለቲካም፣ በኢኮኖሚና በሌሎች ዘርፎች ላይ የሚገኙ ባለድርሻ አካላት ተሳትፈውበት የተሻሉ አማራጮችን በማምጣት የኢትዮጵያ ወደብ የማግኘት ተስፋዋ እውን ሊሆን ይገባል ብለዋል፡፡

## "ስንቀራረብ ወደ ኋላ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ትናንት ተካሂዷል፡፡

ከንቲባ አዳነች አቤቤ በወቅቱ እንደተናገሩት፤ የብሔር ብሔረሰቦች ቀን ላለፉት ዓመታት ሲከበር ቆይቷል፡፡ ከለውጡ ወዲህ የጎደሉትን በመሙላት ብዝሃነትን ማዕከል ባደረገ መልኩ የተለያዩ ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡

የብዝሃ ባሕል፣ ቋንቋ እና እሴት ባለቤት የሆነችው ኢትዮጵያ በብርቱ ልጆቿ ወደ ብልፅግናዋ እየገሰገሰች መሆኑን በመረዳት በጋራ መሥራትንና መተባበርን ማጎልበት ይገባል ያሉት ከንቲባዋ፤ ስንቀራረብ መተዋወቅ ብቻ ሳይሆን ወደ ኋላ የሚጎትቱንን ችግሮች ማሸነፍ የሚቻልበት እድል የሚገኝበት መሆኑን መረዳት ይገባል ብለዋል፡፡

ብዝሃነት በኢትዮጵያ ነባራዊ ሀቅ በመሆኑን ከሀገራዊ አንድነት ሳይነጠል እንደ እድል ልንወስደው ይገባልም ነው ያሉት፡፡

ከለውጡ በኋላ እርስ በእርስ የሚያቀራርቡና የሚያስተሳስሩ በርካታ ሥራዎች ተሠርተዋል ያሉት ከንቲባ አዳነች፤ ይህ የተደረገው ህብረ ብሔራዊ አንድነት ለጋራ ውጤት፣ ስኬትና ብልፅግና ቁልፍ መሰረት መሆኑንን በመረዳት እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

የበዓሉ መከበር እርስ በእርስ ያቀራርባል፣ እሴቶችን ያዳብራል እንዲሁም እድገትን እንደሚያፋጥን ከንቲባዋ ጠቁመዋል፡፡

"ብዝሃነት ነባራዊ ሀቅ፣ መዋቢያችን፣ መድመቂያችን መሆኑን ተገንዝበን ከሀገራዊ አንድነታችን ጋር አስተሳስረን የበለጸገች ኢትዮጵያ እውን ማድረጋችንን እንቀጥላለን" ብለዋል፡፡

ይህን ለማጠናከር በአንድ ግቢ ውስጥ የሁሉንም ብሔር ብሔረሰቦችን ሊወክል የሚችል የባሕል ማዕከል እንዲገነባ ከተማ አስተዳደሩ ወስኖ ወደ ሥራ መግባቱን ጠቅሰው፤ የሚገነባው ማዕከል ለከተማዋ ተጨማሪ የቱሪስት መስህብ ከመሆኑም በላይ በብዝሃነት ውስጥ ያለው አንድነት እንዲጎለብት ዕድል እንደሚፈጥርም ገልጸዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ወይዘሮ ቡዜና አልቃድር በበኩላቸው፤ የሶማሌ ክልል በሀገር አቀፍ ደረጃ የብሔር ብሔረሰቦችን ቀን ያዘጋጅ እንጂ በዓሉ በሁሉም ክልሎችና በሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች በድምቀት እየተከበረ ይገኛል፡፡

በተመሳሳይ የአዲስ አበባን ህብረ ብሔራዊነት በሚመጥን መልኩ የብሔር ብሔረሰቦች ቀን እየተከበረ ይገኛል ብለዋል፡፡

በዓሉንም ምክንያት በማድረግ በከተማዋ ወረዳዎችና በክፍለ ከተሞች የፓናል ውይይት የተካሄደ ሲሆን በመድረኩም ሕገመንግሥትና ፌዴራሊዝም ለህብረ ብሔራዊ አንድነት፣ የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን የማክበር አስፈላጊነት እና አንድነትን የሚሸረሽሩ ጉዳዮችን በሚመለከት እንደተከናወነ ገልጸዋል፡፡

በፌስቲቫሉ የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ፣ የአማራ ክልል ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ፋንቱ ተስፋዬ፣ የአዲስ አበባ ባህል፣ ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ሂሩት ካሳው፣ የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ወይዘሮ ቡዜና አልቃድር እና የክልል አፈ ጉባኤዎች ተገኝተዋል፡፡

ዘንድሮ 18ኛውን የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቀን "ብዝሃነትና እኩልነት ለሀገራዊ አንድነት" በሚል መሪ ቃል ኅዳር 29 በሶማሌ ክልል ጅግጅጋ ከተማ ይከበራል፡፡

## ሀገራዊ ምክክሩ በተፎካካሪ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ተግባራትን አከናውኖ ይቁም ብሔራዊ ምክክሩ እጅግ አስፈላጊ የሆነ ነገር ነው" ሲሉ ያስረዳሉ፡፡

ምክክሩ እንዲሳካ የኢትዮጵያ ጉዳይ ይመለከተኛል፤ ያገባኛል የሚሉ ሁሉ ድጋፍ እንዲያደርጉም ጠይቀዋል፡፡

አያይዘውም፤ ብሔራዊ ምክክርን የመሰለ ሥራ ለመሥራት በሀገር አቀፍ ደረጃ ታች ድረስ ወደ ህዝቡ ሄዶ ለምክክሩ አስፈላጊ የሆነውን መዋቅር መዘርጋት ቀላል እንዳልሆነ ጠቁመው፤ "የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ በአካል ለመንቀሳቀስ አስቸጋሪ ከመሆኑ አንጻር ኮሚሽኑ ያደረገው ጥረት ይበል የሚያሰኝ፤ እየተከተለ ያለው አቅጣጫም ትክክል ነው" ብለዋል፡፡

ኮሚሽኑ እስካሁን ባከናወናቸው ተግባራት ላይ ያላቸውን ግምገማ ሲገልጹ፤ "በአካሄዶች ዙሪያ በምሰራበት ተቋምም ኮሚሽኑን ለማገዝ እንሞክራለን፡፡ ኮሚሽነሮቹ ብዙ ጥረት እያደረጉ እንደሆነ በቅርብ አውቃለሁ" ያሉት ፕሮፌሰር በየነ፤ ኮሚሽኑ ሁኔታዎች በፈቀዱለት መጠን ተንቀሳቅሶ እየሰራ መሆኑን ጠቁመው፣ ሁኔታዎች ከሚፈቅዱት በላይ ብዙ መጠበቅ እንደማይገባም ተናግረዋል፡፡

አንድም ተፎካካሪ ፓርቲ ከምክክሩ መቅረት እንደማይገባው ባሳሰቡበት አስተያየታቸው፣ በፖለቲካ ፓርቲዎች ያጋራ ምክር ቤት ውይይት ተካሂዶ ከሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ጋር በጋራ መስራት አለብን የሚል አቋም መያዙን አውስተው፤ "የፖለቲካ ፓርቲዎች ብሔራዊ ምክክሩን በገምቢነት እያየን እንዲሳካ ጥረት እያደረግን መቀጠል ነው ያለብን" ብለዋል፡፡

በምክክር ካላመንን እና ተግባራዊ እንዲሆን ጥረት ካላደረግን ሌላ ችግር አለብን፡፡ በብሔራዊ ችግሮቻችን ላይ ተግባብተን ወደ ዘላቂ ሰላምና ልማት የሚያሸጋግር ጉዞ ላይ መግባት የሁላችንም ምኞት መሆን አለበት ሲሉም አክለዋል፡፡

የኢዜማ ምክትል መሪ ዮሐንስ መኮንን (አርክቴክት) በበኩላቸው፣ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ከመቋቋሙ በፊት ሀሳቦቻችንን አደራጅተን አማራጭ መንገድ ይሄ ነው ብለን ስናቀርብ ነበር ብለዋል፡፡

ሀገራዊ ምክክሩ ከተዋቀረ በኋላ ደግሞ አብረን እየሰራን እንገኛለን፡፡ እንደ ፓርቲ ዋና የትኩረት አቅጣጫችን በመሆኑ ሀገራዊ ምክክሩ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን የሚከታተልና የሚመራ ከፍተኛ ኤክስፐርቶችና ባለሙያዎች የተካተቱበት ኮሚቴ ሰይመን ወደ ሥራ ገብተናል ብለዋል፡፡

"ሀገራዊ ምክክሩ እንደጠበቅነውና እንደተመኘነው ባሰብነው ፍጥነት አለመሄዱ ቅር ይላል፡፡ መዘግየቱ በኮሚሽኑ የአሠራር ድክመት የመጣ ነው ማለት አይቻለም" ያሉት ምክትል መሪው፤ ሀገራችን የገባችበት የሰላም መደፍረስና የፖለቲካ ችግር ቅርቃር ሀገራዊ ምክክሩ ባሰብነው ፍጥነት እንዳይጓዝ እንዳደረገ ጠቁመው፣ አጠቃላይ ሂደቱ ግን ከሞላ ጎደል ጥሩ የሚባል እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

አርክቴክት ዮሐንስ እንደሚናገሩት፣ እርሳቸውን ጨምሮ የሰባት ፖለቲካ ፓርቲዎች አመራሮች በሌሎች ሀገሮች የተደረጉ የሀገራዊ ምክክር ልምዶችን ለማየት ዕድል አግኝተው፣ በሆላንድ ሀገር አንድ ሳምንት በወሰደ ትኩረቱን ሀገራዊ ምክክር ላይ ባደረገ ውይይት ላይ ተሳትፈዋል፡፡

በውይይት መድረኩ በሰሜን አየርላንድ ለ30 ዓመታት ለሁለት ተከፍለው የእርስ በርስ ጦርነት ሲያደርጉ ቆይተው በኋላ በብሔራዊ ምክክር ችግራቸውን የፈቱትን ተዋጊዎች ጭምር በአካል አግኝተው ትርፍና ኪሳራቸውን ገምግመው ሀገራዊ ምክክር የፈታላቸውን ችግር መመልከታቸውን ገልጸው፣ በቅርቡ በደቡብ አፍሪካ ተመሳሳይ የልምድ ልውውጥ እንደሚኖር ጠቁመዋል፡፡

አክለውም፤ በዓለማችን ላይ ከአንድ ሳምንት በላይ ዕድሜ ሳያስቆጥሩ በአጭሩ የተቀጩና ከ15 ዓመታት በላይ የወሰዱ 30 ያህል ሀገራዊ ምክክሮች መካሄዳቸውን፤ ነገር ግን ስኬታማ የሆኑት ግማሽ ያህሉ መሆናቸውን ገልጸው፤ "ዘግይተን ሀገራዊ ምክክር መጀመራችን ከሌሎች ስህተትና ውድቀት መማር የሚያስችል ልምድ ለመቀመር ይረዳናል" ብለዋል፡፡

"ሀገራዊ ምክክሩ አንዱን ጥሎ ሌላውን አንጠልጥሎ እንዳይካሄድ ጥረት እየተደረገ መሆኑን አውቃለሁ" ያሉት ምክትል መሪው፤ በምክክሩ አንሳተፍም ያሉ የፖለቲካ ኃይሎችም ቅሬታቸውን እየፈቱ ወደ ብሔራዊ ምክክሩ እንዲመጡ በተለየ ትኩረት መሥራትና ጥረት መደረግ እንዳለበት ጠቁመዋል፡፡

የኦሮሞ ነጻነት ግንባር (ኦነግ) ምክትል ሊቀመንበር አቶ ቀጀላ መርዳሳ በበኩላቸው፤ ሀገራዊ ምክክሩ ብዙ ደረጃዎችን አልፎ አሁን ወደ መጨረሻው ምዕራፍ አካባቢ እየደረሰ ይገኛል፡፡ እኛ እንደ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር (ኦነግ) በምክክሩ ለመሳተፍና ከኮሚሽኑ ጋር በትብብር ለመሥራት ዝግጁ መሆናችንን ስንገልጽ ቆይተናል፡፡ ከኮሚሽነሮቹ ጋር በየጊዜው እንደ ድርጅት በተናጠል እየተገናኘን ውይይቶች አካሂደናል ብለዋል፡፡

በተጨማሪም ኦሮሚያ ውስጥ እንደሚንቀሳቀሱ ፖለቲካ ድርጅቶች የኮሚሽኑ ሥራ እንዲሳለጥና ምክክሩ እንዲሳካ ለማድረግ በጋራ የምንሠራቸው ሥራዎች እንዳሉና ኮሚሽኑ የተቋቋመለትን አላማ በአግባቡ መወጣት እንዲችል እየተከታተሉ እገዛ እያደረጉ እንደሚገኙ ገልጸዋል፡፡

"ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ሥራውን በገለልተኝነት ታማኝነትና ቅንነት በተሞላበት መንገድ እየሠራ ነው ብለን እናምናለን" ያሉት ምክትል ሊቀመንበሩ፤ በሂደቱ ውስጥ አስቸጋሪ ሁኔታዎችና ውስብስብ ጉዳዮች ሊያጋጥሙ እንደሚችል ጠቁመው፤ እነዚያን ተጋግዞ በመወጣት ምክክሩን ማሳካት ይገባል ሲሉ አሳስበዋል፡፡

አብዛኞቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች በምክክሩ ለመሳተፍ ፍላጎት እንዳላቸው ማረጋገጫ መስጠታቸውን የጠቀሱት አቶ ቀጀላ፤ አንዳንዶች የተለያዩ ጥያቄዎችን ሲያቀርቡ ነበር፡፡ ከእነዚህ ቡድኖች ውስጥ ብዙዎቹ ወደ ምክክሩ መድረክ ለመምጣት ወስነዋል፡፡ ምናልባት አንድ ሁለት ቀርተው ሊሆን ይችላል፡፡ ለሀገራችን ሕመም መድኃኒቱ ውይይት ብቻ ነው ብለን ስለምናምን ከምክክር መድረኩ መራቁ አይጠቅምም ነው የምንለው ብለዋል፡፡

"እንደ ኦሮሞ ነጻነት ግንባር (ኦነግ) ሀገራዊ ምክክሩ አስፈላጊና ጠቃሚ ነው ብለን እናምናለን" ያሉት ምክትል ሊቀመንበሩ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ለብዙ ዓመታት ሲያወዛግቡ የነበሩ መሠረታዊ የሆኑ ጉዳዮችን ቁጭ ብሎ በመነጋገር በመግባባት በመፍታት አንድ ወጥ የሆነ ሃሳብ ላይ ይደረሳል ብለው ተስፋ እንደሚያደርጉ ተናግረዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ከዲፕሎማሲ ከፍታም በላይ የሆነው የሀገራት ጉብኝት!

አንድ ሀገር በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍ ብላ ከምትደምቅባቸው ጉዳዮች አንዱ በዲፕሎማሲ ዘርፍ የሚኖራት ተቀባይነትና ስኬት ነው። ይህ ተቀባይነት እንደ ሀገር ለመገንባት ለምትሻው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ሥርዓቶች ተቀባይነት የሚኖረው አስተዋጽኦ ከፍተኛ እንደሆነም ይታመናል።

በተለይም አዲስ የፖለቲካ ሥርዓት በመገንባት፤ በሕዝቦቻቸው ነገዎች ላይ ብርሃን ለመፈንጠቅ ጥረት በማድረግ ላይ ለሚገኙ ሀገራት በዲፕሎማሲው ዘርፍ የሚገኙ ስኬቶች በቀላሉ የማይገኙ፣ በብዙ መንገድ ስትራቴጂክ ሆኖ መንቀሳቀስን የሚጠይቁ ናቸው።

ዓለም በብዙ ፍላጎቶች በተወጣጠረችበት፤ እነዚህ ፍላጎቶች በተለያዩ ጎራዎች ዳግም እየከፋፈሉ ባሉበት በዚህ ዘመን ፤ የሀገርና የሕዝብን ዘላቂ ተጠቃሚነት ማጽናት የሚያስችል አቋም ይዞ፤ በመካከለኛው መንገድ፤ በመርህ መጓዝ ከዛሬ ተሻግሮ ነገዎችን ማየት የሚያስችል የአመራር ብስለትን የሚጠይቅ ነው።

በተለይም ራሳቸውን ሆነው በራሳቸው መንገድ እጣ ፈንታቸውን ለመቅረጽ ሌት ተቀን ለሚተጉ በማደግ ላይ ላሉ ሀገራት በዲፕሎማሲው መድረክ የሚያጋጥማቸው ተግዳሮት በቀላሉ የማይታይ፤ ነገዎቻቸውን ብቻ ሳይሆን ዛሬዎቻቸው ላይ ጭምር ዋጋ ሊያስከፍላቸው እንደሚችል ከትናንት ተሞክሮዎች መረዳት የሚከብድ አይደለም።

ሀገራችን ኢትዮጵያም ለዘመናት ካካበተቻቸው የዲፕሎማሲ ተሞክሮዎች በመነሳት፣ ለረጅም ዘመናት በዓለም ፖለቲካ ውስጥ ገለልተኛ አቋም በመያዝ፣ ሀገርና ሕዝብን ተጠቃሚ የሚያደርጉ የዲፕሎማሲ መንገዶችን ስትከተል ቆይታለች። በዚህም በዲፕሎማሲው መድረክ ያላት እውቅና ዘመናት ያስቆጠረ ነው።

በተለይም የለውጡ መንግሥት ወደ ስልጣን ከመጣ ማግስት ጀምሮ እንደ ሀገር ድህነትን ታሪክ ለማድረግ የጀመረውን እልህ አስጨራሽ ትግል በስኬት ለማጠናቀቅ ለዲፕሎማሲው ዘርፍ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ ሲንቀሳቀስ ቆይቷል፤ እየተንቀሳቀሰም ይገኛል።

በችግርም ሆነ በሰላም ወቅት የማይለዋወጥ፤ ወጥነት ያለው፤ ሀገርና ሕዝብን በዘላቂነት ተጠቃሚ ማድረግ የሚያስችል፣ ከሁሉም በላይ ለጀመርነው ድህነትን ታሪክ የማድረግ ትግል በሁለንተናዊ መልኩ አቅም መገንባት የሚያስችል የዲፕሎማሲ ስትራቴጂ ተነድፎ እየተሰራም ነው።

በዚህም ከለውጡ ማግስት ጀምሮ እየተመዘገቡ ያሉ ስኬቶች፤ ሀገር በሕልውና ስጋት ውስጥ በነበረችበት ወቅት ሳይቀር በተጨባጭ የታየና ሀገርን ከብዙ ውስብስብ ሴራዎች፤ ከዚያም ባለፈ ጠንካራ ኢኮኖሚ በመገንባት ሀገርና ሕዝብን ከከፋ ችግር መታደግ ያስቻለ ነው።

ገና በጠዋቱ ከኤርትራ ጋር የነበረውን በጦርነት የመፈላለግ ያልተቋጨ ታሪካዊ ክስተት በውይይት ወደ ሰላማዊ የታሪክ ምዕራፍ በመቀየር የተጀመረው አዲሱ ሀገራዊ የዲፕሎማሲ ጉዞ፤ በሀገራቱ ሕዝቦች መካከል እፎይታ በመፍጠር የቀደመው የወንድማማችነት መንፈስ እንዲታደስ አድርጓል።

ይህንን ተከትሎ ባለፉት አምስት ዓመታት የተከተልናቸው ሰጥቶ በመቀበል መርህ ላይ የተመሰረተ፤ ሀገርና ሕዝብን በየትኛውም መልኩ ተጠቃሚ የሚያደርግ የዲፕሎማሲ አቅጣጫ፤ በብዙ መልኩ ስኬታማ በመሆን በክፉ ቀናት ጭምር በጽናትና በእውነት ከአጠገባችን የሚቆሙ ወዳጆችን ማፍራት አስችሎናል።

በዚህም በግልጽም ይሁን በስውር እንደ ሀገር በዓለም አቀፍ ደረጃም ሆነ በሀገር ውስጥ ያጋጠሙንን፤ ሀገርን እንደሀገር የማፍረስ፤ የመበተን ሴራዎች መሻገር የሚያስችል ትልቅ ጉልበት እንድናገኝ ረድቶናል። ከዚያም ባለፈ ከተለያዩ ሀገራት ጋር የነበረንን ታሪካዊ ግንኙነቶች በማደስ፤ ሀገራቱ ጠንካራ የልማት አጋሮቻችን እንዲሆኑ ረድቶናል።

ሀገራቱ ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ድህነትን ታሪክ እናደርጋለን በሚል፣ ቁጭት በፈጠረው መነቃቃት ለጀመርነው እልህ አስጨራሽ ትግል ስኬት የሚጨበጥ አቅም የሚሆኑበትን አስቻይ ሁኔታ በመፍጠር፤ የቀደሙ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቶች ወደ ልማት አጋርነት የሚለወጡበትን ዕድል መፍጠር አስችሎናል።

በአጠቃላይ የለውጡ መንግሥት ወደ ሥልጣን ከመጣ ማግስት ጀምሮ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በአውሮፓ፣ በአሜሪካ፣ በኤሲያና በመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት ያደረጓቸው ጉብኝቶች ሀገሪቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ የዲፕሎማሲ ከፍታ እንድትቀዳጅ ትልቅ ጉልበት ሆነዋል።

እያንዳንዱን ጉብኝት ተከትሎ የሚደረጉ ትላልቅ የልማት ስምምነቶችም የዲፕሎማሲው ስኬቱ ትሩፋት በመሆን ፤ በተለያዩ መንገዶች ወደ ሀገር ውስጥ ከፍ ያለ ሀብት እንዲፈስ በማድረግ፤ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ የተለያዩ ጫናዎችን ተቋቁሞ ተከታታይ ዕድገቶችን እንዲያስመዘግብ እየረዳ ነው።

ሰሞኑን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ቼክ ሪፐብሊክን ጨምሮ በተለያዩ ሀገራት ያደረጓቸው ጉብኝቶችና ጉብኝቶቹን ተከትሎ የደረሱባቸው የተለያዩ የጋራ ስምምነቶች፤ የሀገራቱንና የዓለም አቀፍ ተቋማትን ግንኙነት ከማደስ ባለፈ፤ ለልማታችን አጋር በመሆን የተሻለ አስተዋጽኦ ማበርከት እንዲችሉ ሰፊ ዕድል የሚፈጥር በመሆኑ የሚበረታታና ዕውቅና ሊሰጠው የሚገባ ነው፤ ከፈጠረው የዲፕሎማሲ ከፍታም በላይ የሆነ ድል ነው!


## አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፦ 011 126 4200

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ኢትዮጵያ ታምርት እኛም እንሸምት

ምሕረት ሞገስ

አብዛኞቹ የዓለም ሸማቾች የሀገር ውስጥ ምርት የመሸመት ከፍተኛ ፍላጎት እንዳላቸው ጥናቶች ያመለክታሉ። ከእነዚህ መካከል የሀገር ውስጥ ምርትን በመሸመት ታዋቂ የሆኑት አውስትራላውያን ናቸው። የህንድ እና የጣሊያን ዜጎችም ከአውስትራሊያ ቀጥለው የሚጠቀሱ ሕዝቦች ናቸው።

ከአውስትራሊያ ሸማች ሕዝብ 74 በመቶ የሚሆኑት ሙሉ ለሙሉ ምርቶችን ከሀገር ውስጥ ካምፓኒ የመሸመት ፍላጎት አላቸው። ከህንዳውያን 72 በመቶ ፤ ከጣሊያናዊያን 69 በመቶ የሚሆኑ ደግሞ የሀገር ውስጥ ምርትን የሚሸምቱ ናቸው።

ይህ የሀገራቱ ሕዝቦች የሀገር ውስጥ ምርትን የመሸመት ፍላጎት መነሻው ፤ ከሀገር ፍቅር ስሜት እና በሀገራቸው ውስጥ እነርሱ የሚሸምቷቸውን ምርቶች የሚሠሩ ሠራተኞችን እና ቤተሰቦቻቸውን ለመርዳት፤ ለማበረታታት እና እንዲያድጉ ከማሰብ እንደሆነ በዘርፉ የተካሄዱ ጥናቶች ያመላክታሉ።

ወደ እኛ ሀገር ስንመጣ እውነታው የተገለቢጦሽ ነው። ኢትዮጵያ ከምታመርተው በላይ ወደ ሀገር ውስጥ የምታስገባቸው ምርቶች ከፍተኛ ናቸው። ይህም ሕዝቧ ከሀገር ውስጥ ምርት ይልቅ የውጭ ምርትን የመሸመት ሰፊ ዝንባሌ እንዳለው የሚጠቁም ስለመሆኑ ባለሙያዎች ይናገራሉ።

ዜጎች የራሳቸውን ሀገር ምርት መሸመታቸው የሀገር ውስጥ አምራቾችን እንደሚያበረታታ ለመገመት ብዙም የሚከብድ አይደለም። በአንድ ሀገር ውስጥ የሚመረተው ምርት በሀገር ውስጥ ገበያ ከሌለው የሚያድግበት ዕድል ውስን መሆኑም እንዲሁ የሚታወቅ ነው።

አንድ አዲስ ምርት በሀገር ውስጥ ገበያ ሽያጭ ቀስ በቀስ ማደግ ካልቻለ እና ምርቱን በጥራትም ሆነ በብዛት ካላሳደገ በዓለም ደረጃ የመታወቅ፣ ተወዳዳሪ ሆኖ ገበያ የማግኘት ዕድሉ አነስተኛ ስለመሆኑ ገበያ ላይ የተካሄዱ ጥናቶች ያመለክታሉ።

ይህ የሀገር ውስጥ ምርትን መግዛት እና የሀገር ውስጥ ካምፓኒዎችን የማበረታታት ጉዳይ ሲጠቀስ፤ ለብዙ የሀገር ውስጥ ካምፓኒዎች ውድቀት በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ መነሻው የካምፓኒው ክፍተት ብቻ ሳይሆን የሀገሩ ዜጎች አለመሸመትም በምክንያትነት ሊነሳ ይችላል።

በተለይ በአነስተኛ ደረጃ በማምረት ቀስ በቀስ ገቢ እያገኙ በሂደት ማደግን አስበው የሚነሱ አምራች ዜጎች፤ ምንም እንኳ ምርቱ ጠቃሚ ቢሆንም፤ የሀገር ውስጥ ምርትን የሚሸምት አለመኖሩ እና ሸማች ማጣታቸው ያመረቱት ምርት አገልግሎት ላይ እንዳይውል እና ታዋቂነትን እንዳያገኙ ያደርጋቸዋል።

የገበያ ሁኔታው አመቺ ካልሆነ እና ገዢ ከጠፋ እነርሱም አማራጭ ገበያን አግኝተው ከማደግ ይልቅ ሥራቸው ሙሉ ለሙሉ ተጎድቶ ለኪሣራ የሚጋለጡበት ሁኔታ መኖሩ እና ሥራቸውን አቋርጠው ሠራተኛ መበተናቸው የማይቀር ነው። ይህንን ታሳቢ በማድረግም የሀገር ውስጥ ምርት በመሸመት አምራቾች እንዲበረታቱ ብዙ ሥራ መሠራት እንዳለበት እየተነገረ ይገኛል።

በርግጥ የሀገር ውስጥ ምርትን የመግዛት ዝንባሌ አምራችን ብቻ ሳይሆን ዜጎችም በተለይ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ዜጎች፣ ምርቶችን በሚፈልጉት ዝቅተኛ ዋጋ እንዲያገኙ ይረዳቸዋል። በተለይ ለሸማች መሠረታዊ የሆኑ ምግብ፣ ልብስ ወይም ሌሎች ከመጠለያ ጋር የተገናኙ የቤት መሥሪያ ግብዓቶች እና የቤት ውስጥ የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎችን አግኝተው በቀላል ዋጋ እንዲገዙ እና እንዲጠቀሙ ይረዳቸዋል።

የሀገር ውስጥ ምርትን መሸመት ለዜጎች ወጪ የመቆጠብ እድልን የሚፈጥር ጭምር ነው፤ ይህ የሀገር ውስጥ ምርትን በመግዛት የተገኘው የቁጠባ ገንዘብ ለሌላ ዓላማ መዋሉም በራሱ ሸማቹ የሚያገኘው ሌላኛው ጥቅም ይሆናል። ከሸማች እና ከአምራች በተጨማሪ የሀገር ውስጥ ምርትን ገበያን ማስፋት ነጋዴዎችንም በእጅጉ የሚጠቅም ነው። ከሌሎች ሀገሮች ምርቶችን በመግዛት ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት የሚያወጡትን የመርከብም ሆነ የጉምሩክ እና ሌሎችም አጠቃላይ የትራንስፖርት ወጪዎችን ይቀንስላቸዋል።

በሀገር ውስጥ የሚመረተው ምርት ለመጓጓዣ የሚያስወጣው ወጪ አነስተኛ መሆን፤ ያለምንም የዓለም አቀፍ ነጋዴ የዋጋ ውድድር በቀላሉ ገዝቶ ማከፋፈል አስመጪ የነበረ እና ጅምላ ሻጭ ነጋዴውንም የሚያበረታታ እና በቀላሉ ከውጭ ከሚመጣው በቀነሰ ዋጋ እንዲያከፋፍሉ እና የተሻለ ገቢ እንዲያገኙ የሚያስችላቸው ነው።

ይህ የሀገር ውስጥ ምርትን መሸመት አምራች ዜጎችን ፤ ሸማቾችን እና አስመጪ ነጋዴዎችን ለመርዳት ብቻ ሳይሆን ሀገርንም በእጅጉ የሚጠቅም ስለመሆኑ አጠያያቂ አይደለም። በዓለም ደረጃ ብዙ ግለሰቦች የሀገራቸውን አምራች ሰዎች የማበረታታ ፍላጎት ያላቸው በመሆኑ፤ ለሀገራቸው ምርት ቅድሚያ በመሥጠታቸው ግለሰቦች ብቻ ሳይሆኑ ሀገራቸውም በከፍተኛ ደረጃ እየጠቀሙ ስለመሆኑም ይነገራል።

ሀገር እንድትጠቀም ከሚያስችሉ ምክንያቶች መካከል ዋነኛው የውጭ ምንዛሬን ማዳን ነው። ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ በመግባት ለገበያ የሚቀርቡት ምርቶች በውጭ ምንዛሬ የሚገቡ በመሆናቸው ያንን ለማዳን እና ሀገርን ከወጪ ለመታደግ ትልቅ መንገድ መሆኑም እየተጠቆመ ነው።

ዜጎችም ሆኑ ሀገራት የሚያገኙትን ጥቅም ታሳቢ በማድረግ፤ ሀገራት በተለያዩ መንገዶች ‹‹የሀገራችሁን ምርት ግዙ›› እያሉ ያበረታታሉ። የኢትዮጵያ ልማት ኢንተርፕራይዝም ከቀጣዩ ወር ከታኅሣሥ ጀምሮ ብዙዎች በሀገር ውስጥ የተሠሩ ምርቶችን መግዛት እንዳለባቸው ለማስታወስ እና ይህም ሁሉንም እንደሚጠቅም ለማስገንዘብ ‹‹ ኢትዮጵያ ታምርት እኛም እንሸምት ›› የሚል መሪ ሃሳብ በመያዝ ቅስቀሳ ለመጀመር መሰናዶ እያደረገ ይገኛል።

ነገር ግን እዚህ ጋር የሀገር ውስጥ ምርት ከመሸመት ጋር ተያይዘው የሚነሱ ጉዳዮች አሉ። አንደኛው ከጊዜ ወደ ጊዜ የምርት ጥራትን ማሳደግ ሲሆን፤ ሌላኛው ከውጭ ከሚገዛው ይልቅ በዝቅተኛ ዋጋ ሊሸመት የሚቻልበት ሁኔታን መመቻቸት ነው። ምርቱ ያለ ብዙ ውጣ ውረድ በቅርብ ርቀት እና ያለ ብዙ ጥበቃ በቀላሉ መገኘት እንደሚኖርበትም እየተነገረ ይገኛል።

ስለዚህ ሸማቾች የሀገር ውስጥ ምርትን መሸመት ላይ ሲያተኩሩ፤ አምራቾች ደግሞ በስፋት ጥራቱ የተጠበቀ ምርት ለማቅረብ ሲሠሩ፤ ነጋዴውም ከሌሎች ሀገሮች ምርቶችን በማስመጣት ላይ መጠመዱን ሲያቆም፤ አከፋፋይም ሆነ ጅምላ ሻጭ በሀገር ውስጥ የተመረተውን ምርት በስፋት በማሰራጨት በቀላሉ የአምራቾችን እና የራሱን ገቢ ያለ ብዙ ውጣ ውረድ የተሻለ ለማድረግ ሲጥር ሀገር ተጠቃሚ ትሆናለች።

ዜጎች ተጠቃሚ ሆነው ሀገር እንድታድግ ኢትዮጵያ ታምርት እኛም እንሸምት።

# ነፃ ሃሳብ

# መጪውን ጊዜ ብሩህ ለማድረግ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ሰው የህልሙ ፈጣሪ እንደሆነ በርካታ ጠቢባን ይናገራሉ። በዚያው ልክ ሰው የመከራው ፈጣሪም እንደሆነ የሚናገሩ ጥቂቶች አይደሉም። ሀገር በዜጎች ሃሳብ፣ በትውልድ የበጎነት ስንቅ እንደምትፈጠር ሁላችንንም የሚያግባባ የጋራ መረዳት አለ። በዚህ መረዳት ውስጥም ከዓለም የገዘፈች ኢትዮጵያ የምትባልን ሀገር ፈጥረን እናውቃለን።

ከትላንት መለስ ብለን አሁንን ስንቃኝ ግን ትግላችን እንደ በፊቱ ለአብሮነት ሳይሆን የብቻ ቤትን ለመሥራት የምንፈራገጥ ነው የሚመስለው። ደግሞም እውነት ነው ተንፈራግጠን ከአምና የተለዩ መልከ ውይብ ማንነትን ፈጥረናል። ይህ አሁናዊ መልካችን እየሆነ ነው።

አሁን አሁን የአብዛኛው ኢትዮጵያዊ የመጀመሪያው ጥያቄ እስከመቼ በሞትና ጦርነት ውስጥ እንኖራለን? መቼ ነው ከዚህ አዙሪት የምንወጣው? ለምንድነው ከንቱ ድካም የማይደክመን? የሚሉት እንደሚሆኑ በልበ ሙሉነት ለመናገር እደፍራለሁ። ለዚህ ደግሞ ዋነኛው ምክንያት እየከፈልነው ያለው ያልተገባ ዋጋ ነው።

የአንድ ሀገር ሕዝቦች ፈተና ካለመግባባትና ከእርስ በርስ ግጭቶች የሚነሱ ናቸው። ለዚህ ሃሳብ አጽንኦት ለመስጠት በሀገራችን የተነሱትን የዜጎች መፈናቀል፣ ስደት፣ ርሀብ፣ ተረጂነት፣ የኑሮ ውድነት፣ የስጋት እንቅስቃሴ፣ የጸጥታ ችግር ሌላም ሌላም መጥቀስ ይቻላል። እኒህ ማህበራዊ ፈተናዎች ባለመግባባትና ቁጭ ብሎ ባለመነጋገር ጉልበት/ጦርነት መር በሆነ አስተሳሰብ የተፈጠሩ ስለመሆናቸው የማይረዳ የለም።

በዚህ መንገድ እስካሁን የበላይነት በሚንጸባረቅበት የአሸናፊነት መንፈስ ውስጥ ያለንን ከማጣትና ከመጣል ባለፈ የተቀዳጀነው ድል የለም። ዛሬም ድረስ የትላንትና የከዛ ወዲያ የአፋችንን ፍሬ እየበላን ነው። "ሞትና ሕይወት በአፍህ ቃል/በምላስ ውስጥ እንደሆኑ ታላቁን መጽሐፍ ቅዱስ ጨምሮ የተለያዩ የእውቀት አፎች ይነግሩናል። ግን አውቀንና ተረድተን ራሳችንን ከስቃይ ትውልዱንም ከጥላቻ አልታደግነውም።

እስካሁን ያሸነፍንባቸውም ሆኑ የተሸነፍንባቸው የወንድማማቾች ግፈያዎች ዛሬ ላይ ማናችንም ከፊት አላቆሙንም። አቁመውናል? ስለእውነት እናገራለሁ አላቆሙንም። ይልቅ ማንም ያልከፈለውን የመከራና የስቃይ ዋጋ እያስከፈሉን ነው። አሁናዊ ስቃዮቻችን፣ አሁናዊ መለያየቶቻችን አሸናፊና ተሸናፊ በሌለው የእርስ በርስ ግጭቶችን የመጡ ናቸው።

ሀገርን መታደግ ሕዝብን መታደግ ነው። ሕዝብን መታደግ ደግሞ ትውልድን መታደግ ነው። እኒህ ሁሉ ልዩ መሳይ አንድ ዓይነት መልኮች ወደቀደመ ኢትዮጵያዊ መልክና ክብራቸው እንዲመለሱ ሄደን ሄደን የምንወድቅበት ሳይሆን ሄደን ሄደን የምንደርስበት የአብሮነት ምኩራብ ያስፈልገናል። ይሄ እንዲሆን ሀገር ባቀና የጨዋነትና የአንተ ትብስ ልማዳችን ተረከዝ እስከመያዝ በሚያደርስ የክብብር መንፈስ ውስጥ በመነጋገር ወጥተን የምንገባበት የእርቅና የተግባቦት እውቀት ያስፈልገናል።

እንዲህ ካልሆነ የምንደርስበት ሩቅ የለም። እንዲህ ካልሆነ የምንደርስበት ህልምና ራዕይ የለንም። ፍቅርና አንድነትን ባጎደለ ምኞትና ህልም ውስጥ የሚመጣ የተሀድሶ ለውጥ የለም። ሀገራዊም ሆኑ ግለሰባዊ ለውጦች በፍቅር ጀምረው በአንድነት የሚያበቁ ናቸው። ተለያይተንና ተራርቀን ንፋስ የገባባቸው ቀዳዳዎቻችን እንዲጠቡ የፍቅር አፎችና የእርቅ አንደበቶች ያሹናል። እንዴትም ብናስብ እንደ እኛ የተቀራረበ ሕዝብ የለም። የታሪኮቻችን መነሻና መድረሻ የአብሮነት ደማቅ ስምን የታከኩ ናቸው።

'ጊዜ የሰውን ልጅ አይቀይረውም'፤ ይሄን እውነት ለመረዳት ዝግ ማለት ግድ ይሆናል። በአሁኑ ሰዓት ዓለም በዚህ አስተሳሰብ ውስጥ ሁለት የተለያዩ ጽንፎችን የምታራምድ ናት። ሰው እንደተረዳው ነው። ማንነቱ፣ ታሪኩ፣ ሕይወቱ፣ ህልሙ ሳይቀር ይሄን እውነት ተደግፎ የቆመ ነው። ምን ለማለት ፈልጌ ነው.. በየትኛውም የሕይወት መንገድ ላይ በጽናትም ሆነ በእንግድጋዴ የምንራመደው በገባን ልክ ነው።

ብዙዎቻችን ዘመንን በተመለከተ ሁለት ዓይነት አረዳድ አለን። ‹ጊዜ የሰውን ልጅ ይቀይረዋል› የሚልና ‹የሰው ልጅ ጊዜን ይገዛዋል› የሚል። በምንም የሕይወት ደረጃ ላይ እንሁን ሁላችንም ከዚህ እውነት ጀርባ የቆምን ነን። ከሁሉም የሚልቀው እውነት ጊዜ በሰው ልጅ ቁጥጥር ስር ነው የሚለው ነው።

ይሄ እውነታ የገባቸው በጊዜ ውስጥ የሚቀይሩት ታሪክ፣ ማንነት፣ ባህል፣ ሥርዓት የላቸውም። ማንነታቸውን ተቀብለው ወደፊት የሚራመዱ እግረ ለሞች ናቸው። ይሄ እውነታ ያልገባቸው ግን ትላንትን እየናቁ ዛሬን የሚያደንቁ፣ ታሪክና ማንነታቸው ኋላቀር እየመሰላቸው ምንም ባላወቁትና ባልተረዱት የሚደናበሩ ናቸው።

ይሄን እውነት ወደእኛ ስናመጣው ብዙ የትዝብት አክርማን መምዘዝ እንችላለን። ዓለም በሌለው ክብርና ነጻነት ውስጥ የቆምን፣ የሰላምና የአብሮነት ደሴት ተብለን የተደነቅን ሕዝቦች ስለምን ዛሬ ሌላ ሆንን? ከኢትዮጵያዊነት ውጭ ሌላ የማናውቅ፣ ተጨማሪ ስምና መጠሪያ የሌለን ሕዝቦች ዛሬ ስለምን በማይረቡ እልፍ ስሞች ተከበብን?።

ተመካክሮ በጥቅምት እኩሌታ ወራኤሉ የከተመ፣ ተግባብቶና ተስማምቶ በአጋዴንና በካራማራ የቆመ ሕዝብ ስለምን ዛሬ ሰላም ራቀው? ባህር ማዶ ተሻግሮ ስለሌላው ሰላም የሞገተ፣ ስለሌላው ነጻነት የተከራከረ ሕዝብ ስለምን ሰላም ናፋቂ ወጣው? ሊቀ ነብያት ሙሴን ያበረቱ ዮቶራዊ አፎች፣ የግሪክ ጸሐፍቶች በድርሰቶቻቸው ያሞካሿት ኢትዮጵያ ስለምን ዛሬ ክብር ራቃት?።

"ኢትዮጵያዊ መልኩን ነብር ዝንጉርጉርነቱን" አይቀይርም ሲል አምላክ በቃሉ ያወሳት ምድር፣ "ኢትዮጵያ እጆቿን ወደእግዚአብሔር ትዘረጋለች" ሲል የእምነቷን አጽናፍ የመሰከረ ቅዱስ ቃል ያላት ሀገር አሁን ምን አገኛትና ከተመሰከረ ማንነቷ ጋር ተጋጨች? ስለሀገሬ ጥቂቱን ተናገርኩ እንጂ ጥንተ ብኩርናዋንና ገናናነቷን የሚናገሩ እልፍ የታሪክ ሰነዶች አሉ። ዛሬ ለምን፤ ስለምን ቀለልን? ስለምን ከክብራችን ተንሸራተትን?

ጥያቄዎቻችን ወደ አንድ አቅጣጫ ነው የሚመሩን..የጥንቱን ባህል ስለመሳት፣ መጤ በሆኑ አጉል አስተሳሰቦች ስለመወሰድ፤ የቱን ያህል በከፋ ራስ ወዳድነት እና ጽንፍ ረገጥ አስተሳሰብ መወሰዳችንን ነው የሚያሳብቁት። ታሪክ ማጣመምን፣ እውነትን መሸሸን ነው የሚነግሩን። በትርክት መሸመድመድን፣ በሀሰት መለያየትን ነው የሚጠቁሙን። ተነጋግሮ አለመግባባትን፣ ተወያይቶ አለመስማማትን ነው የሚነግሩን። ለፍቅርና ለይቅርታ የተዘጉ ልቦቻችንን ነው የሚያስታውሰን። ከባህልና ከሥርዓት ያፈነገጠ ጊዜ ወለድ ማንነታችንን ነው የሚያንጸባርቁብን።

እስከ መቼ አንቀላፍተን፣ እስከ መቼ የራሳችን ጠላቶች ሆነን እንዘልቀዋለን? የጦርነት ነጋሪት ስንጎስም፣ አታሞ ስንመታ እዚህ ደርሰናል። እስኪ ደግሞ በፍቅር ድካሞቻችንን እንርሳ። ተነጋግረንና ተፈቃቅደን ችግሮቻችንን ካልፈታን የጥንቱን አብሮነት የምንመልስበት ሌላ ሁነኛ መላ የለንም።

ከድካሞቻችን ለመበርታት ብቸኛው መዳኛችን እርቀ ሰላም ነው። በእርቅ ሰላም ማውረድ ለእኛ አዲስ ነገራችን አይደለም። ስናስታርቅና ስንመክር፣ ስንገስጽና ስናስተቃቅፍ የኖርን ለዘመናዊው ዓለም ፋና ወጊ የሆንን የሥርዓት ቀደምቶች ነን። ልባችንን በእልህና በክፋት ዘግተነው እንጂ ለዛውም ከወንድሞቻችን ጋር፣ ለዛውም አብሮ ከበላና አብሮ ከተዋለደ ሕዝባችን ጋር መተቃቀፍ አይከብደንም ነበር።

አሁን ላይ የሰላም መንገዶቻችንን የዘጉብን የኃይል አስተሳሰቦች ዘመን አመጣሽ ወይም ደግሞ ከዚህ የተሻለ ስም የሚሰጣቸው ናቸው። እንጂማ ማንና ምን እንደነበርን የምናውቅ ነን። ጥንተ መሠረታችን ፍቅርን አምጦ የወለደ ማህጸን፣ አንድነትን አቅፎ ያሳደገ ክንድ ነው። ጥንተ ማንነታችን አብሮነትን እሽሩሩ ያለ፣ ኢትዮጵያዊነትን ያስቀደመ ሃሳብ ነው። ዛሬ በጥላቻና በመለያየት ቆሽሸን የቆምነው አንደበቶቻችን እብለትን፣ እጆቻችን ግፍን፣ ልቦቻችን ጥላቻን ስለተለማመዱ ነው።

በጥላቻ የቆመ ትውልድ እንደ ሎጥ የክብር መንገድ የለውም። በመለያየት የቆመ ሕዝብ እንደ አብረሃም የበረከት ቤት የለውም። ሎጥ ከሰዶም ሲወጣ፣ አብረሃም ከካራን ሲጠራ በፍቅር ልብ በኩል ነው። እኛም የፍቅር ልብ ያስፈልገናል። ከድህነትና ከኋላቀርነት ብሎም ጦርነት እያስከፈለን ካለው አበሳ ለመራቅ ምክክርን እንደሁነኛ አማራጭ ልንቀበለው ግድ ይለናል።

ልዩነት ለምን ተፈጠረ ሳይሆን ልዩነትን እንዴት ማጥበብ እንዳለብን ማወቁ ነው የሚበጀን። ለውይይት ቢሮውን የከፈተ ባለሥልጣን፣ ለምክክር ፖለቲካውን ያዘጋጀ ፓርቲ ለሀገር ጥፋት የሚሆንበት ምንም ምክንያት የለም። ለእርቅና ለተግባቦት የተዘጋጀ ማህበረሰብ የልዩነት ድጦች አዳልጠው አይጥሉትም።

> ልዩነት ለምን ተፈጠረ ሳይሆን ልዩነትን እንዴት ማጥበብ እንዳለብን ማወቁ ነው የሚበጀን። ለውይይት ቢሮውን የከፈተ ባለሥልጣን፣ ለምክክር ፖለቲካውን ያዘጋጀ ፓርቲ ለሀገር ጥፋት የሚሆንበት ምንም ምክንያት የለም። ለእርቅና ለተግባቦት የተዘጋጀ ማህበረሰብ የልዩነት ድጦች አዳልጠው አይጥሉትም

የሩዋንዳና የደቡብ አፍሪካን የብሔራዊ ምክክር አውድ ስንቃኝ መነሻው የልዩነት ጽንፍ ሆኖ መድረሻው ደግሞ ሀገራዊ ውጥንቅጥ ነበር። በሄዱበት ሁሉን አካታች የምክክርና የውይይት ቅብብሎሽ ችግራቸውን ቀርፈው ሀገራቸውን ወደሰላማዊ ይዞታዋ መመለስ የቻሉበትን ሁኔታ ማስታወስ ይቻላል። በእኛም ሀገር ተመሳሳይ ነገር ስለመንጸባረቁ የኮሚሽኑ ዓመታትን የዘለቀ ዝግጅት ጥቁምታን የሚሰጥ ነው።

በሰፊ መድረክ፣ በሰፊ ተሳትፎ ሰፊዋን ሀገራችንን ከአስተሳሰብ ጥበት ለማውጣት እየተሰራ ያለው ሥራ የሚደነቅ ነው። በእንዲህ ዓይነቱ አካታችና አሳታፊ፣ ገለልተኛና ነጻ መድረክ ፊት ካልሆነ ወደ ሰላም የሚያስገባን ቀዳዳ እንደሌለም የሚታመን ነው። ለአንድነት በአንድነት ስንቆም ሰፍተን እንደምንገዝፍ ብዙ ያለፉ ታሪኮቻችን ምስክሮች አሉን። ከእኛ የማሰብና የመዋሃድ አቅም አንጻር ሲታዩ ችግሮቻችን እዚህ ግቡ የሚባሉ አይደሉም። የሰላም መንገዶቻችንን የዘጉብን እውቀት ማነስ ሳይሆን ለፍቅር አለመሸነፋችን ነበር።

ታሪክና እሴት፣ ወግና ልማድ የሳተ ፖለቲካ ለሀገር አይበጅም። በታላላቅ ባህልና ሥርዓት ውስጥ በቅለን ፍሬ አልባ ዛፍ የሆነው ርካብ በሳተ ርምጃችን ነው። ሀገር በመገንባት ሂደት ውስጥ ትልቁ ብቃታችን ሊሆን የሚገባው በምንም የማይሸራረፍ የአብሮነት መንፈስ ነው። ቀጣይ በሚኖረን የእርቅና የተግባቦት መድረክ ላይ እንዲህ ዓይነቱን መንፈስ በማራገብ ልዩነቶቻችንን ማጥበብ እንችላለን።

ሕይወት የአረዳድ መልክ ነው። እየኖርን ያለነው በተረዳንውና በገባን ልክ ነው። አረዳዳችንን ከኃይል ይልቅ ለሰላም፣ ከጥላቻ ይልቅ ለፍቅር እስካላስገዛን ድረስ ህልሞቻችን ፍሬ አይቋጥሩም። በአንዳንድ ትርክቶችና አንድነት ጠል ቡድኖች ከመነሻችን ሸሽተን ሌላነትን እየተለማመድን ነው። ከእውነታ የራቀ አረዳድ ትርክት ከማድመጥ ባለፈ ትርክት የማጥራት አቅም የለውም። በሀሰትና በማስመሰል እውቀት ጥራዝ ነጠቆች ሆነን ትውልዱን እየመረዝን ያለነው ባልገባን እውቀት ነው።

በወሬ ሳይሆን በተግባር፣ በትርክት ሳይሆን በታሪክ ሀገር እንፍጠር። በጥላቻ ሳይሆን በፍቅር፣ በመለያየት ሳይሆን በማበር ትውልድ እንታደግ። መጪውን ጊዜ ብሩህ የሚሆነው በዚህ ለሁላችንም በሚበቃና፤ ሁላችንን በሚበጅ እውነትና እምነት፣ ሃሳብና ተግባር ስንቃኘው ብቻ ነው።

# የአርሶ አደሩን ችግር ለመፍታት ታልሞ የተከናወነው የማዳበሪያ ግዢ

## የአፈር ማዳበሪያን ለአርሶ አደሩ በወቅቱ ለማቅረብ

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

አሁን ያለንበት ወቅት 2016/17 የመኸር ምርት የሚሰበሰብበትና አርሶ አደሩ ለቀጣይ ሥራ የሚዘጋጅበት ነው። ‹‹አንድ ክረምት የነቀለውን አስር ክረምት አይመልሰውም›› እንደሚባለው አርሶ አደር የክረምት ወቅት በረከቱን ሰብስቦ ጎተራውን ይሞላል። ከዚያም የቀጣዩን ሥራ ለማስጀመር ደፋ ቀና ይላል። እንደሚታወቀው አሁን ላይ በኢትዮጵያ የምርት ጊዜያት በርከት እያሉ መጥተዋል። ለወትሮው በዓመት አንድ ጊዜ ክረምት ተጠብቆ የሚሠራው የግብርና ሥራ ዛሬ በተለያዩ አካባቢዎች የበጋ መስኖ ተለምዷል።

በመኸር የተዘራው ሰብል ተሰብስቦ ሲያበቃ የሚቀጥለው የመስኖ ሥራ ነው። ይህ የመስኖ ሥራ ታዲያ በርካታ ግብዓቶችን ይፈልጋል። ከእነዚህም መካከል አርሶ አደሩ በብዙ ሲፈተንበት የቆየው የአፈር ማዳበሪያ ጉዳይ ነው። የአርሶ አደሩን የማዳበሪያ ጥያቄ ለመመለስ መንግሥት የተለያዩ ጥረቶችን ሲያደርግ እንደቆየ ይታወቃል። ይሁንና በተለያዩ ምክንያቶች የአፈር ማዳበሪያ ለአርሶ አደሩ ፈተና ሆኖ ቆይቷል።

ሀገራዊ እድገት እና ምጣኔ ሀብታዊው መሠረቱ በግብርና ትከሻ ላይ ለተመሠረተባቸው እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሀገራት የአርሶ አደሩን ፍላጎት አለማሟላት ጎን ለጎን በርካታ ችግሮችን የሚያስከትል ነው። አርሶ አደሩ ዛሬን እንደምንም ቢወጣው ነገ ሕዝቡ ላይ የሚፈጥረው ጫና ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም። በመሆኑም አርሶ አደሩ የሚያስፈልገውን የግብርና ግብዓቶች ለማሟላት ቀድሞ ማሰብ የግድ ይሆናል። ለዚህም ነው የአምናው ዘንድሮ እንዳይደገም በሚል ግብርና ሚኒስቴር ከወዲሁ የአፈር ማዳበሪያ ገዝቶ ወደ አርሶ አደሩ ለመድረስ ደፋ ቀና እያለ የሚገኘው።

ከሰሞኑ የግብርና ሚኒስቴር የአፈር ማዳበሪያን አስመልክቶ ለጋዜጠኞች መግለጫ ሰጥቷል። ይህም በኢትዮጵያ አንገብጋቢ የሆነውን የአፈር ማዳበሪያ ቀድሞ መግዛትን ይመለከታል። ምን ያህል ተገዛ፤ ምን ያህሉ ሀገር ውስጥ ገባ፤ ምን ያህሉ ጅቡቲ ወደብ ደረሰ የሚሉና መሰል ጉዳዮችን የገለጹት የግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ሶፊያ ካሳ (ዶክተር) ናቸው።

እርሳቸው እንዳሉት፤ የአፈር ማዳበሪያ ግዥ የሚፈጸመው በፌዴራል መንግሥት አማካኝነት ሲሆን፤ ሀገር ያላትን አቅም መነሻ በማድረግ ይከናወናል። በዚህም መሠረት ለ2016/17 የምርት ዘመን ከ23 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የአፈር ማዳበሪያ ለማቅረብ በእቅድ የተያዘ ቢሆንም በዘንድሮ የምርት ዘመን ሀገሪቷ ያላት የመግዛት አቅም 19 ነጥብ አራት ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ መሆኑ ታውቋል። ለዚህም 930 ሚሊዮን ዶላር ወጪን ጠይቋል። ከዚህ ውስጥም እስካሁን የ14 ነጥብ 79 ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ግዥ ተፈጽሟል።

በአርሶ አደሩ ዘንድ በጣም ተፈላጊ የሆኑ የማዳበሪያ ዓይነቶች ሁለቱ ናቸው። እነርሱም ኤን ፒ ኤስ እና ዩሪያ ሲሆኑ፤ እነዚህም አጠቃቀማቸው ግን ልዩነት አለው። ለአብነት እንደ ሀገር ባለው አጠቃቀም በዘር ወቅት የሚያገለግለውና የሚጠቀመው የአፈር ማዳበሪያ ኤን ፒ ኤስ / ኤን ፒ ኤስ ቦሮን/ ሲሆን፤ 60 በመቶውን ይይዛሉ። አርሶአደሩ ሰብሉ በቡቃያ ወቅት ሲደርስ የሚጠቀመው ዩሪያ ደግሞ 40 በመቶን የሚሸፍን ነው። ከ19 ነጥብ አራት ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ውስጥ ስምንት ነጥብ ሁለት ኩንታል የዩሪያ አፈር ማዳበሪያ ሲሆን ቀሪው 11 ነጥብ 19 ሚሊዮን ኩንታል ደግሞ ኤን ፒ ኤስ መሆኑን ያስረዳሉ።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታዋ ገለጻ፤ ባለፈው ዓመት ለትግራይ ክልል የተገዛውን የአፈር ማዳበሪያ ሳይጨመር 12 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ኩንታል ተገዝቷል። ከዚህ የዘንድሮው አንጻር ከፍተኛ ጭማሪ አለው። በዚህ ደግሞ የምርት ዘመኑን ኢትዮጵያ በታሪኳ ከፍተኛ የሆነ የማዳበሪያ ግዥ የፈጸመችበት ያደርገዋል። ከዚያም ባሻገር ይህ የምርት ዘመን የአፈር ማዳበሪያውን ፈጥኖ



**የግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ሶፊያ ካሳ (ዶክተር)**

በማስገባትም ጥሩ አፈጻጸም የታየበት ነው።

እሳቸው እንዳሉት፤ የመጀመሪያዋ መርከብ ታኅሣሥ 18 ቀን 2015 ዓ.ም የደረሰች ሲሆን፤ በዚህ ዓመት ደግሞ 51 ሺህ 420 ሜትሪክ ቶን ዩሪያ የጫነች የመጀመሪያዋ መርከብ በጥቅምት ወር ጅቡቲ ወደብ ላይ ደርሳለች።

ለ2016/17 የምርት ዘመን እስከ ኅዳር 19 ቀን 2016 ዓ.ም 207 ሺህ 295 ሜትሪክ ቶን የዩሪያ ማዳበሪያ ጅቡቲ ወደብ መድረሱንና ከዚህ ውስጥም 104 ሺህ 304 ሜትሪክ ቶን ዩሪያ ወደ ሀገር ውስጥ መጓጓዙን ያነሱት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ ከኅዳር 21 እስከ ታኅሣሥ 4 ቀን 2016 ዓ.ም ደግሞ 174 ሺህ 500 ሜትሪክ ቶን ኤን.ፒ.ኤስ ቦሮን የጫኑ ሶስት መርከቦች ወደ ጅቡቲ የሚደርሱ እንደሆነ በወቅቱ አስረድተዋል።

በተደጋጋሚ እንደተገለጸው የአፈር ማዳበሪያ ጉዳይ ለከፊል አርብቶ አደሩና አርሶ አደሩ ቀድሞ እንዲደርስ ከማድረግ አንጻር በርካታ ማሻሻያዎችን ማድረግ እንደቻሉ ያስረዱት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ ለዚህ ስኬት ደግሞ የተለያዩ ምክንያቶች እንዳሉት ጠቅሰዋል። ከእነዚህ ምክንያቶች መካከልም ቀድሞ የነበረውን የግዢ መመሪያ መቀየር፤ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን ቦርድ በአዲስ መልክ እንዲደራጅ ማድረግ እና የቴክኒክ ኮሚቴ እንዲቋቋም መሆኑ፣ የተለያዩ የግዢ አማራጮችን በመጠቀም ግዥ ማከናወንና የማዳበሪያ ዋጋ በሚቀንስበት ጊዜ ጠብቆ ግዢውን ማከናወን የሚሉት ዋና ዋናዎቹ መሆናቸውን ገልጸዋል።

በተጨማሪም እስካሁን ድረስ ሆኖ የማያውቀው 11 ኤልሲ መከፈቱ፤ ለመስኖ፤ ለበልግና ለመኸር አፈር ማዳበሪያ የሚያስፈልጋቸው አካባቢዎች የትኞቹ ናቸው ተብሎ መለየቱና ግዢ መፈጸሙ ደግሞ ስኬቱ ቀጣይነት እንዲኖረውና ማረጋገጫ የሚሰጥ እንዲሆን የሚያስችል እንደሆነ ነው የተናገሩት። አሁን ባለው የግዢ መጠን ትንሽ የሚቀረው ለመኸር የሚሆን ነው። ለዚህም ሰሞኑን የተወሰነ ግዢ የተፈጸመ ሲሆን፤ ቀሪውን ደግሞ የአፈር ማዳበሪያ ዋጋ የሚቀንስበት ወቅት እየታየ የሚገዛ መሆኑን ተናግረዋል።

እንደ ሚኒስቴር ዴኤታዋ ማብራሪያ፤ ግብርና ሚኒስቴር የሚቆጣጠረው ከጅቡቲ ተነስቶ እስከ ማዕከላዊ መጋዘን ያለውን የመጓጓዝ ሁኔታ ነው። መረጃ የሚሰጠውም ይህንን መሠረት አድርጎ ሲሆን፤ አርሶ አደሩ ጋር ባለፉት ሁለት ዓመታት በደረሰው ዋጋ እንዲደርስ በማሰብና ከምርት በኋላ የገበያው ዋጋ እንዳይጨምር ለማድረግ በመንግሥት በኩል የዋጋ ተመኑ ይወጣል። ያንን ተከትሎ አንዳንድ የትራንስፖርትና ጫኝ አውራጅ እንዲሁም የመጋዘን ኪራይ የመሳሰሉት በክልሉ ከደረሰ በኋላ በመጨመር ለአርሶ አደሩ የሚደርስ ይሆናል። ስለዚህም ዘንድሮ እንደ አምናው አርሶ አደሩ የዋጋ ጉዳይ አያሳስበውም። በአምናና በካቻምና ዋጋ የሚገዛበት እድል ተመቻችቶለታል።

በዚህ የምርት ዘመን በማዳበሪያ ግዢ ዙሪያ ቁጠባን ጭምር ያየንበት ነው። ምክንያቱም የማዳበሪያ ፍላጎታችንን ከፍ በማድረግ የመንግሥትን የድጎማ ጫና ቀንሰናል የሚሉት ሚኒስቴር ዴኤታዋ፤ ባለፈው ዓመት አንድ ቢሊዮን ዶላር ተሰጥቶን የትግራዩን ሳይጨምር 12 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ኩንታል መግዛት ተችሏል። በዘንድሮው ዓመት ግን 930 ሚሊዮን ዶላር ተፈቅዶልን እስከ 19 ነጥብ አራት ሚሊዮን ኩንታል ተገዝቷል። ለዚህ ደግሞ አዲስ የተቋቋመው የቴክኒክ ኮሚቴ ከአቅራቢዎች ጋር ከፍተኛ ድርድር አድርጎ ግዢው እንዲፈጸም አስችሏል። በሌላ በኩል የማዳበሪያ ዋጋ ከፍና ዝቅ የሚልበትን ጊዜ ጠብቆ መገዛቱ አዋጭ ሆኗል።

ሌላው ሚኒስቴር ዴኤታዋ ያነሱት ነገር ያልተገባ የማዳበሪያ ዝውውርና ልውውጥን ለማስቀረት የተሰራውን ሥራ ሲሆን፤ ይህም እንደ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ክትትል የሚደረግበትና የአፈር ማዳበሪያው ከጅቡቲ እስከ አርሶ አደር ድረስ መድረሱን የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ነው። ሥርዓቱ ሰርቋል አልሰረቀም የሚለውን ለማሳደድ ሳይሆን፤ ለአርሶ አደሩ ማዳበሪያው መድረሱን ዋስትና ለመስጠት መሆኑን ገልጸዋል። ለአብነት አምና የገጠመው ዋነኛ ችግር አማራ ክልል ላይ በሕገ ወጥ ሲዘዋወር የነበረው የአፈር ማዳበሪያ ሲያዝ ከኦሮሚያ ነኝ ይላል፤ ኦሮሚያ የተያዘውም አማራ ክልል ነኝ ይላል። ስለሆነም ተጠያቂ ለማድረግ አልተቻለም። አሁን ግን ከመነሻው ጀምሮ በኮድ ተይዞ የሚወጣ በመሆኑ ወጥቶ ቢሸጥ እንኳን የመያዝ እድል አለው ብለዋል። ሥርዓቱ ተጠያቂነትን ጭምር የሚያሰፍን በመሆኑ በዚህ ዓመት እውን ለማድረግ እየተሰራ ነው ብለዋል።

በዚሁ የምርት ዘመን ሌላም ተግባራዊ የሚደረግ ሥራ ስለመኖሩ የገለጹት ሚኒስቴር ዴኤታዋ፤ ይህም ከአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት ጋር ተያይዞ የሚከወነው ተግባር አዳዲስ ክልሎች ወደ ሥርዓቱ ማስገባትን ያለመ ነው። በመሆኑም ከግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን የአፈር ማዳበሪያን በግዢ የሚወስዱ ክልሎች ይኖራሉ። አንዱ ደግሞ አፋር ክልል ሲሆን፤ ከማዕከላዊ መጋዘን ግዢው በይፋ ይጀመርለታል። በሚቀጥለው ዓመት ደግሞ የጋምቤላና የሱማሌ ክልልን ወደ ግዢ ሥርዓቱ የማስገባት ሥራ ይከናወናል። ይህ መሆኑ ደግሞ ከማዕከላዊ መጋዘናቸው በቀላሉ የአፈር ማዳበሪያውን እንዲገዙና እንዲጠቀሙ ያስችላቸዋል ብለዋል።

የ2016/17 ምርት ዘመን የማዳበሪያ ሥርጭቱን በተመለከተ ከጸጥታ አኳያም ችግር እንዳይገጥምና ሥርጭቱ እንዳይስተጓጎል ከክልሎች ጋር በመነጋገር እየተሰራ መሆኑን ጠቅሰው፤ በእጀባ ጭምር ማዳበሪያ ወደ ክልሎች እየገባ እንደሆነ ገልጸዋል። የአፈር ማዳበሪያን በስፋት የሚወስዱ ክልሎችን በመጥቀስ ካለፈው ዓመት ጋር ያነጻጸሩት ሚኒስቴር ዴኤታዋ፤ ትግራይ ክልል ባለፈው ዓመት 800 ሺህ ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ የተገዛለት ሲሆን፤ በዘንድሮው ደግሞ 700 ሺህ የአፈር ማዳበሪያ ተገዝቶለታል። በተመሳሳይ ከፍተኛ ቁጥር ያለውን የአፈር ማዳበሪያ የሚጠቀሙት አማራና ኦሮሚያ ክልሎች ሲሆኑ፤ ኦሮሚያ ክልል ባለፈው ዓመት አምስት ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን ኩንታል የቀረበለት ሲሆን፤ በዚህ ዓመት ስምንት ነጥብ 92 ሚሊዮን ኩንታል የሚወስድ ይሆናል። ባለፈው ዓመት አምስት ነጥብ ሁለት ያገኘው አማራ ክልል ደግሞ በዚህ የምርት ዘመን ስምንት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ እንዲያገኝ ይደረጋል ነው ያሉት።

መንግሥት በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ የማዳበሪያ ዋጋ ጭማሪ ቢኖርም የአርሶና ከፊል አርብቶ አደሮችን አቅም ከግምት ውስጥ በማስገባት በየዓመቱ ያደረገውን ከፍተኛ ድጎማ ያነሱት ሚኒስቴር ዴኤታዋ፤ ባለፉት ሶስት ተከታታይ ዓመታት ያሉትን መረጃዎች ሲጠቅሱ መንግሥት የ52 ቢሊዮን ብር ድጎማ ማድረጉን ነው ያብራሩት። ይህም ማለት በ2014/ 15 የምርት ዘመን 15 ቢሊዮን ብር፤ በ2015/16 ምርት ዘመን 21 ቢሊዮን ብር እንዲሁም በ2016/17 ምርት ዘመን 16 ቢሊዮን ብር በድምሩ 52 ቢሊዮን ብር ድጎማ ተደርጓል። ይህ የሆነበት ምክንያት ደግሞ ገበያውን ከማረጋጋት አኳያ የማይተካ ሚና እንዳለው በመታመኑ ነው ብለዋል።

እነዚህ ተግባራት መከናወናቸው በርካታ ችግሮችን እንደሚፈቱ ያነሱት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ አንዱ እስከዛሬ እንደሆነው ሚያዝያና ሰኔ እንዲሁም ሌሎች ወቅቶች ላይ የሚዘራው አርሶ አደር እስከ ሰኔ እኩል ማዳበሪያ ፍለጋ እንዳይሰለፍ ያደርገዋል። ሌላኛው ደግሞ ከኮርፖሬሽኑ ማዳበሪያ በመውሰድ ችግሩ ወደ ገጠመበት ቦታ ለማድረስ መሯሯጥ አይኖርም። ከክልል ክልል ማዳበሪያ የማዘዋወር ሥራም አይከናወንም። በቀጥታ የሚያስፈልጋቸውን የአፈር ማዳበሪያ በጊዜው ከማከፋፈያ ማዕከላቸው እንዲያገኙ ይሆናሉ። ክልሎችም ሆኑ አርሶ አደሮች ይህንኑ አውቀው መንቀሳቀስ እንዳለባቸውም አሳስበዋል።

አዲስ ዘመን | ሰኞ ኅዳር 24 ቀን 2016 ዓ.ም



# ፍላጎትና ገበያ ያልተጣጣመበት የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና

**እዮሩስ ተስፋዬ**

በኢትዮጵያ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት እና ሥልጠና መስጠት የተጀመረው ከ1940ዎቹ አካባቢ ጀምሮ እንደሆነ መረጃዎች ያመላክታሉ። ተቋማቱ ከተከፈቱባቸው ከተሞች መካከል ደግሞ አዲስ አበባ በቀዳሚነት ትጠቀሳለች። ከዚህ ጋር ተያይዞም ተቋማቱ የገበያውን ፍላጎት መሠረት ያደረገ ሥልጠና እና ትምህርት መስጠት እንዳለባቸው ይነገራል። የሚሰጠው ሥልጠና ገበያው የሚፈልገው ወይም ገበያ መር ካልሆነ ብክነት እንደሆነም ይታመናል። ይህም ቀጣሪ የሚፈልገው እንዲሁም ራሱ ተቀጣሪው ግለሰብ ወጥቶ በሙያው ሥራ ቢጀምር ገበያ ሊያገኝ ይችላል ወይ? የሚለውን ጥያቄ ይመልሳል።

ሠልጣኞች የሚሰለጥኑት በሁለት መልኩ ሲሆን፤ አንደኛው ቀጣሪዎች ተቀጥረው እንዲሠሩ እና የራሳቸውን ሥራ እንዲፈጥሩ በሚያስችላቸው መልኩ ነው። ለመቀጠር የማያስችላቸውን ሥልጠና ብቻ ከወሰዱ ግን ትርፉ ብክነት ይሆናል። የሥራ አጡን ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ ያበዛዋል። በዚህም ሳቢያ ማኅበራዊ ቀውስ እንዲከሰት ከማድረግ ባለፈ፤ ሰዎች ወደ ወንጀል ሥራ እና ሀገርን ሊጎዱ ወደሚችሉ እንቅስቃሴዎች እንዲገቡ ይገፋፋቸዋል። መዋዕለ ነዋይም ይባክናል።

ይህንን ሁሉ ችግር ለመፍታት ነው የሚሰጠው ሥልጠና የግድ የገበያውን ፍላጎት መሠረት ያደረገ መሆን አለበት የሚባለው። ከዚህ አንጻር በአዲስ አበባ እየተሰጠ ያለው የትምህርት እና ሙያ ሥልጠና የገበያ ፍላጎትን መሠረት ያላደረገ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትምህርትና ሥልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለሥልጣን አስታውቋል። ባለሥልጣኑ በተለያዩ ምሁራን ባስጠናው ጥናት መሠረት በከተማዋ በአብዛኛው ገበያ ተኮር ፍላጎትን መሠረት ያደረገ የትምህርት እና ሥልጠና ሥርዓት መከተል እንዳለባት ቢታወቅም እየተሰጠ ያለው የትምህርት ሥልጠና ግን ክፍተት ያለበት ነው ተብሏል።

ባለሥልጣኑ «ጥናት እና ምርምር ለትምህርት እና ሥልጠና ጥራት» በሚል ርዕስ ባዘጋጀው የውይይት መድረክ ላይ ጥናቱን ያቀረቡት ዶክተር ገነነ አበበ እንዳሉት፤ በከተማዋ የሚሰጠው የቴክኒክ እና ሙያ ሥልጠና የገበያውን ፍላጎት የሚያሟላ አይደለም። የሙያ ደረጃ ሥርዓተ ትምህርቱ፣ የማሰልጠኛ መሳሪያዎች እና የመመዘኛ መሳሪያዎች በአብዛኛው የገበያውን ፍላጎት ሙሉ በሙሉ አያንፀባርቁም።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትምህርትና ሥልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለሥልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ዳኘው ገብሩ በበኩላቸው እንደሚናገሩት፣ መሥሪያ ቤቱ በአዋጅ ከተሰጠው ሥልጣን እና ኃላፊነት እንዲሁም ተግባራት መካከል ጥናት እና ምርምሮችን አድርጎ የባለሥልጣኑ ዋና የትኩረት አቅጣጫ የሆነውን የትምህርት ጥራትን ማረጋገጥ እንዲሁም «ሠልጣኖች ምን ያህል ደረጃውን የጠበቀ ትምህርት አግኝተዋል?» ብሎ ምዘና ማካሄድ እና ውጤታቸውን መስጠት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፤ ይህንኑ ተግባርም እያከናወነ ይገኛል።

ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ከትምህርት ቢሮ እና ከቴክኒክና ሙያ ቢሮዎች ጋር በቅርበት ይሰራል። ጉድለቶች እንዲሟሉ፤ በጥንካሬዎች ላይ ደግሞ መቀጠል እንደሚገባ አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ በዓመት አራት ጊዜ የጥናት እና ምርምር ሥራዎችን ያከናውናል። ከነዚህ መካከል በ2015 ዓ.ም የተጠናው ፍላጎት ተኮር የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና አንዱ መሆኑን ሥራ አስኪያጁ ያወሳሉ።

እንደ ሥራ አስኪያጁ ማብራሪያ በቴክኒክ እና ሙያ ተቋማት ውስጥ የሚሰጠው ሥልጠና ለሀገር ግንባታ ወሳኝ ነው። አብዛኛው ዜጋ የሚፈራው ከቴክኒክ እና ሙያ ተቋማት ነው። ተቋማቱ ተገቢው ትኩረት ካልተሰጣቸው የሀገር እድገት የሚታሰብ አይደለም። የሀገር እድገት እንዲያድግ ከተፈለገ ለሙያው ትኩረት መስጠትና ተማሪዎችን ማብቃት ይጠይቃል። ጥናቱ እንዳመላከተው ግን ብዙ መሰናክሎች እንዲሁም ብዙ ጉድለቶች እንዳሉ ነው። በአጭሩ የትምህርት ስብራት መኖሩን እና ስብራቱን ለመጠገን ደግሞ የቴክኒክን ሙያ ቢሮ ዋናው ሥራው ቢሆንም ከሌሎች ባለድርሻ አካላት በቅንጅት መሥራትን ይጠይቃል።

አቶ ታደለ አየለ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቴክኒክ እና ሙያ ሥልጠና ቢሮ የሥልጠና እና አካዳሚክ ጉዳዮች ዳይሬክተር ናቸው። እንደ እርሳቸው ገለፃ የቴክኒክና ሙያ ስትራቴጂ ገበያ መር እንዲሆን ያዛል። እንደ ቢሮም ክፍተቶችን ለመለየት በየሁለት ዓመቱ ጥናት



የጥናቱ አቅራቢ ገነነ አበበ (ዶክተር)፤



አቶ ዳኘው ገብሩ፤

> በአሁን ወቅት ከቴክኒክ እና ሙያ ሥልጠና ትምህርት ቤቶች የሚወጡትን መፈለግ ብሎም የመቅጠሩ ነገር ከዚህ ቀደም ከነበረው ጋር ሲነጻጸር መሻሻሎች ታይተውበታል

የሚያደርግ ሲሆን፤ በኢንደስትሪ አካባቢ ያሉ ችግሮች መቅረፍ እንዳለባቸው ይታመናል። ከቴክኒክ እና ሙያ ተቋማት የሚወጣው የተማረ ኃይል የኢንደስትሪውን አቅም ሊያሟላ እንደሚችል በማመን የቀረውን ጥናት በግብዓትነት ተጠቅሞ የማስተካከል ሥራ ይሠራል።

አቶ ዳኘው በበኩላቸው እንደሚናገሩት፣ ኢንዱስትሪዎች ይህንን ሥራ ለመንግሥት ብቻ ወይም ለአንድ ተቋም የመተው አዝማሚያ ይታይባቸዋል። በተግባር ልምምድ ላይ ከፍተኛ እንቅፋት የሚፈጥሩ ሲሆን፤ በጋራ ተግባብቶ መሥራት ያስፈልጋል። አንዳንድ ተማሪዎች ፍላጎት ላይ መሠረት ያደረገ ሥልጠና ለመውሰድ ፈቃደኛ ሲሆኑ አይስተዋልም ወይም ፍላጎቱ የላቸውም። ተማሪዎቹ በሀገር እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንደሆኑ የጥናቱ ግኝትን እና ምክረ ሃሳቦችን በማጤን መሥራት ያስፈልጋል።

ከብቃት ምዘና ጋር በተያያዘ በመዲናዋ በተአማኒነትና ብልሹ አሠራር በኩል መሻሻሎች መኖራቸውን ዶክተር ገነነ ተናግረው የተሻሻለ ነገር የታየ ቢሆንም አሁንም የበለጠ መሠራት እንዳለበት ይጠቁማሉ። ከሴቶች ተሳትፎ አንጻርም በሚገባ አበረታች ሥራ መሠራቱንና የተለየ ፍላጎት ላላቸው ለአብነትም የማየት፣የመስማት፣ የእንቅስቃሴ እና የመሳሰሉት ችግር ላለባቸው ተማሪዎች ፍላጎታቸውን ለማሟላት ተመሳሳይ ሥራዎች መሠራታቸውን ይጠቅሳሉ። ይሁን እንጂ ገና ብዙ ሥራ መሥራት እንደሚጠይቅ በጥናቱ ግኝት ለማወቅ ተችሏል። የተግባር ልምምድ ጋር በተያያዘ አሁንም የተወሰነ ክፍተት መኖሩ እንደታየ ይናገራሉ።

አቶ አየለ በበኩላቸው እንደሚናገሩት አካቶ ትምህርትን በተመለከተ ለአካል ጉዳተኛ ምቹ እንዲሆን ከማድረግ ባለፈ የሪሶርስ ማዕከላት (ከሥልጠና ወጥተው ልምምድ የሚያደርጉበት) ቦታ ተዘጋጅቷል። የሙያ መረጣን አስመልክቶ ለሴቶች፣ለአካል ጉዳተኞች ነጥቡን ዝቅ ከማድረግ በተጨማሪ ቅድሚያ በመስጠት ልዩ ትኩረት እንዲያገኙ ይደረጋል። በአጠቃላይ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር የአካል ጉዳታቸውን ዓይነት በመለየት ወደ ሙያ ሥልጠናው እንዲገቡ ይደረጋል።

የትብብር ሥልጠና በቴክኒክ እና ሙያ ሥልጠና ተቋማት ላይ በመሠረታዊነት ይሰጣል። የተግባር ልምምዱ በኢንደስትሪ ውስጥ እንዲሰጥ ይፈለጋል። አሁን ላይ ኢንደስትሪዎች ጠቀሜታውን እያወቁት ነው። ነገር ግን አንዳንድ ዘርፎች ላይ በተለይም በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ላይ ማሽኖች ለተለማማጆች ተላልፈው ተሰጥተው ቢሰባበሩ «ማን ይተካልናል?» የሚል ስጋት አለ። ችግሩን ለመፍታት የቴክኒክ እና ሙያ ሥልጠና አዋጁን መሠረት አድርጎ እንዴት ማካካስ እንደሚቻል እና ሌላ የሕግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት እንደሚገባ ምክረ ሃሳብ ቀርቧል። በተወሰነ መልኩ ፍላጎት እና አቅርቦት መኖሩ ጥናቱ በማመላከቱ ይህንንም ከአምራች ኢንደስትሪዎች እንዲሁም ከአገልግሎት ሰጪ ቀጣሪዎች ጋር ቀጣይነት ያለው ምክክር፣ ውይይት እና በጋራ መሥራት እንደሚያስፈልግ ዶክተር ገነነ ያብራራሉ።

ባለሥልጣኑ ችግሩን ለመፍታት ለመዛኞች እንዲሁም ለኢንዱስትሪ እና ለተቋማት አሰልጣኞች ስታንዳርድ አውጥቶ በዛ መንገድ ስለመሰራቱ መከታተል አስፈላጊ መሆኑን ዶክተር ገነነ ይጠቁማሉ። የሙያ ደረጃ፣ ሥርዓተ ትምህርት፣ የማሰልጠኛ መሳሪያዎች እና ሌሎችም ሲዘጋጁ የገበያውን ፍላጎት መሠረት አድርገው እየተሰጡ ስለመሆናቸውም ፍተሻ ማድረግ እንደሚገባ ይጠቅሳሉ። ተቋማቱም ሥልጠና ለመስጠት በሚያስችላቸው ቁመና ላይ መሆናቸውን ማረጋገጥ እንደሚያስፈልግ በጥናቱ ላይ በመፍትሔነት ከቀረቡት ሃሳቦች መካከል ተጠቃሽ መሆኑን ያስረዳሉ።

ዶክተር ገነነ ጨምረው እንደሚያስረዱት በአዲሱ የትምህርት እና ሥልጠና ፖሊሲ ላይ የተለያዩ አማራጮች ተቀምጠዋል። በተለይም የተግባር ልምምድን በተመለከተ ሰልጣኞች ሊማሩ ከሚገባቸው ጋር ተያይዞ ከሚማሩት ጋር የተዛመደ መሆን ይኖርበታል። በኢንደስትሪዎች ውስጥ እየተሰጡ ያሉ እና ኢንደስትሪው በትክክል ሊያሰለጥኑ የሚችሉ ትክክለኛ አሰልጣኞችን መመደባቸውን ከዚህ በተጨማሪም በተግባር ልምምድ ጊዜ የክትትል ሥራዎች መሠራታቸውን መከታል ያስፈልጋል።

በአሁን ወቅት ከቴክኒክ እና ሙያ ሥልጠና ትምህርት ቤቶች የሚወጡትን መፈለግ ብሎም የመቅጠሩ ነገር ከዚህ ቀደም ከነበረው ጋር ሲነጻጸር መሻሻሎች ታይተውበታል። ይሁን እንጂ አንዳንዴ ከተቀጠሩ በኋላ ከእውቀት፣ ከሙያ በተጨማሪ የአመለካከት ክፍተት መኖሩ ታይቷል። እንዲሁም ኢንዱስትሪዎች ሰልጣኞቹን ከቀጠሯቸው በኋላ የሰዓት አጠቃቀም፣ የሥራ ፍላጎት አናሳ መሆን በሰልጣኞቹ በኩል እንደ ችግር ይነሳል። በቀጣሪው በኩል ደግሞ በቂ የሚባል ክፍያ ስለማይከፈላቸው ለቆ የመውጣቱ ነገር በስፋት መታየቱ በጥናቱ ተመላክቷል።

በከተማዋ በሚገኙ አንዳንድ ሰልጣኞች ላይ የቴክኒክ እና ሙያ ሥልጠና ትምህርት እንደ ጊዜ ማሳለፊያ እና ሌላ ዕድል እስከሚያገኙ ድረስ ያለፍላጎታቸው የሚማሩ መኖራቸው በጥናቱ አማካኝነት ታውቋል። ተግባራዊ ልምምድ ሳይወስዱ እንደወሰዱ ተደርጎ «ደብዳቤ ፃፉልን፡» የሚሉ ሰልጣኞችም አልጠፉም። ስለዚህም በተማሪዎች በኩል ለቴክኒክ እና ሙያ ትምህርት ያለው ዝቅተኛ አመለካከት ሙሉ በሙሉ ተቀርፏል ብሎ መናገር አይቻልም።

በተመሳሳይ በማኅበረሰቡ በኩል የአስተሳሰብ መዛባት አለ ያሉት አቶ አየለ፤ የተለያዩ አደረጃጀቶችን በመጠቀም ተማሪዎች አማራጭ አጥተው ሳይሆን መርጠውት እንዲመጡ ኅብረተሰቡ እንዲያውቀው እየተሠራ ነው ሲሉ ይገልፃሉ። ከትምህርት ቢሮ ጋር በጋራ በመሆን ተማሪዎች ገና ወደ ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ከመምጣታቸው በፊት የግንዛቤ ሥራ እየተሠራ መሆኑንም ይጠቁማሉ። በተጨማሪም ከተቋማቱ ወጥተው የራሳቸውን ድርጅት ከፍተው እና በተለያዩ ቦታዎች ላይ ተቀጥረው እየሠሩ ያሉ ሰዎችን በመገናኛ ብዙኋን የማስተዋወቅ ሥራ እየተሰራ መሆኑን ያስረዳሉ።

በአንዳንድ ሠልጣኞች በኩል ሥልጠናውን የማይፈልጉበት ምክንያት «እስከ ደረጃ አምስት ከተማርን በኋላ ለማደግ አያስችለንም።» የሚል ይሁን እንጂ በአዲሱ የትምህርት እና ሥልጠና ፖሊሲ መሠረት ተማሪዎቹ ጠንክረው ከተማሩ እስከ ደረጃ ስምንት (ከፒኤች ዲግሪ ጋር እኩል ) ለመድረስ እንዲቻላቸው ሁኔታዎች እንደተመቻቹላቸው ይጠቅሳሉ። በማኅበረሰቡ፣ በቀጣሪዎች እንዲሁም በሠልጣኞች የተወሰነ መሻሻሎች ቢኖሩም ብዙ መሥራትን እንደሚጠይቅ ይገልጻሉ።

አቶ አየለ በበኩላቸው እንደሚሉት በአሁን ወቅት በቴክኒክ እና ሙያ እስከ ደረጃ ስምንት መማር የሚቻልበት ሁኔታ በመፈጠሩ በሙያ የተደገፈው ትምህርት ለመማር የሚያስችል አሠራር ተዘጋጅቷል። በ2015 ዓ.ም የአስራ ሁለተኛ ክፍል ውጤትን አስመልክቶ በርካቶች ውጤት ያላመጡ መሆናቸው እንደ መልካም ዕድል መቆጠር አለበት። ወደ ዩኒቨርሲቲ የገባ ብቻ አይደለም በትምህርት ዘርፍ መቀጠል የሚችለው። ቴክኒክ እና ሙያ ሌላ አማራጭ ነው። ተማሪዎች ወደ ተቋማቱ የመግባታቸው ነገር የሰፋ በመሆኑ በቴክኒክና ሙያ ተቋማት ላይ ምንም የሚፈጥረው ጫና የለም። ከዚህ ጋር ተያይዞም ከደረጃ አንድ እስከ አምስት ሥልጠና ለመስጠት በቂ ዝግጅት ተደርጓል።

የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ እንደሚገልጹት፤ ገበያን መሠረት ያደረገ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ለሀገር እድገት ወሳኝ መሆኑን በመረዳት ባለሥልጣኑ በቀጣይ በግኝቱ መሠረት ችግሮችን ለይቶ የቁጥጥርና የድጋፍ ሥራዎችን ይሠራል።

# ወቅታዊ

# ‹‹ሜቴክ ያሳረፈው ጠባሳ የከፋ ቢሆንም፤ ተቋማትን ትርፋማ ማድረግ ተችሏል››

*የኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አምባሳደር ሱለይማን ደደፎ*

እስማኤል አረቦ

ስለሙስናና ምዝበራ ሲነሳ ቀድሞ ከሚታሰቡ ተቋማት ውስጥ የቀድሞው የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን(ሜቴክ) አንዱ ነው። ሜቴክ ከተቋቋመበት ዓላማ በተጻራሪ መልኩ በበርካታ መዝበራና ብልሹ አሰራር ውስጥ በመውደቁ ለትውልድ የሚተርፍ ዕዳ አውርሶ ሄዷል። በቅርቡ በመገናኛ ብዙሃን ይፋ እንደተደረገውም በሜቴክ አማካኝነት ከባንክ ወጥቶ ምን ላይ እንደዋለ የማይታወቅ 65 ቢሊዮን ብር በመንግሥት እንዲሰረዝ መደረጉ የዚሁ አንድ ማሳያ ነው።

የለውጡ መንግሥት እንደመጣ በመጀመሪያ ከተቃወማቸውና ስር ነቀል ለውጥ ያስፈልጋቸዋል ብሎ አቋም ከወሰደባቸው አሰራሮች ውስጥ የመጀመሪያው የሜቴክን መዋቅር እና አሰራር ማፍረስ ነው። ይህን ሕገ ወጥ አሰራር ሲሰሩ የነበሩትን ወደ ሕግ ከማቅረብ ጀምሮ በስሩ የነበሩ ተቋማትን ለሁለት በመክፈል አዲስ አደረጃጀት ለመፍጠር ተችሏል። ወታደራዊ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትን በመከላከያ ሚኒስቴር ውስጥ ማካተት የመጀመሪያው ሲሆን ለሕዝብ የዕለት ተዕለት አገልግሎት የሚሰጡትን ቀሪዎቹን ተቋማት በአንድነት በማደራጀት ኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ የሚል ስያሜ ተሰጥቷቸዋል።

የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍልም በአዲስ መልክ ከተቋቋመውና የኢንዱስትሪውን ዘርፍ በበላይነት እንዲመራ ተልዕኮ ከተሰጠው ከኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አምባሳደር ሱለይማን ደደፎ ጋር ቆይታ አድርጓል። መልካም ንባብ።

**አዲስ ዘመን፡- የቀድሞው ሜቴክ የአሁኑ ኢትዮ ኢንጂነሪንግ ሲቋቋም አላማው ምን ነበር ?**

**አምባሳደር ሱለይማን ደደፎ፡-** ሜቴክ የተቋቋመበት ዋነኛ ዓላማ የሀገሪቱን የኢንዱስትሪ ዘርፍ እንዲመራ ነው። በፈጠራ እና በቴክኖሎጂ ሽግግር በሀገሪቱ ያሉትን ኢንዱስትሪዎች እንዲደግፍና የጥናትና ምርምር ሥራዎችን እንዲያካሂድ ታልሞ የተቋቋመ ግዙፍ ድርጅት ነው።

በሀገሪቱ ተበታትነው የነበሩ የብረታ ብረት ኢንዱስትሪዎችን በማስተባበርና በመምራት ለሀገሪቱ የኢንዱስትሪ እድገት አስተዋጽኦ የማበርከት ኃላፊነት የተጣለበት ተቋም ነበር። በአጠቃላይ ሜቴክ የሚባለው ተቋም የተሰጠው ኃላፊነት ሰፊና ሀገሪቱንም በኢንዱስትሪው ዘርፍ እምርታ እንድታመጣ ታልሞ የተቋቋመ ትልቅ ተቋም ነበር። ይህ ግዙፍ ተቋም ከሀገሪቱ ኢንዱስትሪ ባሻገር የመከላከያ ሠራዊትን በተለያዩ ፈጠራዎች የማጠናከር ተልዕኮም ተሰጥቶታል።

ሀገር የሚያድገው በብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ዘርፍ በመሆኑ፤ ይኸው ድርጅት የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ተቋም ሆኖ እንዲቋቋም መንግሥት ሲወስን ኢትዮጵያን በኢንዱስትሪው ዘርፍ ወደፊት ያራምዳል ከሚል እምነት ነበር።

በሀገር ውስጥ የማይመረቱ እና በሕዝብ ተፈላጊ የሆኑ ምርቶችን በማምረት ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን የመተካትም ሚና ነበረው።

በተለይም ለመከላከያው ዘርፍ ጥናትና ምርምሮችን በማድረግ ሀገሪቱ በወታደራዊው ዘርፍ ልቃ የምትወጣበትን ሁኔታ ማመቻቸትም የተልዕኮው አንዱ አካል ነበር። የተለያዩ ትጥቆችን፤ መሳሪያዎችን እና ለወታደራዊ ተልዕኮ አጋዥ የሆኑ ልዩ ልዩ ልማቶችን እንዲያካሂድም ኃላፊነት የተጣለበት ተቋም ነው።

ሆኖም በነበሩ ብልሹ አሰራሮች እና አስተሳሰቦች የተሰጠውን ተልዕኮ ከግብ ሳያደርስ ተኮላሽቶ ቀርቷል። አካሄዱም እጅግ አደገኛና ሀገርንም ለበርካታ ችግሮች የተጋለጠ ነበር። ያወረሰውም ዕዳ ለትውልድ የሚተላለፍ ሆኗል።

**አዲስ ዘመን፡- ሜቴክ ከተሰጠው ተልዕኮ አፈንግጦ እንዴት ወደ ምዝበራ ሊገባ ቻለ?**

**አምባሳደር ሱለይማን ደደፎ፡-** በሂደት በሜቴክ ውስጥ ያለው አመራር ከተሰጠው ኃላፊነት በማፈንገጥ የራሱን ኢምፓየር መመስረት ጀመረ። ለመንግሥታዊ አሰራር፤ ለሕግና ደንብ ለመገዛት ፍቃደኛ አልነበረም። አመራሩ በመንግሥት ለመታዘዝ አለመፈለግና ጭራሹኑም ከመንግሥት በላይ የመሆን ፍላጎት አደረበት። በተግባርም አዋለው።



> የሜቴክ አመራሮች ይህን ሁሉ ሕገ ወጥ ተግባር ሲፈጽሙ የነበረው ከአናቱ የነበሩ አመራሮችን በመተማመን ነበር። ከተቀማጭ ገንዘብ ላይ ገንዘብ ለግለሰቦች ያለዋስትና የሚሰጥበት ሀገር የለም። በኢትዮጵያ ግን ያለምንም ማስያዣ ገንዘብ እንደልብ ከባንክ ይወጣ ነበር

አመራሩ ለራሱ በሚጠቅመው መልኩ ሕግና አሰራሮችን መተርጎም፤ ሕግን በራስ እጅ ውስጥ የማስገባትና አንዳንዴም የራስን ህሕ የማውጣት አካሄዶችን ይከተል ነበር። የንብረት አያያዝ፤ አጠቃቀም፤ ግዢ ሥርዓት ሁሉ ከመንግሥት መመሪያ ውጭ ይፈጸም ነበር። የውጭ ምንዛሬ የሚገኝበትም ሆነ የገንዘብ ዝውውር የሚካሄድበት መንገድ ፍጹም ሕገ ወጥ አካሄድን የተከተለ ነበር። በአጠቃላይ በሂደት ተቋሙ የተሰጠው ተልዕኮ ከሽፎ የሕገ ወጦች መናኸሪያ እና የዘረፋ ተቋም ለመሆን በቃ ።

በተዘረጋው የዘረፋ ሰንሰለትም ግለሰቦች፤ ቡድኖች እራሳቸውን የሚያበለጽጉበትና እንደፈለጉ የሀገርና ሕዝብ ሀብት እያፈሱ የሚሰጡበት ተቋም ወደ መሆን ተሸጋገረ። ከዛም አለፍ ብሎ ከተለያዩ የመንግሥት ተቋማት ግዢዎችንና ኮንትራቶችን በትዕዛዝ በመቀበል ለግል ጥቅማቸው ያውሉ ነበር። ጭራሽ ተቋሙ የሚከተለው በትዕዛዝና በማስፈራራት የተወሰደ ኮንትራትና ግዢ ውል የማይፈጸምበትና ስምምነትም የማይፈረምበትን አካሄድ ነበር።

ተቋሙ ኮንትራቶችን የሚወስደው ውል ቢፈራረምም እንደማይከሰስና ተጠያቂነትም እንደሌለበት ተፈርሞለት ሆነ። በዚህ አካሄድም ከእያንዳንዱ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ኮንትራቶችን ወስዶ መና አስቀርቷል። ተቋሙ እንደ ንጉስ የማይከሰስ ስለሆነ የወሰደውን ኮንትራት ባይፈጽም የሚጠይቀው አልነበረም። አሁን ሜቴክ የተፈራረማቸውን ሰነዶች ስንመለከት ‹‹ሜቴክ የወሰዳቸውን ኮንትራቶች በወቅቱ ባይፈጽም በድርድር ይፈታል እንጂ በህግ አግባብ አይጠየቅም›› የሚሉ ውሎች ቤቱን ሞልተውት ተገኝተዋል።

ሜቴክ ሲፈራረማቸው የነበሩ ውሎች ከሕገ መንግሥቱ በላይ ሥልጣን የሰጠው ነበር። በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ማንኛውም ሰው፤ ባለሥልጣን፤ ቡድን፤ ተቋም ላጠፋው ነገር ይከሰሳል። ሁሉም አካል ከሕግ በታች ነው። ሜቴክ ግን ማንም አይከሰውም፤ ጥፋት ቢያጠፋም ለምን አጠፋህ ብሎ የሚጠይቀው አልነበረም። ይህ ደግሞ ሀገሪቱ የምትከተለውን ሕገ መንግሥትንና እሱን ተከትለው የወጡ ሕጎች የሚጥስና ተቋሙንም አይነኬ ያደረገ ነበር።

ከሜቴክ ጋር ውል የሚገቡ ተቋማት ወደ ሥራ የሚገቡት መጀመሪያውኑ ስምምነት ሲያደርጉ ሜቴክን እንደማይከሱ ፈርመው ነው። ይህን የሚያደርጉት ደግሞ ወደው አይደለም፤ ተገደው ነው። የሚደርሳቸው ማስፈራርያም ከሥራ መሰናበት ብቻ ሳይሆን ሕይወትንም እስከማጣት የሚያደርስ ነበር። በፀረ መንግሥትነት፤ በፀረ መከላከያነትና በፀረ ሜቴክነት ተከሰው መቀመቅ ሊገቡ ይችላሉ።

**አዲስ ዘመን፡- ከሕግ ውጭ እነዚህን ሥራዎች ሲፈጽም የሚጠይቀው አካል አልነበረም ?**

**አምባሳደር ሱሌማን ደደፎ፡-** ችግሩ የነበረው ከአናቱ ነው። የሜቴክ አመራሮች ይህን ሁሉ ሕገ ወጥ ተግባር ሲፈጽሙ የነበረው ከአናቱ የነበሩ አመራሮችን በመተማመን ነበር። ከተቀማጭ ገንዘብ ላይ ገንዘብ ለግለሰቦች ያለዋስትና የሚሰጥበት ሀገር የለም። በኢትዮጵያ ግን ያለምንም ማስያዣ ገንዘብ እንደልብ ከባንክ ይወጣ ነበር። የሜቴክ አመራሮች በሙሉ የበላይ ኃላፊዎችን በመተማመን በገሃድ ሲፈጽሙት የቆዩት ተግባር ይህንን ነው። የሜቴክ አመራሮች ከንግድ ባንክ፤ ከልማት ባንክ እና ከሌሎች የፋይናንስ ተቋማት ዶላር አዘው እና በሻንጣ ይዘው ወደ ውጭ ሀገር የሚወጡበትና በውጭ ባንኮችም የፈለጉትን ያህል ዶላር የማስቀመጥ መብት ነበራቸው።

የሜቴክ አመራሮች በሙሉ የራሳቸው አሠራር አላቸው፤ የራሳቸው ፋይናንስ አላቸው፤ የራሳቸው አካሄድ አላቸው። በአጠቃላይ ኢትዮጵያን የግላቸው አድርገው ሲመዘብሯት ኖረዋል። በዚህም ሀገሪቱ እስካሁን ተከፍሎ ያላለቀ እና ለትውልድ የሚተርፍ እዳ አሸክመዋታል። ትውልድም የእነዚህን ሰዎች ጦስ ተሸክሞ ዕዳ ሲገፈግፍ ይኖራል።

**አዲስ ዘመን፡- ከሜቴክ ውስጥ የአሁኑ ኢትዮ ኢንጂነሪንግ እንዴት ወጣ ?**

**አምባሳደር ሱሌማን ደደፎ፡-** የለውጡ መንግሥት እንደመጣ በመጀመሪያ ከተቃወማቸውና ስር ነቀል ለውጥ ያስፈልጋቸዋል ብሎ አቋም ከወሰደባቸው አሰራሮች ውስጥ የመጀመሪያው የሜቴክን መዋቅር እና አሰራር ማፍረስ ነው። ይህን ሕገ ወጥ አሰራር ሲሰሩ የነበሩትን ወደ ሕግ ከማቅረብ ጀምሮ በስሩ የነበሩ ተቋማትን ለሁለት በመክፈል አዲስ አደረጃጀት ለመፍጠር ተችሏል። ወታደራዊ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትን በመከላከያ ሚኒስቴር ውስጥ ማካተት የመጀመሪያው ሲሆን፤ ቀሪዎቹን ለሕዝብ የዕለት ተዕለት አገልግሎት የሚሰጡትን ተቋማት በአንድነት በማደረጃት ኢትዮ ኢንጂነሪንግ የሚል ስያሜ እንዲሰጣቸው ተደረገ።

ኢትዮ ኢንጂነሪንግ ዘጠኝ ተቋማትን በማቀፍ የተቋቋመ ግዙፍ ተቋም ነው። ኢትዮ ፕላስቲክ፤ አዲስ ማሽን መለዋወጫ ፋብሪካ፤ አቃቂ ቤዚክ ሜታልስ ኢንዱስትሪ፤ ቢሾፍቱ አቶሞቲቭ ኢንዱስትሪ፤ አዳማ የግብርና ማሽነሪዎች ማምረቻ ፋብሪካ እና ደብረ ብርሃን ላይ የሚገኘው የኮንስትራክሽን ዕቃዎች ማምረቻ ይገኙበታል።

**አዲስ ዘመን፡- ከሜቴክ ወደ ኢትዮ ኢንጂነሪንግ የነበረው ሽግግር ምን ይመስላል?**

**አምባሳደር ሱሌማን ደደፎ፡-** እጅግ ከባድ ነበር። ሜቴክ በቀውስ ውስጥ የነበረ ተቋም በመሆኑ ሽግግሩም ቀውስ የነበረበት ነው። ሜቴክ ሀብትና ንብረቱ የማይታወቅ፤ ዕዳው የማይታወቅ፤ ተጠያቂነት የሌለበት ተቋም ነበር። እናም ይህንን አጣርቶና አደራጅቶ ለሀገርና ለሕዝብ የሚጠቅም ተቋም ማድረግ እጅግ ፈታኝ ቢሆንም፤ በዚህ እልህ አስጨራሽ ጥረት ውስጥ ኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ የሚባል አዲስ ተቋም ሊወለድ ችሏል።


በሜቴክ ውስጥ የነበሩት ተቋማት ግዙፍ ነበሩ። ቢሆንም በአሰራር ብልሹነት የመከኑ ስለነበሩ እነዚህን ተቋማት ወደ ምርታማነት ለመመለስ እጅግ ፈታኝ ነበር። ተቋማቱን በአዲስ አደረጃጀትና አመለካከት ጭምር የተነቃቁና አትራፊ እንዲሆኑ ለማድረግ ወደ አራት ዓመታት ፈጅቷል።

አሁን ፈታኝ ከሆኑብን ጉዳዮች አንዱ ሜቴክ በነበረበት ወቅት የወሰዳቸውን ኮንትራቶች በአግባቡ ባለመጨረሱ

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

# ወቅታዊ

ከ ገጽ 9 የዞረ



የተለያዩ አካላት ተቋሙን መክሰስ ጀምረዋል። ኢትዮ ኢንጂነሪንግ ባልፈጸመው ወንጀል በሜቴክ ምክንያት እየተከሰሰ ነው። ሜቴክ ይከተለው በነበረው አሰራር የደላላ ባህሪን ተላብሶ ይስራ ስለነበረ ከአንድ ተቋም ሥራዎችን ይወስድና እንደ ደላላ ሆኖ በሰብ ኮንትራት አካሄድ ሥራውን አሳልፎ ለአንድ ተቋራጭ ወይም ድርጅት ይሰጣል። ያም ድርጅት የሚከታተለው አካል ስለሌለ ሥራውን በአግባቡ ሳያከናውን ገንዘቡን ወስዶ ይጠፋል። በዚህ ሁኔታ በርካታ ተቋማት ገንዘባቸው ተበልቶ ቀርቷል። በዚህ የተነሳ በርካታ የክስ ፋይሎች እየመጡ ነው።

ለምሳሌ ግዙፍ የሆነውን ያዩ የማዳበሪያ ፋብሪካን እገነባለሁ ብሎ ሥራውን ከኬሚካል ኮርፖሬሽን ከወሰደ በኋላ ሜቴክ እራሱ መሥራት ሲገባው ተክሉ ብርሃን አምባዬ ለተባለ ድርጅት አሳልፎ ሰጥቷል። ሆኖም በብዙ ቢሊዮን ብር የፈሰሰበት ይህ የማዳበሪያ ፋብሪካ ሳይሰራ መክኖ ቀርቷል። ያዩ ማዳበር እና ሌሎች መሰል ዕዳዎችም ሊከፈሉ የማይችሉ ስለሆኑ በኦዲት ተረጋግጦ ከ65ቢሊዮን ብር በላይ ለመንግሥት ቀርቦ እንዲሰረዝ ተደርጓል። ይህ ለኢትዮጵያ ትልቅ ኪሳራ ነው። ከድሃ እናት መቀነት፤ ከድሃ አርሶ አደር ኪስ፤ ከጉሊት ቸርቻሪ እናት ኪስ የወጣ ገንዘብ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ይሄ 65 ቢሊዮን ብር ንብረት ላይ የዋለ ነው ወይስ በግለሰቦች በጥሬው የተወሰደ?**

**አምባሳደር ሱስይማን ደደፎ፡-** ገንዘቡ በግለሰቦች አማካኝነት ከባንክ ወጥቷል። ነገር ግን ምን ላይ እንደዋለ አይታወቅም። ኦዲት ሲደረግም በዚህ ገንዘብ የተገዛ ዕቃ ወይም ንብረት የለም። ስለዚህ ይህ 65 ቢሊዮን ብር ዕቃ የገዙበት ይሁን ወይም የተከፋፈሉት የሚታወቅ ነገር የለም።

አንዳንድ ዕቃዎች ተገዙም ቢባል ጥቅም የሚሰጡ አይደሉም። ለምሳሌ አምስት ሺ ትራክተሮች ተገዝተው አንድም ቀን አገልግሎት ሳይሰጡ ዝም ብለው አዳማ ላይ ተቀምጠዋል። እነዚህ አምስት ሺ ትራክተሮች ለአንድም ቀን አልሰሩም። ትራክተሮቹ የተገዙት ከየቦታው ተለቃቅመው ነው። ከተገዙት ውስጥ የአንዳንዶቹ ትራክተሮች ፋብሪካ ከተዘጉ ዓመታት ተቆጥረዋል። መለዋወጫ እንኳን የላቸውም። ስለዚህም ብክነቱ በቃላት ከሚገለጸው በላይ ነው።

ሜቴክ በሀገር ውስጥ ያለውን ነዳጅ የማይጠቀሙ ሁለት አውሮፕላኖችን ገዝቶ ያስገባ ድርጅት ነው። ለእነዚህ አውሮፕላኖች የሚሆን ነዳጅ በሀገር ውስጥ ስለሌለ በከፍተኛ ብር የተገዙት እነዚሁ አውሮፕላኖች ያለምንም ጥቅም ተቀምጠዋል። እነዚህ አውሮፕላኖች አንድም ቀን በረው አያውቁም። ኢትዮ ኢንጂነሪንግም እንደንብረት የሚረከባቸው አይደሉም።

በተመሳሳይም ሕዳሴ ግድብ ላይ ተፈጽሞ የነበረው ግፍ አንዱ የሜቴክ ቅሌት ነው። ብቃትና ዕውቀቱ ሳይኖረው ሕዳሴን የሚያክል ግዙፍ ፕሮጀክት እሰራለሁ ብሎ ተነስቶ ሥራውን ከማጓታት ባሻገር በርካታ ሚሊዮን ብሮች ባክኖ እንዲቀር አድርጓል። ሆኖም እንደ አጋጣሚ ሆኖ የመንግሥት ለውጥ በመምጣቱ የሕዳሴ ግድብ ከውድቀት ተረፈ እንጂ እንደሜቴክ አካሄድ የሕዳሴ ግድብ መክኖ መቅረቱ ሳይታለም የተፈታ ነበር።

በአሁኑ ወቅት የማዳበሪያ ጉዳይ ኢትዮጵያን እየፈተነ ያለና የአርሶ አደሩም የዕለት ተዕለት ጥያቄ ነው። ሜቴክ ያባከነው 65 ቢሊዮን ብር በርካታ የማዳበሪያ ፋብሪካ ይገነባ ነበር። ከዛሬ ስምንት ዓመት በፊት በ65 ቢሊዮን ብር ትላልቅ ሜጋ ፕሮጀክቶችን መገንባት ይቻል ነበር። ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ሳስበው የድህነታችን ሚስጥር አባካኝነታችን እንደሆነ ይሰማኛል። የደሃ ሀገር እና ሕዝብን ገንዘብ በዚህ መጠን ማባከን እንደሀገር ውድቀት ነው።

ሆኖም ሀገርና ሕዝብ መቀጠል አለባቸውና ቀደም ሲል የተሰሩ ስህተቶች እንደሀገር እያረምን እየሄድን ነው። በተለይም እንደ ተቋም እጅግ ፈታኝ የነበረው የምዝበራና የሌብነት አስተሳሰብን ማስወገዱ ነው። በሜቴክ ውስጥ እጅግ የገነገነ የሌብነትና የምዝበራ አስተሳሰብ ነበር። ከታች እስከ ላይ ድረስ ሰርቶ ከማደግ ይልቅ በምዝበራ የመበልጸግ ሜቴካዊ አስተሳሰብ ነበር። ዛሬም ይህ አስተሳሰብ ሙሉ በሙሉ ተወግዷል ብለን አፋችንን ሞልተን ባንናገርም፤ አሁን በትግል ነገሮች በመለወጥ ላይ ናቸው።

ነገር ግን የሌብነት ጉዳይ ከተነሳ በሜቴክ ውስጥ ብቻ ሳይሆን አሁንም እንደሀገር ትልቅ ችግር አለ። የሌብነትና በአቋራጭ የመክበር አስተሳሰብ የትውልዱ በሽታ ነው ማለት ይቻላል። ስለዚህም ሀገር እንድትድን የሚፈልግ ዜጋ በሙሉ በዚህ ጉዳይ ላይ ሊያስብበት ይገባል። ሌብነት ላይ በዘመቻ ትልቅ የባህል አብዮት አካሂደን ችግሩን ከስር መሠረቱ ካልነቀልነው በስተቀር እንደ ሀገር ሊያጠፋን የሚችል ችግር ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የራሱ የሆነ አኩሪ ባህል ያለው ሕዝብ ነው። ሌብነትን የሚጸየፍና ብሎም የሚቆጣ ነው። ስለዚህም ዘረፋን፤ ሌብነትንና በአቋራጭ መክብርን እንደ ሕዝብ ተነስተን ልንዋጋው የሚገባ ጉዳይ ነው። ሌብነት አስነዋሪ ነው፤ ማጭበርበር አስነዋሪ ነው፤ የሕዝብ ሀብት ማባከን አስነዋሪ ነው፤ የራስ ያልሆነን ንብረት መወሰድ አስነዋሪ ነው። ስለዚህም እነዚህን አስነዋሪ ተግባራት መዋጋት ለፖሊስ ወይም ለአንድ የሕግ አካል የምንተወው ሳይሆን ሁላችንም በአንድነት በመቆም ልንዋጋው የሚገባ የሀገር ጠላት ነው።

በአዲስ መልክ የተቋቋመው ኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕም በዚህ ላይ ትግል እያደረገ ነው። በተለይም ተቋሙ ከሜቴክ የሌብነትና የምዝበራ አስተሳሰቦች የጸዳና በአንጻሩም ሌብነትና ብልሹ አሰራሮችን የሚጸየፍ ሠራተኞች እንዲኖሩት የተለያዩ ስልቶችን ነድፎ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል።

**አዲስ ዘመን፡- ከሜቴክ ወደ ኢትዮ ኢንጂነሪንግ ሲሸጋገር የዓላማ ለውጥ አድርጓል?**

**አምባሳደር ሱሌማን ደደፎ፡-** የዓላማ ለውጥ አላደረገም። ሜቴክም ቢሆን እኮ በወረቀት ላይ ያለው ዓላማው የሚናቅ አይደለም። ዋነኛ ዓላማውም ከላይ እንደገለጽኩት የሀገሪቱን የኢንዱስትሪ ዘርፍ መምራት ነው። በሀገር ውስጥ የማይመረቱና በሕዝብ ተፈላጊ የሆኑ ምርቶችን በሀገር ውስጥ በማምረት ክፍተትን መሙላት ነው። ጥናትና ምርምር በማድረግም የሀገሪቱ ኢንዱስትሪዎች ዘመናዊ አሰራርን እንዲከተሉና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማድረግ ነው። እነዚህ አላማዎች ደግሞ የሚደገፉና ሀገርንም ወደፊት የሚያራምዱ ናቸው።

ስለዚህ ሜቴክ ቀድሞ ስለያዛቸው እኛ ልንወስዳቸው አንችልም አንልም። እኛ ያደረግነው የአሰራር፤ የአስተሳሰብ፤ የአካሄድ ለውጥ ማድረግ ነው። ኢትዮ ኢንጂነሪንግ በሕግ ጥላ ስር ሆኖ በሕግ የሚመራ፤ ተጠያቂነት ያለበት፤ ሲያጠፋ የሚቀጣ፤ የሚከሰስ፤ ተቋም ሆኖ እንዲቀጥል ማስቻል ነው። የተሰጡትን ሀገራዊ ተልዕኮዎች የሚወጣና ኢንዱስትሪውንም በዕውቀት የሚመራ ተቋም እንዲሆን ማስቻል ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮ ኢንጂነሪንግ በአሁኑ ወቅት ምን ያህል ውጤታማ ነው ?**

**አምባሳደር ሱሌማን ደደፎ፡-** ኢትዮ ኢንጂነሪንግ ከመጣበት ጊዜ ጀምሮም ቢሆን ሜቴክ ያሳረፈበት ጠባሳ ከባድ በመሆኑ ፤ ላለፉት አራት ዓመታት በኪሳራ ውስጥ ቆይቷል። እስካለፈው አጋማሽ ድረስ ዘጠኙም ፋብሪካዎች ኪሳራ ውስጥ ነበሩ። በተለይም ተቋማቱ በአግባቡ ሲመሩ ስላልቆዩና የማሽነሪዎችም እርጅና ስላለ በፍጥነት ወደ ውጤታማነት መለወጥ አዳጋች ነበር። ሠራተኛውም ቢሆን በሚፈለገው መልኩ ውጤታማ አልነበረም። የጥሬ ዕቃ እጥረት አንዱ ችግር ነበር።

ካሉን ዘጠኝ ፋብሪካዎች ስድስቱ ከውጭ በሚገባ ጥሬ ዕቃ ላይ የተመሰረቱ በመሆናቸው፤ የውጭ ምንዛሬን የሚሹ ናቸው። አሁን ባለንበት ተጨባጭ ሁኔታ እንደ ሀገር ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ እጥረት ያለብን በመሆኑ፤ እነዚህ ፋብሪካዎች ከውጭ ጥሬ ዕቃ ለማግኘት ተቸግረዋል። ባላቸው አቅምም ለማምረት አልቻሉም። ኢትዮ ኢንጂነሪንግ ሜቴክ ያሳረፈበት ጠባሳ የከፋ ቢሆንም፤ በስሩ ያሉት ትልልቅ ተቋማት ከብዙ ጥረት በኋላ ካለፈው ዓመት ወዲህ ትርፋማ መሆን ጀምረዋል።

ከብዙ ጥረት በኋላ ካለፈው ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ ጀምሮ ትርፋማ መሆን ጀምረዋል። ባለፈው የ2015 በጀት ዓመትም ኢትዮ ኢንጂነሪንግ ወደ 480 ሚሊዮን ብር ማትረፍ ተችሏል። አጠቃላይ ሀብታቸውም ወደ ሁለት ቢሊዮን ብር ደርሷል። ይህ በቂ አይደለም። ኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግዙፍ ተቋም ከመሆኑ አንጻር ገና ብዙ ማትረፍና ለሀገሪቱንም የኢንዱስትሪ እንቅስቃሴ አርአያ ሊሆን የሚገባው ነው።

ሆኖም ኢትዮ ኢንጂነሪንግ የነበሩበትን መሰናክሎችና ውጣ ውረዶች አልፎ ማትረፍ እንደሚችል አረጋግጧል። ይህንንም ከግምት ውስጥ በማስገባት በ2016 በጀት ዓመት አጠቃላይ ምርቱን 15 ቢሊዮን ብር ለማድረስና የሁለት ቢሊዮን ብር ዓመታዊ ትርፍ ለማስመዝገብም አቅዷል። በተለይም መንግሥት ለአቅርቦት የሚሆን የዶላር ብድር ስለተፈቀደለት ከውጭ የሚገቡ ጥሬ ዕቃዎችን በቀላሉ በማስመጣት ፋብሪካዎቹ በሙሉ አቅማቸው እንዲሰሩ ለማድረግ እንሞክራለን።

ከቻይና ገበያ በተጨማሪ የአውሮፓ ገበያን በመጠቀም ጥሬ ዕቃዎች የሚገቡበት ሁኔታ ይመቻቻል። ጥሬ ዕቃ የምናገኝባቸውን የገበያ አማራጮች ማስፋት አለብን በሚል በአሁኑ ወቅት ከአንዳንድ የአውሮፓ ገበያዎች ጋር ግንኙነት ማድረግ ጀምረናል። ለምሳሌ ቀደም ሲል ጀምሮ የጣሊያን ምርቶች በጥራትም ሆነ በጥንካሬ በኢትዮጵያ ተወዳጅ ምርቶች ነበሩ። ጥራት እና ጥንካሬ ያላቸው የጣሊያን የጭነት መኪናዎች፤ አውቶቡሶች በኢትዮጵያ ለዘመናት አገልግሎት ሲሰጡ ቆይተዋል። እነሱን ለማስመለስ እንቅስቃሴ ጀምረናል። በተመሳሳይም የጀርመን፤ የኔዘርላንድ አውቶቡሶች በኢትዮጵያ ተመራጮች ናቸው። እነዚህን ለማስገባት ድርድር ላይ እንገኛለን።

ባለፉት ዓመታት ኢትዮጵያ የርካሽ ዕቃዎች ማራገፊያ ሆና ቆይታለች። አነስተኛ ዋጋ በሚል ሰበብ በሚወጣ ጨረታ ለሀገርና ለሕዝብ የማይመጥኑ ዕቃዎች ኢትዮጵያን አጨናንቀዋታል። በየቦታው ሶስት ዓመት እንኳን ሳይሰሩ የሚቆሙ መኪኖች፤ አውቶቡሶች፤ በርካታ ናቸው። ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚቀርቡ ቁሳቁሶች አንድ ጊዜ አገልገለው የሚወረወሩ ናቸው። በአጠቃላይ ስታንዳርድ አጥተናል። ለጥራት ያለን አመለካከት ተዛብቷል።

ጥራት ያለውን እቃ እየተውን ተልካሻ ዕቃ በመረጥን ቁጥር ድህነትን እናባዛለን እንጂ አናተርፍም። ርካሽ ዕቃ እያሳደደን በሄድን ቁጥር ሀብትን እያባከንን እንሄዳለን። ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡ ዕቃዎች በሙሉ ርካሽ ስለሚሆኑ ብዙም አገልግሎት ሳይሰጡ ከጥቅም ውጭ ይሆናሉ። ነገር ግን እንደ ሀገር የምናወጣው ገንዘብ ውድ ዕቃዎችን ጭምር ለመግዛት የሚያስችለን ነው። የሚወጣው ገንዘብ በርካሽ ዋጋ ልክ አይደለም። ሌብነቱ ተጨምሮበት፤ ማጭበርበሩ ታክሎበት ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን ዕቃዎች ሊገዛ የሚችል ገንዘብ ነው እየባከነ ያለው።

በሀገር ውስጥ ያሉ በርካታ የመንግሥትም ሆነ የግል ፋብሪካዎች የሚገጥሟቸው ማሽኖች በአውሮፓ ለረጅም ዘመናት ያገለገሉና ዘመን ያለፈባቸው ናቸው። በርካቶችም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ እንዲሸጡ ውሳኔ የተላለፈባቸውና የማምረት አቅማቸውም የተዳከመ ነው። ሆኖም በደላላ አማካኝነት እነዚህ ማሽኖች ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ ተደርገው ብዙም ሳይሰሩ ይቆማሉ፤ ለመለዋወጫም በርካታ ዶላሮችን ያስወጣሉ።

በእኛ እጅ እንኳን ከ10 በላይ ፋብሪካዎች በዚህ ዓይነት መልኩ ያረጁ ማሽኖች የተገጠሙላቸው ናቸው። ዓይነታቸው የማይታወቁ፤ ምን እንደሚሰሩ የማይታወቁ እንዲሁ ተገዝተው ቁጭ ያሉ አሮጌ ማሽኖች በእኛው ድርጅት ውስጥ አሉ። እዚህ ከገቡ ጀምረው አንድም ቀን ያልተንቀሳቀሱ ማሽኖች አሉ።

አጠቃላይ እንደ ሀገር ጥራት አጥተናል። የትምህርት ሥርዓታችን ጥራት የለውም። አስተራረሳችን ጥራት የለውም። አናናራችን ጥራት የለውም። ንግድ ሥርዓቱ ጥራት የለውም። ይህ እንደ ሀገር አሳሳቢ ነው። ጥራት ያለው ዜጋ ካልተፈጠረ ደግሞ ጥራት ያለው ምርት ማምረት የሚታሰብ አይደለም። ጥራት ያለው ዕቃ አምርቶም መጠቀም አይቻልም። ስለዚህም ኢትዮጵያውያን ለጥራት ትኩረት መስጠት አለብን። ኢትዮጵያም በጥራት ከሚታወቁ ሀገራት ተርታም መሰለፍ አለባት። የራሳችንን የምርምርና የጥናት ሥራዎች በማጠናከር ጥራት ያላቸውን ምርቶች አምርተን ቢያንስ ለሀገር ውስጥ ፍጆታ ማዋል አለብን ብለን እየተንቀሳቀስን ነው።

ስለዚህም ኢትዮጵያንና ሕዝቧን የሚመጥኑ ዕቃዎች እንዳይገቡ የተደረገበት መንገድ የሚያስቆጭ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥራት ያለው ነገር አይወድም ያለው ማን? ይህ እንደ ሀገር ሊያስቆጨን የሚገባ ጉዳይ ነው። ስለዚህም ኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ የሀገሪቱን የጥራት ደረጃ ከፍ ሊያደርጉ የሚገቡ መገልገያዎችን ለማምረትና ወደ ሀገር ውስጥም ለማስገባት የበኩሉን ጥረት ያደርጋል።

**አዲስ ዘመን፡- ቀጣይ የኢትዮ ኢንጂነሪንግ ዕቅድ ምንድን ነው ?**

**አምባሳደር ሱስይማን ደደፎ፡-** ኢትዮ ኢንጂነሪንግ ተዘርዝረው የተሰጡትን ኃላፊነቶች በአግባቡ እንዲወጣ ማድረግ ነው። የሀገሪቱን የኢንዱስትሪ ዘርፍ መምራት ዋነኛው ተልዕኮው ስለሆነ እሱ ላይ ጠንክሮ ይሰራል። በሀገር ውስጥ የማይመረቱና በሕዝብ ተፈላጊ የሆኑ ምርቶችን በሀገር ውስጥ በማምረት ክፍተርን መሙላት አንዱ ዓላማው ስለሆነ በዚህ ዘርፍም ውጤት ለማምጣት ይጥራል። ከዚህም አልፎ ለውጭ ገበያ አዳዲስ ሞዴል ያላቸውን መኪናዎች የማቅረብ ዕቅድ አለው። ጥናትና ምርምር በማድረግም የሀገሪቱ ኢንዱስትሪዎች ዘመናዊ አሰራርን እንዲከተሉና ተወዳዳሪ እንዲሆኑም ለማድረግ ይሰራል።

እነዚህን ተልዕኮዎቹን ለማሳካት ከወዲሁ የጀመራቸው ሥራዎች አሉ። ከጥቂት ወራት በኋላ ሞጆ ላይ በ50ሚሊዮን ዶላር ትልቅ የትራክተር ፋብሪካ መገንባት እንጀምራለን። በአፍሪካ ደረጃም ትልቅ ሊባል የሚችል ነው። ፋብሪካው ትራክተር የሚገጣጥም ሳይሆን ትራክተሩን ለማምረት የሚያስችሉ ዕቃዎችን የሚያመርት እራሱን የቻለ ፋብሪካ ነው። ይህ ፋብሪካ የትራክተር ሞተር ጭምር የሚያመርት ነው።

ባሉን ፋብሪካዎችም ሻንሲ የመሥራት አቅም እያዳበርን በመሆኑ፤ ሞተር ማምረት ከቻልን መኪና የማምረት አቅም ላይ እንደርሳለን። ከእኛ አቅም በላይ የሚሆኑትን ደግሞ ለሌሎች የሚሠሩ አካላት በመስጠት ሥራውን ለውጤት እናበቃለን። በውጭ ሀገራት ያሉ በርካታ ፋብሪካዎች ሁሉንም ነገር እራሳቸው አያመርቱም። ለመለስተኛ ተቋማት እንዲሠራላቸው ይሰጣሉ። ለምሳሌ ቦይንግ በኢትዮጵያ አየር መንገድ እንዲሠራ የሰጠው የአውሮፕላን ክፍል አለ። የኢትዮጵያ አየር መንገድ በአሁኑ ወቅት እያመረተ ለቦይንግ በማስረከብ ላይ ይገኛል። ገቢም በማግኘት ላይ ይገኛል።

ኢትዮ ኢንጂነሪንግም መኪናና ትራክተሮችን በራሱ ለማምረት ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል። ይህ የትራክተር ፋብሪካ ለግብርና አገልግሎት የሚውሉ ፓንፖችን ጭምር የሚያመርት ነው።

ኢትዮጵያ በግብርና የምትተዳደር ሀገር በመሆኗ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ትራክተር ያስፈልጋታል። በተለይም እያደገ የሚሄደውን ሕዝብ ቁጥር ለመመገብና ግብርናዋን ዘመናዊ ለማድረግ ሰላሳ አርባ ሚሊዮን ትራክተሮች ያስፈልጉናል። አሁን በተጨባጭ ያሏት የትራክተሮች ቁጥር በመላ ሀገሪቱ 100ሺ ትራክተር የሚሞላ አይመስለኝም። በዚህ የትራክተር ቁጥር ደግሞ ምርታማ ሆና ሕዝቧን መመገብ አትችልም። ከፍተኛ የምግብ እጥረት ያጋጥመናል። ይህ ደግሞ ለሀገሪቱ አደጋ ነው።

ተገዝተው በሚመጡ ትራክተሮች ብቻ የኢትዮጵያን ግብርና ማዘመን አይቻልም። ስለዚህም ኢትዮጵያ የራሷን ብራንድ መትከል ስለሚገባት በሚሊየን የሚቆጠር ትራክተር የሚያመርት ፋብሪካ መገንባት አለበት ብለን ወደ ተግባር በመግባት ላይ እንገኛለን።

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ሰፊ ማብራሪያ አመሰግናለሁ።**

**አምባሳደር ሱስይማን ደደፎ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## እምብዛም ትኩረት ያልተሰጣቸው የማዕድን ጌጣጌጦች

ሰሚራ በርሀ



በሀገራችን አብዛኛዎቹ ሰዎች ለማጌጥ ከሚመርጡት የማዕድን ዓይነቶች ወርቅና ብር በብዛት ይጠቀሳሉ። ሆኖም ግን በዓለም አቀፍ ደረጃ ብዙ የማዕድን ዓይነት ለጌጣጌጥ ይውላሉ። ማዕድናቱ የተለያዩ ዓይነት ሲሆኑ ጌጣጌጦችን በማስዋብ ሥራ ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎች ወቅቱን በሚፈልገው መልኩ አስውበው ለገበያ ያቀርባሉ። ከወርቅና ከብር በተጨማሪም እንደ ኦፓል፣ ኤመራልድ፣ ዳይመንድ፣ ቶፓዝ፣ አስፓየር እና ሳፋየር ከመሳሰሉ ማዕድናት ጌጣጌጦች ይሰራሉ። እነዚህም አብዛኛዎቹ ማዕድናት በሀገራችን በተለያዩ ቦታዎች ይገኛሉ።

በቅርቡም የማዕድን ሚኒስቴር ሀገራችን ያላት እምቅ የማዕድን ሀብት ለማስተዋወቅ ያለመ የማዕድን ኤክስፖ ማዘጋጀቱ ይታወሳል። ለአምስት ቀናት በቆየው ኤክስፖ ላይ በሀገራችን ያሉ የተለያዩ ዓይነት ማዕድናት ለእይታ ቀርበዋል። በኤክስፖው ላይ በዘርፉ የተሰማሩ የማዕድን አምራቾችና ላኪዎች ማህበራት ተሳትፈዋል።

በኤክስፖ ከተሳተፉት ‹‹ቱ ጂ ጀምስቶን›› የተሰኘ የማዕድን አምራችና ከማዕድን የሚሰሩ ጌጣጌጦችን ለዓለም ገበያ የሚያቀርብ ድርጅት አንዱ ነው። የድርጅቱ የጌጣጌጥ ሽያጭ ክፍል ባለሙያ ወጣት ሳራ ደጀኔ ከወርቅና ከብር ውጭ ከማዕድን ለሚሰሩ ጌጣጌጦች በሀገራችን ያለው ተቀባይነት እምብዛም መሆኑን ትናገራለች። ለዚህም ምክንያቱ እነዚህ ማዕድናት በመዋቢያ በጌጣጌጥ መልክ ተሰርተው ሲቀርቡ ብዙም የተለመደ ባለመሆኑ ማህበረሰቡ ማዕድናት ያላቸውን ጠቀሜታ እንዳልተረዳው ትናገራለች። ከዚህም በተጨማሪ በገበያው ላይ ያሉት በማዕድናት የተሰሩ ጌጣጌጦች የሚሸጡበት ዋጋ ሁሉንም የማህበረሰብ ክፍል ያማከለ አለመሆን ብዙዎች ሲጠቀሙበት አይታይም ትላለች።

በማዕድን የሚሰሩ ጌጣጌጦችን ለሁሉም ተደራሽ በሆነ መልኩ ለማቅረብ ሁሉም ግብዓቶች በሀገራችን እንደሚገኙ የምትጠቆመው ወጣት ሳራ፤ ድርጅታቸው ከማዕድን የተሰሩ ጌጣጌጦችን ሁሉንም የማህበረሰብ ክፍል ያማከሉ እንዲሆኑ ለማድረግ እየሠራ እንደሚገኝ ገልጻለች። ይህ የማዕድን አምራች ድርጅት በሀገራችን የማዕድን ሀብት ክምችት ስሙ በትልቁ ከሚነሱ አካባቢዎች ውስጥ በሻኪሶ ከተማ የራሱ የማዕድን ስፍራ ያለው ሲሆን በማዕድን የሚሰሩ ጌጣጌጦችን ከማቅረብ ባሻገር የተለያዩ ማዕድናትን ያቀርባል።

ሀገራችን በተለያዩ ተፈጥሯዊ ሀብቶች የበለጸገች ስትሆን በዓለም ላይ ካሉ የከበሩ ማዕድናት አብዛኛው እዚሁ ሀገራችን ውስጥ ይገኛሉ የምትለው ወጣት ሳራ፤ ነገር ግን በማዕድን ጌጣጌጥ ዘርፍ ላይ የተሰማሩ እና ማዕድን አምራቾችና ባለሙያዎች የሚቸገሩት ግብዓቶቹን እንደልብ አለማግኘት፣ ማዕድኑን አውጥቶ ለሚፈለገው አገልግሎት ለማዋል በሚጓጓዝበት ወቅት የሚገጥሙ የተለያየ ችግሮች ስለመኖራቸው ትገልጻለች። በሀገራችን ያለው የማዕድን አውጥቶ ለመጠቀም የሚያስችለው ቴክኖሎጂ ማሽነሪዎች በበቂ ሁኔታ አለመኖር እና የማዕድን ቴክኖሎጂ በሀገራችን የሚገኝበት ደረጃ በቂ እና ከጊዜው ጋር የሚሄድ አለመሆን በሥራው አንድ ተግዳሮት መሆኑን አንስታለች።

ወጣት ሳራ እንደምትለው፤ ድርጅቱ የማምረታቸው የማዕድን ጌጣጌጦችን ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ያቀርባል፤ በፋሽን ኢንዱስትሪ ዘርፍ ፋሽኑን የጠበቀ ከዘመኑ ጋር የሚሄድ የሚለው ርዕስ የተለመደ ሲሆን የሚሰሩ ጌጣጌጦችም እንዲሁ ወቅቱን የሚመስሉ እንዲሆኑ በደንበኞች ዘንድ ይፈለጋል። የመዋቢያ ጌጣጌጦችም የሚሰሩት ምንም እንኳን ከማዕድናት ቢሆንም በተለያየ ጊዜ እና ወቅት የሚኖራቸው ዲዛይን የሚፈለጉበት ዓይነትና ስሪታቸው ከጊዜ ጊዜ ይቀያየራል። በመሆኑም የማዕድን ጌጣጌጥ ሙያ ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎች ከዘመኑ ጋር የሚሄድ ዘመኑን የሚመጥኑ ጌጣጌጦች ከመሥራት ባሻገር ለሁሉም የእድሜ ክልል ውስጥ ለሚገኙ ደንበኞች የሚሆኑ ጌጣጌጦችን ለወጣቶች፣ ለሴቶች፣ የሚሆኑትን በማጥናት አዳዲስ ዲዛይኖችን ያቀርባሉ። በተጨማሪም ደግሞ ከማዕድን የተሰሩ ጌጣጌጦች ተቀባይነት እንዲያገኙ ለእይታ ቀለል ያሉ እና የሁሉንም የማህበረሰብ ክፍል ኪስ በማይጎዳ መልኩ ተመጣጣኝ በሆነ ዋጋ በሚያመሩ ዲዛይኖችን ጌጣጌጦች ይሰራሉ።

እነዚህን የማዕድን ጌጣጌጦች ወደ ገበያ ለማቅረብ በአብዛኛው ከደንበኞች ጋር በአካል በመገናኘት የገጽ ለገጽ ግብይትን የሚጠቀሙ ሲሆን ደንበኞች ወደ መሸጫ ሱቃቸው እና ቢሮአቸው በመምጣት የሚፈልጉትን የጌጣጌጥ ዓይነቶች እንደሚገዙ ትናገራለች። ስለማዕድን ጌጣጌጦች ሰዎች ያላቸው አቀባበል ብዙም ባለመሆኑ ጌጣጌጦቹን የሚያውቁ የረጅም ጊዜ ደንበኞች በማንኛውም ጊዜ ወደ ሱቃቸው በመምጣት የሚገበያዩ መሆኑን ጠቅሳ፤ የማዕድን ኤክስፖው ከሌሎች ባለሙያዎችና ድርጅቶች ጋር ልምድ እንዲለዋወጡ እድል እንደፈጠረላቸው ትናገራለች።

ሌላኛው በኤክስፖው ሲካፈል ያገኘነው ወጣት እያዩ ግዛው ‹‹ብራይተን›› ከተሰኘ የማዕድን አምራች የመጣ ሲሆን የጌጣጌጥ የማስዋብ ሥራ ባለሙያ ነው። ጌጣጌጦችን በማስዋብ ሥራ የ13 ዓመት ልምድ አለው። በኤክስፖው የተለያዩ ማዕድናትን ለእይታ ይዞ ቀርቧል። በሀገራችን ከማዕድን የተሰሩ ጌጣጌጦች ሽያጭ ብዙም ያልተለመደ በመሆኑ ድርጅታቸው ‹‹ብራይተን›› የሚሰሯቸውን ከማዕድን የተሰሩ ጌጣጌጦች በአብዛኛው ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡ ናቸው። ጌጣጌጦችን በተለያዩ ቅርጻና ዲዛይን ከማምረት ባሻገርም ራሳቸው ማዕድናቱንም በተለያየ ቅርጽ በማዘጋጀት ከከሰል ድንጋይ ጀምሮ ኦፓል ኤመራልድ፣ እና የመሳሰሉ ሌሎች ማዕድናትን ያቀርባሉ። በማህበረሰቡ ዘንድ ያለውን ተቀባይነትም ለማሻሻልና ከማዕድን የተሰሩ ጌጣጌጦችን እንዲለመዱ እየሰሩ ይገኛሉ።

ጌጣጌጥ ሲባል ተፈላጊነቱ ለመዋብ ውበትን ለማጉላት በመሆኑ የገዢዎች በመጀመሪያ ሲያዩት ዓይናቸው ሊወደው ይገባል የሚለው ወጣት እያዩ፤ በመሆኑም የደንበኞችን ፍላጎት ለማሟላት ወቅታቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ በሥራው የተሰማሩ ባለሙያዎች የራሳቸውን ልምድ በማከልና ክህሎታቸውን በማሳደግ አዳዲስ የጌጣጌጥ ዲዛይኖችን እንደሚያቀርቡ ይናገራል።

እንደ እያዩ ገለጻ፤ በኤክስፖው ላይ መገኘታቸው ለጎብኚዎች ማስታወሻ በመጣላቸው ግንዛቤ ስለመፍጠራቸው አንስቷል። ከሌሎች ተቋማት ጋር የልምድ ልውውጥ ከማድረግ ባሻገር ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር በጋራ ለመሥራት የሚያስችል የገበያ ትስስር የመፍጠር እድልን አግኝተዋል።

ኢትዮጵያ ያላትን የማዕድን ሀብት በመጠቀም ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ጥቅም እንድታገኝ መንግሥት ዘርፉ ላይ ከዚህ በበለጠ ትኩረት ሰጥቶ በመሥራትና የሚያስተዋሉ ሕገ-ወጥ ተግባር ላይ የተሰማሩ አካላትን በማስቆም፣ በግብይት ሂደቱ ላይም ያለውን እንቅስቃሴ ማሳደግ ይገባል ብሏል። በተጨማሪም በዘርፉ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ ባለሙያዎችን የሚያበረታታ የፖሊሲ ማሻሻያዎች በማድረግ አሁን ካለበት ደረጃ ከፍ ማድረግ እንደሚቻል ተናግሯል።

# ትዝብት/ ማረፊያ

## የግል ትምህርት ቤቶች «የግል ሥርዓተ ትምህርት»!

ሚዛን

ታላቁ የነጻነት ታጋይና የፖለቲካ መሪ የቀድሞው የደቡብ አፍሪካ ፕሬዚዳንት ኔልሰን ማንዴላ ለትምህርት የተለየ ፍቅር እንደነበራቸው ይነገራል። ብዙ ጊዜ ስለእርሳቸው ሲነሳ “ዓለምን መለወጥ የሚያስችል ብቸኛው መሳሪያ ትምህርት ነው” የሚለው አባባላቸው ሳይጠቀስ የማይታለፈውም ለዚሁ ነው። በርግጥም ትምህርት ራስን፣ አካባቢን፣ ሀገርንና ወገንን ከፍ ሲልም ዓለምን የመለወጥ ኃይል አለው። ይህንን የሚያደርገው ደግሞ የሰውን ልጅ የአስተሳሰብ አድማሱን በማስፋት፣ ዓለምን የሚመለከትበት ዕይታውን ወይንም አመለካከቱን በማስተካከልና ነገሮችን የመከወን ክህሎቱን በማሳደግ ነው።

ትምህርት የሰው ልጅ አዕምሮ ችግር ፈች በሆነ አስተሳሰብ እንዲሞላ ስለሚያደርገው አዳዲስ ነገሮችን የመፍጠር ብቃትን ያላብሰዋል። ዓለም በየጊዜው ያለፈችበት የለውጥ ሂደትና አሁን ላይ የደረሰችበት አጠቃላይ የሥልጣኔና የዕድገት ደረጃም የሰው ልጅ በትምህርት አማካኝነት በየጊዜው የሚገጥሙትን ችግሮች እየፈታና አዳዲስ ነገሮችን እየፈጠረ በአሸናፊነት ወደፊት መጓዝ የመቻሉ ውጤት ነው።

ለዚህ ደግሞ ትምህርት የሚጠበቅበትን ዓላማ ማሳካት እንዲችልና በትክክል የለውጥ መሳሪያ ሆኖ እንዲያገለግል የዜጎችን አካላዊና አዕምሯዊ የእድገት ደረጃ ያማከለና ሁሉንም እንደየፍላጎቱና አቅሙ ተጠቃሚ ሊያደርግ በሚችል ተገቢ ሥርዓተ ትምህርት ሊመራ ይገባዋል። ይሁን እንጂ በሀገራችን በተለያዩ አካባቢዎች በተለይም በመዲናችን አዲስ አበባ ከመደበኛው የሀገሪቱ ሥርዓተ ትምህርት ውጭ የሆነ የራሳቸውን ማስተማሪያ መጽሐፍ አዘጋጅተው የሚያስተምሩ አንዳንድ የግል ትምህርት ቤቶች መኖራቸውን በተለያየ አጋጣሚ ሕብረተሰቡ በስፋት ሲያነሳው የሚሰማ ጉዳይ ነው።

ከሰሞኑ በአንድ አጋጣሚ በዚሁ ጉዳይ ላይ የታዘብኩትና እንደ አንድ ኃላፊነት የሚሰማው ኢትዮጵያዊ በጉዳዩ ላይ አሳሳቢ ሆኖ ያገኘሁትን ችግርና ጉዳዩ የሚመለከተው አካል መፍትሔ ይፈልግለት ዘንድ ሃሳቤን ላካፍላችሁ ወደድኩ።

ከሰሞኑ ወደ አንድ ጓደኛዬ ቤት ጎራ ብዬ ነበር። አዲስ አበባ ውስጥ በአንድ የግል ትምህርት ቤት ውስጥ አስተማሪ ነው። ታዲያ ቤት ውስጥ ተቀምጠን ስለሥራ፣ ኑሮ... የተለያዩ ጉዳዮችን እያነሳን እየተጨዋወትን እያለ በመሃል “አንተ እኮ እንግሊዝኛ ነው ያጠናኸው፤ እስኪ እነዚህን መጽሐፎች እያቸው” አለና ከኋላው ካለው ጠረጴዛ ላይ አራት የሚሆኑ የ“ኤ4” መጠን ያላቸው ትልልቅ ሞጁል መሳይ መጻሕፍቶችን አንስቶ ሰጠኝ። እርሱ በሌላ የትምህርት መስክ ተመርቆ ነው በትምህርት ቤቱ ውስጥ የእንግሊዝኛ ቋንቋ አስተማሪ የሆነው። ይህንንም ያዙልኝና ወደዋናው ጉዳዬ ልለፍ።

ከዚያም በጥያቄው መሠረት መጻሕፍቱን ተቀብዬ በጉጉት ማገላበጥ ጀመርኩ። ሁሉም የአራተኛ ክፍል ማስተማሪያዎች ናቸው። በእያንዳንዱ ሞጁል ላይ የተጻፈው የትምህርት ዓይነት ስም እንደ ወረደ አንደኛው “ኢንግሊሽ”፣ ሁለተኛው “ስፖክን”፣ ሦስተኛው “ሪዲንግ ስኪል” አራተኛው ደግሞ “ጀኔራል ሳይንስ” ይላል። እርሱ እንዳለው የተመረኩበት የትምህርት ዘርፍ እንግሊዝኛ ቋንቋ በመሆኑ ትኩረቴን እንግሊዝኛ ሞጁሎቹ ላይ አድርጌ ምልከታየን ቀጠልኩ። “ኢንግሊሽ” የሚለውን ሞጁል አንስቼ የመጀመሪያውን ገፅ ገልበጥ አድርጌ ማውጫውን ስመለከት በመጀመሪያው ምዕራፍ ላይ “ፕሩፍ ሪዲንግ” የሚል ርዕስ ሳይ ክው ብዬ ደነገጥኩ።

ራሴን ማመን ስላቃተኝ በፍጥነት ሞጁሉን ዘጋሁትና እንደገና ጀርባውን አፍጥጬ ሳይ መጽሐፉ እውነትም ለአራተኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ ነው። ቀና ብዬ ጓደኛዬን በግርምት ተመለከትኩትና “እውነት ይሄን ለአራተኛ ክፍሎች ነው የምታስተምሯቸው?” በማለት ስጠይቀው “እኔን ግራ የገባኝና አንተ እንድታየው የፈለኩትም እኮ ለዚህ ነው” አለኝ። የአራተኛ ክፍል ሕጻናትን “ፕሩፍ ሪዲንግ” የሚያስተምር ትምህርት ቤት እንደ እውነታው “የዕውቀት ቤት” ሳይሆን “የውድቀት ቤት” በመሆኑ እዚያ አስተማሪ መሆን የሚጎዳው ትውልድን ብቻ ሳይሆን የአስተማሪውንም ኅሊና ጭምር ነውና በርግጥም ነገሩ ግራ ከማጋባት አልፎ የሚያሳዝንም ሆኖ ነው ያገኘሁት።

“ፕሩፍ ሪዲንግ” ማለት እኮ የንባብ የመጨረሻው ደረጃ ሲሆን ከፍተኛ የአዕምሮ ብስለትንና የማሰብ ችሎታን የሚጠይቅ ለአዋቂዎች ሳይቀር የሚከብድ ክህሎት ነው። ለአዋቂዎችም የሚከብድ ነው የሚባልበት ምክንያትም ትምህርቱ በእጅጉ አስተዋይነትንና ጥንቃቄ የሚፈልግ በመሆኑ ነው። ለአብነትም “kill him not, leave him” በሚለው ለቅጣት አስፈጻሚ ፖሊስ የተጻፈ የእንግሊዝኛ ዓረፍተ ነገር ውስጥ ኮማ የምትባለውን ሥርዓተ ነጥብ “not” ከሚለው ቃል በፊት ተሳስቶ ቢያስቀምጣት እንደማንኛውም ስህተት በይቅርታ ወይም በእርማት የሚታለፍ አይደለም፤ በመሳሳታችን ምክንያት ክቡር የሆነውን የሰው ሕይወት አጥፍተናልና! እንግዲህ እንዲህ ዓይነት ስህተቶችን የማስቀረት ክህሎት ነው “ፕሩፍ ሪዲንግ” የሚባለው።

ታዲያ ማንበብ በደንብ የማይችል አንድ የአራተኛ ክፍል ሕጻን ማንበብ እንኳን ሳይችል በምን ተዓምር ነው ከማንኛውም ዓይነት ስህተት በፀዳ መንገድ ማንበብን እንዲማር የሚደረገው? እኔው ራሴ ተምሬ የተመረኩት በእንግሊዝኛ ቋንቋ ሲሆን እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ “ፕሩፍ ሪዲንግ” የሚባል ነገር አላውቅም። ፕሩፍ ሪዲንግን የተማርኩት ዩኒቨርሲቲ ከገባሁ በኋላ ያውም መጨረሻ ዓመት ላይ ነው። እዚህ ግን ማንበብና መጻፍ እንኳን በደንብ ያለመዱ የአራተኛ ክፍል ሕጻናት ያለ አቅማቸሁ ተማሩ ተብለው ሲጨነቁ ይውላሉ።

ይህን በማሳያነት አነሳን እንጂ ሌላም ብዙ ብዙ ነገር አለ። ከላይ እንደቀረበው አንዱ የእንግሊዝኛ ቋንቋ የትምህርት ዓይነት “ኢንግሊሽ”፣ “ስፖክን” “ሪዲንግ ስኪል” አንዳንዶቹ የግል ትምህርት ቤቶች አካባቢ ደግሞ “ራይቲንግ” ተብሎ አንዱን አራት ጊዜ ያስተምሯቸዋል። ተመልከቱ እንግዲህ ስፖክን፣ ሪዲንግና ራይቲንግ በቋንቋው ውስጥ የሚገኙ ክህሎቶች ሆነው እያለ የተለያየ የትምህርት ዓይነት ሆነው ሥርዓተ ትምህርት ተቀርጾላቸው መጽሐፍ ተዘጋጅቶላቸው ተማሪዎች እንዲማሩ ሲደረግ። እናማ እንግዲህ በእንግሊዝኛ ጻፍ ስትለው “በራይቲንግ ነው እንጂ በእንግሊዝኛ መጻፍ ይቻላል እንዴ? የሚል ትውልድን ቀርጸው እስከሚያስረክቡን በትዕግስት መጠበቅ ነው እንጂ ምን እንላለን።

ሌላም አለ። “ጀኔራል ሳይንስ” የትምህርት ዓይነታቸው ደግሞ እነዚህን የአራተኛ ክፍል ሕጻናት ልጆቻችንን ማወቅ ስለሚገባቸው ስለ አምስቱ የስሜት ህዋሳትና ስለ ዋና ዋና የአካል ክፍሎቻችን አገልግሎት ትተው ለሕጻናቱ ቀርቶ ስፔሻሊስት ሃኪሞች እንኳን በስንት ድካም የሚረዱትን ውስብስቡን የሥርዓተ ነርቭ ሳይንስ ያስተምሯቸዋል ማለቴ ያሰፍሩባቸዋል። ስለ ሥርዓተ ነርቭ የተማርኩት አስረኛ ክፍል ላይ መሆኑን በሚገባ አስታውሳለሁ፣ ከሥነ ሕይወት ትምህርት ብዙዎቻችን የሚከብደንም ይኼ እንደነበርም ትዝ ይለኛል።

እናም የተማሪዎችን ዕድሜ፣ የአዕምሮ ዕድገት ደረጃና አቅም ያላገናዘበ በአንዳንድ የግል ትምህርት ቤቶች ጥቅም ላይ እየዋለ የሚገኘው የትምህርት ሥርዓት ችግር የሚፈታ ሳይሆን ትውልድን ለችግር የሚያጋልጥ አካሄድ ነው። ከዚህም ባሻገር በአንድ ሀገር ውስጥ የግል ትምህርት ቤት እንጂ የግል ሥርዓተ ትምህርት ሊኖር ስለማይችል ሁኔታው መፍትሔ ሊፈለግለት ይገባል።

# ዓለም አቀፍ




## 118 ሀገራት የታዳሽ ኃይል ልማታቸውን በሦስት እጥፍ ለማሳደግ ተስማሙ

በጋዜጣው ሪፖርተር

118 ሀገራት የታዳሽ ኃይል ልማት ላይ በትብብር መሥራት የሚያስችላቸውን ስምምነት በዱባይ ተፈራርመዋል።

አስገዳጅነት አይኖረውም የተባለው ስምምነት በ2030 ከታዳሽ የኃይል ምንጮች የሚገኘውን ኃይል አሁን ካለበት በሦስት እጥፍ ለመጨመር የሚያስችል ነው።

ሀገራቱ ከፀሐይ፣ ንፋስ እና ውሃ የሚገኘውን የኤሌክትሪክ ኃይል ወደ 11 ሺህ ጊጋ ዋት ከፍ ለማድረግ ነው ቃል የገቡት።

እቅዱን ለማሳካት የሀገራት ነባራዊ ሁኔታ ከግምት ውስጥ መግባቱን የኮፕ28 ፕሬዚዳንት ዶክተር ሱልጣን አል ጃበር ገልጸዋል።

118ቱ ሀገራት የኃይል አጠቃቀማቸውን ለማዘመን እና ብክነትን ለመቀነስ መስማማታቸውም በዱባይ በተፈረመው የቃልኪዳን ሰነድ ላይ ሰፍሯል።

ከዓለማችን የከባቢ አየር ብክለት 80 በመቶ ድርሻ ያላቸው የቡድን 7 እና 20 አባል ሀገራትም ለዚህ ስምምነት ድጋፋቸውን መስጠታቸው ተገልጿል።

የአውሮፓ ኅብረት ኮሚሽን ፕሬዚዳንት ኡርሱላ ቮን ደር ላይን ስምምነቱ በታዳሽ ኃይል ልማት ላይ ለተሰማሩ አልሚዎች “ትልቅ ብስራት” ነው ብለዋል።

በአሁኑ ወቅት በዓለምአቀፍ ደረጃ ከታዳሽ የኃይል ምንጮች የሚገኘው ኃይል 3 ሺህ 400 ጊጋዋት ብቻ መሆኑንም ነው ያብራሩት።

የዓለም አቀፉ የታዳሽ ኃይል ኤጀንሲ መረጃ እንደሚያሳየው በ2022 መጨረሻ የታዳሽ ኃይል ምንጮች ያስገኙት ኃይል 3 ሺህ 372 ጊጋዋት ነው፤ ከዚህም ውስጥ 37 ከመቶው ከውሃ፤ 31 ከመቶው ደግሞ ከፀሐይ የተገኘ ነው ሲል የዘገበው አል ዓይን ነው።




## ዓረብ ኢምሬት ስተጋላጭ ማኅበረሰብ የውሃ ደኅንነት 150 ሚሊዮን ዶላር ለገሰች

በጋዜጣው ሪፖርተር

ዓረብ ኢምሬት ለተጋላጭ ማኅበረሰብ የውሃ ደኅንነት 150 ሚሊዮን ዶላር ለገሰች።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በየዓመቱ በአየር ንብረት ለውጥ ዙሪያ የዓለም ሀገራት፣ የአየር ንብረት ለውጥ ባለሙያዎችን እና ሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይመክራል፡፡

ይህ ጉባኤ በተመድ አባል ሀገራት እየተዟዟረ በየዓመቱ የሚካሄድ ሲሆን የዘንድሮው ዓለም አቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ በተባበሩት ዓረብ ኢምሬት አስተናጋጅነት በዱባይ በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡

ካሳለፍነው ዓርብ ጀምሮ እየተካሄደ ያለው የዚህ ዓለም አቀፍ ጉባኤ አዘጋጅ የሆነችው ዓረብ ኢምሬት ተጨማሪ ድጋፎችን እንደምታደርግ አስታውቃለች፡፡

ሀገሪቱ ላልተረጋጉ ሀገራት የውሃ ደኅንነታቸውን ለማረጋገጥ 150 ሚሊዮን ዶላር ድጋፍ እንደምታደርግ አስታውቃለች፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ከግል ባለሀብቶች እና የንግድ ኩባንያዎች 18 ቢሊዮን ድርሃም ወይም 5 ቢሊዮን ዶላር በመሰብሰብ ለአካባቢ ጥበቃ ሥራዎች ድጋፍ እንደምታውልም ገልጻለች፡፡

በዱባይ እየተካሄደ ባለው 28ኛው የተመድ አየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ ላይ የ200 ሀገራት መሪዎች፣ የአየር ንብረት ለውጥ ባለሙያዎች፣ የተቋማት መሪዎች እና ሌሎች ተጋባዥ እንግዶች በመሳተፍ ላይ ናቸው፡፡

ዓረብ ኢምሬትን ጨምሮ የተለያዩ ሀገራት ለአየር ንብረት ለውጥ ጉዳት ፈንድ ያዋጡት ገንዘብ 400 ሚሊዮን ዶላር መድረሱ ተገልጿል፡፡

የዓረብ ኢምሬትስ ፕሬዚዳንት ሼክ ሞሐመድ ቢን ዛይድ ሀገራቸው ለአየር ንብረት ለውጥ መፍትሔዎች የ30 ቢሊዮን ዶላር ፈንድ ማቋቋሟን ማስታወቃቸው ይታወሳል።

ለአየር ንብረት መፍትሔዎች ፈንድ የተቋቋመው የአየር ንብረት ፋይናንስ ክፍተቱን ለመሙላት እና ገንዘቡ በተገቢው መልኩ ተደራሽነቱን ለማመቻቸት ነው ብለዋል ሲል የዘገበው አል ዓይን ነው።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
ዘመን
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንዘብ ድረገጾቻችንንና ፌስቡክ ገጾቻችንን ይቃብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን
ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# የኢትዮጵያውያን የበላይነት የነገሰበት የቫሌንሲያ ማራቶን

ቦጋለ አበበ

በስፔኗ የባህር ዳርቻ ከተማ ቫሌንሲያ ታላቁ የቫሌንሲያ ትሪኒዳድ አልፎንሶ ማራቶን ትናንት ሲካሄድ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በሁለቱም ፆታ የበላይነት ይዘው ፈፅመዋል። የዓለማችን ከዋክብት አትሌቶች በተፋለሙበት በዚህ ውድድር ብዙም የአሸናፊነት ግምት ያልተሰጠው አትሌት ሲሳይ ለማ የቦታውን ክብረወሰን በመስበር አሸናፊ ሆኗል። በሴቶች አትሌት ወርቅነሽ ደገፋ አሸንፋለች።

የ2021 ለንደን ማራቶን አሸናፊው ሲሳይ ርቀቱን ለማጠናቀቅ 2:01:48 የወሰደበት ሲሆን፤ ይህም የቦታውን ክብረወሰን ከመሆን ባሻገር የራሱን ምርጥ ሰዓት ያሻሻለበት ሆኗል። በተጨማሪም ከጀግናው አትሌት ቀነኒሳ በቀለ በመቀጠል ሁለተኛው ኢትዮጵያዊ የማራቶን ፈጣን ሰዓት ባለቤት አድርጎታል።

ሲሳይ ለማ ገና ከጅምሩ ጠንከር ያለ ፍጥነት በመሮጥ ከሌላኛው ኢትዮጵያዊ ዳዊት ወልዴ እና ኬንያዊው ኪቢወት ካንዲ ጋር መሪነቱን ቢቀላቀልም ከ35ኛው ኪሎ ሜትር በመምጣት ውድድሩን በ 2፡01 48.በሆነ ድንቅ ሰአት የፍጻሜውን መስመር በማለፍ ባለፈው ዓመት በኬንያዊው ኬልቪን ኪፕተም (2:01:52) የተያዘውን የቦታውን ክብረወሰን ሰብሯል። በዚህ ውድድር ትኩረት ያልተሰጠው ኬንያዊው አትሌት አሌክሳንደር ሙቲሶ ሲሳይን ተከትሎ በመግባት በ2:03:10 ሁለተኛ ሆኖ አጠናቋል። ሌላኛው ኢትዮጵያዊ አትሌት ዳዊት ወልዴ 2:03.48 በመግባት ሦስተኛ ደረጃ ይዞ ሲያጠናቅቅ፣ በርቀቱ ከፍተኛ የአሸናፊነት ግምት ተሰጥቶት የነበረው ቀነኒሳ በቀለ 2:04.19 አራተኛ ደረጃ ይዞ አጠናቋል።

የዓለማችን ሦስተኛው ፈጣን የማራቶን ሰአትን በ2፡01.41 በበርሊን 2019 ማራቶን የጨበጠው ቀነኒሳ በቀጣዩ የፓሪስ ኦሊምፒክ ላይ ለአራተኛ ጊዜ ሀገሩን ለመወከል ትልቅ ጉጉት



አትሌት ሲሳይ ለማ፣




አትሌት ወርቅነሽ ደገፋ፣

የነበረው ሲሆን፤ እዚያ የሚያደርሰውን ቲኬት ለመቁረጥ የሚያስችለውን ሚኒማ ለማሟላት ያለው ብቸኛ አማራጭ ይህ የቫሌንሲያ ማራቶን ነበረ። ለዚህም ጥሩ ዝግጅት በማድረግ ከፍተኛ አሸናፊነት ግምት አግኝቶ ነው ወደ ውድድር የገባው።

ጀግናው አትሌት ከውድድሩ ቀደም ብሎ “ከዚህ ቀደም በትራክ እና በሀገር አቋራጭ ውድድሮች ላይ የተቀዳጃቸውን ታላላቅ ድሎች በጎዳና ላይ ውድድሮች መድገም አልቻልኩኝም። በማራቶንም የአቅሜን ያህል ስኬታማ ነኝ ብዬ አላስብም። ለረጅም ጊዜያት ከጉዳት ጋር ስታገል ቆይቻለሁ። ጠንካራ ልምምዶችን ስሰራ ቆይቻለሁ፤ ነገር ግን ልምምዶቼን በጥሩ መንገድ ጨርሼ አላውቅም። አዕምሮዬ የሚነግረኝ አሁንም በማራቶን የተሻለ ነገር መሥራት እንደምችል ነው። ብዙ ግቦች አሉኝ። ኦሊምፒክ ከፊታችን አለ። ምናልባትም ፓሪስ የመጨረሻው ኦሊምፒኬ ሊሆን ይችላል።” በማለት ተናግሮ ነበር። ይሁን እንጂ የቀድሞው የኦሊምፒክ የሦስት የወርቅ ሜዳሊያ አሸናፊ እንዲሁም የ10ና 5ሺ ሜትር ባለክብረወሰን ቫሌንሲያ ላይ ሊሳካለት አልቻለም። ያስመዘገበው 2:04:19 ሰአት ግን የዓለም የአንጋፋዎችን የማራቶን ክብረወሰን የሰበረ ሆኗል።

ቀነኒሳ ከውድድሩ በኋላ በማኅበራዊ ትስስር ገፁ ባሰፈረው መልእክት በቫሌንሲያ ያስመዘገበው ውጤት ወደፊት የተሻለ ሰአት ለማስመዝገብ ተስፋ እንዳሳደረበት ገልጿል። በውድድሩ የነበረው ድጋፍ ከጠበቀው በላይ እንዳስደሰተውና ቫሌንሲያ ክብረወሰን ሊመዘገብበት የሚችል ጥሩ ውድድር እንደሆነ ጠቁሞ ምስጋናውን አቅርቧል።

የ5 እና የ10 ሺ ሜትር የዓለም ክብረወሰኑን ከቀነኒሳ የተረከበው የዓለምና የኦሊምፒክ ቻምፒዮኑ ዩጋንዳዊ አትሌት ጆሽዋ ቼፕቴጌይ የመጀመሪያ የማራቶን ውድድሩን ትናንት ቫሌንሲያ ላይ ማድረጉን ተከትሎ ከቀነኒሳ ጋር የሚያደርገው ፉክክር ከፍተኛ ግምት አግኝቶ ነበር። ይሁን እንጂ ቼፕቴጌ በውድድሩ የተጠበቀውን ብቃት ሳያሳይ አቋርጦ ወጥቷል።

በሴቶች መካከል በተካሄደው ውድድር ከወሊድ መልስ ውድድሯን ያደረገችው አትሌት ወርቅነሽ ደገፋ በድንቅ ብቃት ወርቁን አጥልቃለች። ወርቅነሽ በ2፡15.51 ሰአት የግል ምርጥ ሰአቷን በማሻሻል በታሪክ 7ኛዋ ፈጣን አትሌት ሆናለች። በዚሁ ውድድር የሪዮ ኦሊምፒክን በ10ሺ ሜትር የዓለም ክብረወሰን ታጅባ ያሸነፈችው አትሌት አልማዝ አያና የራሷን ፈጣን ሰዓት አስመዝግባ 2ኛ ሆና ስታጠናቅቅ፤ ህይወት ገብረኪዳን 3ኛ በመሆን ውድድሩ በኢትዮጵያውያን የበላይነት ሊጠናቀቅ ችሏል። የቀድሞዋ የ1500 ሜትር የዓለም ቻምፒዮን የክብረወሰን ባለቤት ገንዘቤ ዲባባ ውድድሩን ማጠናቀቅ አልቻለችም።

የቦስተን እና የዱባይ ማራቶን አሸናፊዋ አትሌት ወርቅነሽ በ33 ዓመቷ ወደ ቀድሞ ድንቅ ብቃቷ የተመለሰችበትን ውጤት በቫሌንሲያ አሳክታለች። ወርቅነሽ ያለፉትን ሁለት ዓመታት ሁለት ጊዜ በወሊድ ምክንያት ከውድድር ርቃ ቆይታለች። አትሌቷ ከሳምንታት በፊት ወደ ውድድር በተመለሰችበት መድረክ የግማሽ ማራቶን ርቀትን 1:07:48 በሆነ ሰአት አጠናቅቃ ወደ ቀድሞ ብቃቷ ለመመለስ ብዙ እንዳልራቀች አሳይታ ነበር።

ሁለተኛ በመሆን ያጠናቀቀችው የ32 ዓመቷ አትሌት አልማዝ አያና ፊቷን ወደ ማራቶን ካዞረች ጥቂት ጊዜ ቢሆናትም በመድረኩ ግን እያስመዘገበች ያለው ውጤት ብዙዎችን ያስደነቀ ሆኗል። አልማዝ ባለፈው በአምስተርዳም ማራቶን የመጀመሪያ ማራቶን ውድድሯን ማሸነፏ ይታወሳል።